# እራስን የመገምገሚያ የመሳርያ ጥቅል ፡-

## ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ሰርቫይቨሮች ሁለንተናዊ ድጋፍ ለማድረግ የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን እንዲሁም መልካም እድሎችን መተንተን



GIJTR
Global Initiative for Justice
Truth & Reconciliation

## ስለ ኢንተርናሽናል ኮአሊሽን ኦፍ ሳይተስ ኦፍ ኮንሽንስ

ኢንተርናሽናል ኮአሊሽን ኦፍ ሳይትስ ኦፍ ኮንሽንስ (ICSC ወይም ጥምረቱ) የሰብዓዊ መብቶች ልዩ የሆኑ ውጣ ውረዶችን በማስታወስ እና የሚያስከትሏቸውን ውጤቶች በመፍታት ፍትሃዊ እና ስላማዊ የሆነ መጪ ዘመንን ለመገንባት የሚተጋ ዓለም አቅፍ የሙዚየሞች፣ ታሪካዊ ስፍራዎች እንዲሁም ከማህረሰቦች ጋር በቅርበት የሚሰሩ ስራዎች መረብ ነው። እ.አ.አ በ1999 የተመሰረተው ይህ ጥምረት በአሁኑ ወቅት ከ 300 በላይ ሳይትስ ኦፍ ኮንሽንስ አባላትን በ65 ሀገራት ያካትታል።ጥምረቱ እነዚህን አባላቱቶቹን በጋራ መስራትን እና ዓለም አቅፍ የእውቀት እና የመልካም ተሞክሮ ልውውጦችን በሚያበረታቱ ሰባት ክልልላዊ መረቦች በኩል ይደግፋል። ለፍትህ፣ እውነት እና እርቅ ዓለም አቀፍ ኢኒሺየቲቭ ( ግሎባል ኢኒሺዬቲቭ ፎር ጀስቲስ፣ ትሩዝ ኤን ሪኮንሲሊዬሽን GIJTR) የጥምረቱ ዋነኛ መርሃግብር ነው።

International Coalition of SITES *of* CONSCIENCE

**Learn more at www.sitesofconscience.org.**

**ምሳሌዎች:** Ignatius Ade

# ስለዚህ እራስን የመገምገሚያ የመሳርያ ጥቅል

**በ2024 የታተመ ሲሆን ይህ እራስን የመገምገሚያ የመሳርያ ጥቅል በ GIJTR አባላት ህብረት፣ ICSC እና የሁከት እና የእርቅ ጥናት ማእከል (CSVR) የተደረጉ ምርምሮችን እንዲሁም የህብረት ለፍትህ ፣ የዓለም አቅፍ ወንጀል ምርመራ ኢንስቲቲዩት (IICI) ፣ የ ዶ/ር ዴኒስ ሙክዌጌ ፋውንዴሽን እና ዓለም አቀፍ የተጎጂዎች ፈንድ (ግሎባል ሰርቫይቨርስ ፈንድ) አማካሪ አጋሮች የባለሙያ ግብአት ያሰባሰበ ነው።**

ይህ እራስን የመገምገሚያ መሳርያ ጥቅል የሲቪል ማህበር ድርጅቶች (የሲቪል ማህበራት) እውነትን፣ ፍትህን እና ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት የደረሰባቸውን ሰርቫይቨሮችን ለመፈወስ የሚጫወቱትን ከፍተኛ ሚና እውቅና በመስጠት ለሲቪል ማህበር ድርጅቶች ተዘጋጅቷል። የመሳርያ ጥቅሉ አላማ ሲቪል ማህበራት የሰርቫይቨሮች ሁሉም ፍላጎቶች በራሳቸው አውድ ውስጥ ምን ያህል በተጠቃለለ መልኩ እየተሟሉ መሆኑን እና ሲቪል ማህበራት በመርሃ ግብሮቻቸው ሊሞሉዋቸው የሚችሏቸው ክፍተቶች ካሉ እንዲገመግሙ መሳርያዎችን ለማቅረብ ነው። ይህ እራስ ግምገማ የሲቪል ማህበራትን ነባር የጠለቀ እውቀት በሚሰበስብ መልኩ የተዘጋጀ እና በድርጅቶች፣ በግለሰብ ድረጃ፣ እንዲሁም በቡድን ሆነው በሚሰሩ ድርጅቶች ሊተገበር የሚችል ነው።

ይህ መሳርያ ድርጅቶች እና በግንባር ቀደምትነት የተሰለፉ ባለሙያዎችን ከተለያዩ አውድ ውስጥ የተረፉትን ለመደገፍ የተሻሉ ልምዶችን ያጋራል፤ እንዲሁም በኢስያ ፍትህ እና መብቶች (AJAR)፣ የ ዶ/ር ዴኒስ ሙክዌጌ ፋውንዴሽን፣ የሰብአዊነት ህግ ማእከል፣ ዓለም አቀፉ የእውነት እና ፍትህ ፕሮጀክት፣ PEECH አፍሪካ ፋውንዴሽን፣ ሩታ ፓሲፊካ ዲ ላስ ሙጀእርስ እና ህብረት ለፍትህ የተዘጋጁ ከ20 በላይ ጥልቅ ቃለመጠይቆችን እና ሰባት ጥናቶች የተሰበሰቡ እይታዎችን ያካተተታል። ይህ መሳርያ ከሩታ ፓሲፊካ ዲ ላስ ሙጀእርስ ጋር በጋራ በመሆን በሜዲሊን ኮሎምቢያ በኅዳር 2023 እንዲሁም ዶ/ር ዴኒስ ሙክዌጌ ፋውንዴሽን ጋር በባንጂል፣ ማእከላዊ አፍሪካ ሪፐብሊክ በጥር 2024 ተሞክሯል።

ይህ የመሳርያ ጥቅል በመልካም ተሞክሮዎችን እና በዘርፉ ላይ ያሉትን እድገቶች ለማካተት የሚሻሻል ሰነድ እንዲሆን የታቀደ ነው። GIJTR ሰነዱን ከተጠቀሙ ድርጅቶች አስትያየቶችን የሚቀበል ሲሆን በ gijtr@sitesofconscience.org መላክ ይቻላል።

### ምስጋናዎች

**አዘጋጆቹ ለዚህ ሰነድ ግዜ እና ሙያቸውን ላበረከቱ በርካታ ግለሰቦች ምስጋና ያቀርባሉ። አዘጋጆቹ ጥልቅ የሆነ አድናቆት በተለይም መሳርያውን በማዘጋጀት ወቅት በእያንዳንዱ ደረጃ መሳርያውን ቅርፅ በማስያዝ ትልቅ ሚና ለተጫወቱ ሰርቫይቨሮች አላቸው። በእዚህ ሰነድ ላይ በስም ባይገለፁም በሰነዱ ውስጥ የሚገኙት የአብዛኞቹ ቁልፍ የሆኑ ምልከታዎች ምንጭ እንዲሁም በይበልጥ ፍትሃዊ፣ሰላማዊ የሆነ ቀጣይ ዘመን ለመፍጠር የሚተጉ ለዚህ መርሃግብር መነሻዎች ናቸው።**

የመሳርያውን የሙከራ ስራዎችን በኮሎምቢያ እና ሴንትራል አፍሪካን ሪፕብሊክ ስለመሩ ለማሪና ጋሌጎ ዛፓታ፣ ኬሊ ኢቺኢቭሪይ፣ ዶሚኒክ ቪዳሌ-ፕልዛ እና ሳራ ኮሊንስ አዘጋጆቹ የተለየ ምስጋና ያቀርባሉ። በሙከራ ስራው ላይ የተሳተፉት በቀጣይ የተዘረዘሩት ድርጅቶች ተወካዮች መሳርያውን ለማጠናከር እና ከተጎጂዎች ጋር በቅርበት የሚሰሩ ድርጅቶችን ተጨባጭ ሁኔታ እንዲያጤኑ አዝጋጆቹን በመደገፍ የማይተካ አስተዋፆ ነበራቸው፤ አሚጋ ጆቨን፣ ኮርፖራሲኦን ፓራ ላ ቪዳ ሙጄኤርስ፣ ኪዩ ክሪአን፣ኮርፖራሲኦን ቫሞስ ሙጄር፣ ኮንሴጀሪአ ዴ ሙጄር የ ጄኒሮ ድ ላ ኦርጋናዜሲኦን ኢንዲገኢና ዲ አንቲኦኩአ፣ ሩታ ፓሲፊካ ዲ ላስ ሙጄኤርስ አንቲኦኩአ፣ ኮርፖራሲኦን ፕሪኢማቬራ፣ ሬድ ኮሎምቢአና ዲ ሙጄኤርስ ፖር ሎስ ዲሪቾስ ሴክሹአልስ የ ሪፕሮዳክቲቮስ፣ ኮሌስቲቫ ጆስቲካ ሙጄኤር፣ ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ሰርቫይቨሮች ብሔራዊ ንቅናቄ (MOSUCA) ተጎጂዎች ብሔራዊ ንቅናቄ፣ የ ካውንስል ናሺኦናል ዲ ኤድ አዩ ቪክቲምስ (CNAV) እና በማእከላዊ አፍሪካ ሪፕብሊክ የሴቶች ጠበቆች ማህበር። ለካሪ ኮመር፣ ማርታ ቫሊኢናስ፣ ኒኢቪስ ጎሜዝ፣ እና ቬኒታ ጎቬንደር የሙከራ ስራውን በምስተባበር እና የመሳርያውን የመጀመርያ ረቂቅ ላደረጉት ማስተዋል የተሞላበት ግብአት ልዩ ምስጋና ያቀርባሉ።

**ዋና አዘጋጆች፡-** ኦሊቪያ ሄድ እና ሳራ ኬዝ (ICSC).
**አስተዋፆ ያደረጉ፡-** ብሬት ኤድዋርድስ (ICSC)፤ ክሪስቲ ፉጂኦ እና ሜራ ኤፍታኢሃ (ህብረት ለፍትህ)፤ ጋብርኤል ኦስቱኢዘን (IICI)፤ ዶሚኒክ ቪዳሌ-ፕላዛ (ዶ/ር ዴኒስ ሙክዌጌ ፋውንዴሽን)፤ ክላራ ሳንዶቮአል (ግሎባል ሰርቫይቨርስ ፈንድ) እና ኬቲ አና ፖትጊተር፣ ሌዝሊ ኩማሎ፣ እና አሚና ማዋኢኪአምቦ (CRSV)።

---

**gijtr.org**



# ስለ GIJTR

**በዓለም ዙርያ ከፍተኛ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ታሪክ ያላቸው ሀገራት ከጨቋኝ ሰርአት ወደ አሳታፊ እና ዴሞክራሲያዊ መንግስታዊ ስርዓት የሚያደርጉት ሽግግር ላይ ጥላ ባጠላባቸው ሀገራት ለፍትህ፣ እውነት እና እርቅ እየጨመረ የመጣ ጥሪ አለ። ይህንን ፍላጎት ለማሟላት ጥምረቱ በ GIJTR ነሐሴ 2014 አስጀመረ። GIJTR በግጭት ውስጥ ወይም በሽግግር ውስጥ ያሉ እየተፈፀሙ ባሉ ወይም የተፈፀሙ የሰብአዊ መብቶች በደሎች ባሉባቸው ሀገራት ያሉ አዲስ ችግሮችን ለመፍታት ይሰራል። ጥምረቱ GIJTRን ይመራል፣ ሌሎች ስምንት ድርጅታዊ ጥምረቶችን ጨምሮ፡- አሜሪካ ባር አሶስዬሽን ሩል ኦፍ ሎ ኢኒሺዬቲቭ (ABA ROLI)፣ ዩናይትድ ስቴትስ፤ AJAR፣ ኢንዶኔዢያ፤ CSVR፣ ደቡብ አፍሪካ፤ ዶኩመንቴሽን ሴንቴር ኦፍ ካምቦዲያ (DC-Cam)፣ ካምቦዲያ፤ ዲዩ ፕሮሰስ ኦፍ ሎ ፋውንዴሽን (DPLF)፣ ዩናይትድ ስቴትስ፤ ፋውንዴሲኦን ዲ አንትሮፖሎጂአ ፎሬንሴ ዴ ጉዋተማላ (FAFG)፣ ጉዋተማላ፤ የሰብአዊነት ህግ ማእከል (HLC)፣ ሰርቢያ፤ እና ፕብሊክ ኢንተርናሽናል ሎ ኤንድ ፖሊሲ ግሩፕ (PILPG)፣ ዩናይትድ ስቴትስ። የ GIJTR አባላትን እውቀት ጥቅም ላይ ከማዋል በተጨማሪ ጥምረቱ በ65 ሀገራት የሚገኙ ከ 300 በላይ አባላቶቹን ለረዥም ጊዜ የቆየ ማህበራዊ ግንኙነት የGIJTRን ስራ ለማጠናከር እና ለማስፋት ጥቅም ላይ ያውላል። GIJTR አጋሮች ከጥምረቱ አባላት ጋር በመሆን ለከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ፍትህ እና ተጠያቂነት ወደነበረበት የመመለስ እንዲሁም የበቀል ስልቶችን በመጠቀም የተለያዩ የፈጣን ምላሽ እና ከፍተኛ**

**ውጤት መርህ ግብር ተግባራትን አዘጋጅተው ተግባር ላይ አውለዋል።**

በ GIJTR ስር ያሉ ድርጅቶች እውቀት የሚከተሉትን ያካትታል፤

- እውነትን ይፋ ማውጣት፣ እርቅ፣ መታወሻ/መታሰቢያ ስራዎች፣ እና ሌሎች የታሪካዊ ማስታወሻ አይነቶች
- የሰብአዊ መብቶች በደሎችን ለሽግግር ፍትህ አላማ መሰነድ
- ከጠፉ እና የተሰወሩ ሰዎች ጋር የተያያዙ የፎሬንዚክ ትንተና እና ሌሎች ስራዎች
- ፍትህ የማግኘት፣ የስነ ልቦና ድጋፍ፣ እና የስሜት ቀውስ መቀነስ ተግባራትን የመሳሰሉ ለተበዳዮች የሚደረግ ውትወታ
- የሽግግር ፍትህ ሂደቶችን እንዲያስተዋውቁ እና በሂደቶች ውስጥ እንዲሳተፉ ለሲቪል ማህበራት አክቲቪስቶች እና ድርጅቶች የቴክኒክ እገዛዎች መስጠት እና አቅም መገንባት
- የማካካሻ ፍትህ ተግባራት
- በእነዚህ ሁሉ ሂድቶች ውስጥ በሙሉ የስርዓተ ጾታ ፍትህን ማረጋገጥ

እስከ ዛሬ ድረስ GIJTR በብዙ ሀገራት ውስጥ የሲቪል ማህበራትን የመሰነድ እና እውነትን ይፋ የማውጣት መርሃ ግብሮችን ማዘጋጀት እና መተግበር ሂደትን መርቷል፤ የመታወሻ/መታሰቢያ ስራዎችን ፣ የስነዳ፣ እና የአካባቢያዊ ድርጅቶችን የስነልቦና ድጋፍ አቅም ግምገማዎችን ተግብሯል፤ እና በኢስያ፣ አፈሪካ፣ እና መካከለኛው ምስራቅ እና ሰሜን አፍሪካ ክፍሎች ለተጎጂዎች ስልጠና፣ ድጋፍ፣ እና በማህበረሰብ የሚመሩ የሽግግር ፍትህ መንገዶችን በመንደፍ እና በመተግበር ውስጥ እንዲሳተፉ እድሎችን መስጠት። የ GIJTR አጋሮች እና የጥምረቱ ኔትወርክ አባላት የልምድ እና ክህሎት ልዩነት በመኖሩ፣ መርሀ ግብሩ ከግጭት የወጡ ወይም ከጨቋኝ አገዛዝ እየወጡ ላሉ ሀገራት የሽግግር ፍትህ ፍላጎታቸውን በተገቢው ጊዜ እንዲያገኙ ከማድረግ ጎን ለጎን አካባቢያዊ ተሳትፎን እና የማህበረሰብ አጋሮች አቅም ግንባታ እንዲበረታታ ልዩ እድል ይሰጣል።



# ማውጫ


**How and why was this self-assessment toolkit developed? ......3**
Methodology ......7

**How to use this self-assessment toolkit ......8**
How to conduct the self-assessment ...... 10
Engaging survivors in the self-assessment ...... 12
A note for donors and international organizations ...... 13

**Foreword ...... 14**

**1. Ethics and best practices for working with survivors ......16**
Assessment questions for organizations to pose ...... 18

**2. Holistic support services ......23**
Assessment questions for organizations to pose ...... 26

**3. Truth-telling and documentation ......31**
Who can undertake documentation and for what purpose? .. 33
Assessment questions for organizations to pose ...... 36

**4. Justice and accountability ......43**
Assessment questions for organizations to pose ...... 46

**5. Reparations ......50**
Assessment questions for organizations to pose ...... 53

**6. Reform and prevention ......56**
Assessment questions for organizations to pose ...... 58

**7. Memory and education ......62**
Assessment questions for organizations to pose ...... 64

**8. Community and solidarity ......68**
Assessment questions for organizations to pose ...... 70

**Further reading ...... 73**

# በዚህ የመሳርያ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ትርጎሜዎች ላይ ማስታወሻ

ይህ የመሳርያ ጥቅል "ተጎጂ" እና "ሰርቫይቨር" የሚለውን ቃል ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት የደረሰባቸው ግለሰቦችን ለማመላከት የሚጠቀም ሲሆን እነዚህ ቃላት ጥቅም ላይ የሚውሉበት ዐውድ ሊለያይ እንደሚችል እና አንድ ግለሰብ እንደ "ተጎጂ" ወይም "ሰርቫይቨር" በሚለው ቃል መለየታቸው የሚወሰነው በዋነኝነት በራሳቸው ምርጫ እና ራሳቸውን በሚገልፁበት መልክ መሆኑን እውቅና በመስጠት ነው። "ተጎጂ"" አብዛኛውን ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውለው የተጎጂነት ሁኔታን እና የህግ ዐወድ እንዲሁም ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት የደረሰባቸው ተጎጂዎች በሙሉ ከወንጀሉ የማይተርፉ መሆኑን አሳዛኝ እውነታ ለማመላከት ነው፡ ፡ "ሰርቫይቨር" ጾታዊ ጥቃት የደረሰባቸው ግለሰቦችን ጥንካሬ እና ማብቃት አፅኖት የሚሰጥ እና በስነልቦና እና የማህበረሰብ ድጋፍ ሴክተሮች ውስጥ የተለመደ በመሆኑ በእዚህ መሳርያ ውስጥ በተደጋጋሚ ጥቅም ላይ ውሏል፡ ፡

በጥቅም ላይ የዋሉ የቁልፍ ቃላት ትርጎሜዎች በሙሉ GIJTR ከዚህ ሰነድ ጋር በጋራ እንዲሄድ በተዘጋጀው ቅርፅ ማስያዣ ሰነድ ላይ ቀርበዋል።

# ይህ እራስን የመገምገሚያ የመሳርያ ጥቅል እንዴት እና ለምን ተዘጋጀ?

## ይህ እራስን የመገምገሚያ የመሳርያ ጥቅል ለምን ተዘጋጀ?

ባለፉት አስር አመታት ከግጭት እየወጡ ካሉ ማህበረሰቦች ጋር በጋራ በመስራት GIJTR የጦርነት እና የግፍ እና የጭካኔ ወንጀሎች ስርዓተ ጾታዊ ተፅእኖን ከሁሉም የስርዓተ ጾታ የመጡ ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት (CRSV) ከደረሰባቸው በሁዋላ በቤተሰብ እና በማህበረስብ መገለል የደረሰባቸው ግለሰቦች፣ የቤተሰብ አስተዳዳሪዎች ወንዶች እና ወንዶች ልጆች በጎጂ አባታዊ ልማዶች የስነልቦና ድጋፍ ከማግኘት ወደኋላ በማለታቸው ቤተሰባቸውን ለማገዝ ከትምህርት ቤት በቀሩ ወጣት




**ሴቶች ለመመልከት ችሏል። አብዛኛውን ጊዜ እነዚህን አይነት ጥሰቶች በየሽግግር ፍትህ ሂደቶች ውስጥ ችላ የተባሉ ሲሆን በማወቅም ሆነ ባለማወቅ በተዋጊዎች እና ስልጣን ባላቸው ላይ ትኩረት የሚያደርጉ ትርክቶችን በመምረጥ እነዚህን አይነት ጥሰቶች ወደኋላ ይገፋሉ፣ GIJTR ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት (CRSV) ጋር በተገናኘ በተለይም መንግስት በወንጀል ውስጥ ተሳትፎ የነበረው ወይም በተገቢው ሁኔታ ምላሽ መስጠት ባልቻለባቸው አውዶች ውስጥ አብዛኞቹ መልካም ለውጦች በተጎጂዎች/ሰርቫይቨሮች እና በዙሪያቸው ያሉ የድጋፍ ማህበረሰቦች ያላሰለሰ ጥረት የተመራ መሆኑን ተመልክቷል። አብዛኛውን ጊዜ ሰርቫይቨሮች የሚጋሩት የተሻለ ፍትሃዊ እና ሰላማዊ መጪ ዘመንን ለመፍጠር ካላቸው መሰጠት የመነጨ እውነትን፣ ፍትህን እና ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት መዳንን በማራመድ፤ ለተጎጂዎች ፍላጎት ትኩረት በመሳብ እና ሰርቫይቨሮችን ለመደገፍ እና እነዚህ ጥሰቶች በድጋሚ እንድይከሰቱ ፈጠራ የተሞላባቸው መፍትሄዎች በማቅረብ የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት (CSOs) ሚና ወሳኝ ነበረ። ሲቪል ማህበራት መር ስራዎች እንደ ሲቲ ኦፍ ጆይ፣ በዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኦፍ ኮንጎ ለሰርቫይቨሮች የሚሰጥ የአመራር ስልጠና መርሃ ግብር (በዶ/ር ዴኒስ ሙክዌጌ እና ፓንዚ ፋውንዴሽን የተቋቋመ) እና የሴቶች የእውነት እና ማስታሻ ኮሚሽን (በሩታ ፓሲፊክ ዲ ላስ ሙጄርስ በ2010 በ ኮሎምቢያ የተጀመረ) ሰርቫይቨሮች የራሳቸውን የማገገሚያ እና እውነትን ይፋ የማድረግ ሂደት እንዲነድፉ ቀዳሚ ስፍራ በመስጠት እና የረዥም ጊዜ አጠቃላይ ድጋፍ በመስጠት አስተዋፅኦ አድርገዋል።**

ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት በመቀረፍ GIJTR ያየውን የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት ከፍተኛ ሚና የተባበሩት መንግስታት የፀጥታው ምክር ቤት ሬዞልዩሽን 2467 (UNSCR 2467) በ2019 አፅኖት ይሰጠዋል። የተባበሩት መንግስታት የፀጥታው ምክር ቤት ሬዞልዩሽን 2467 (UNSCR 2467) በ 2019 ባፀደቀው ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ችግሮችን ለመፍታት "ሰርቫይቨሮችን ማእከል ያደረገ መንገድ" መከተልን ይወተውታል እንዲሁም በሁሉም በመከላከል እና ምላሽ ጥረቶችን ላይ የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት በተለይም በሴቶች፣ ሰርቫይቨሮች እና ሀይማኖታዊ እና የማህበረሰብ መሪዎች የሚመሩ የሲቪል ማህበራትን የማስተዋወቅ እና የመደገፍ አስፈላጊነትን እውቅና ይሰጣል።

2000ዓ.ም መሰረት የጣለ ወሳኔ አሁን የሴቶች፣ የሰላም እና ፀጥታ (WPS) አጀንዳ፦ UNSCR 1325 በመባል የሚታወቀውን አጀንዳ ካስጀመረ ጀምሮ በፀጥታው ምክር ቤት ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ጥበቃ፣ መከላከል እና ክስን የሚመለከቱ አሁን ካሉት ከስድስት ውሳኔዎች ውስጥ UNSCR 2467 የመጨረሻው ነው። ይህ ውሳኔ ከሴቶች መብት ድርጀቶች እና የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት በ 1990ዎቹ ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት እንዲቆም እና በሰላም እና ፀጥታ ድርድሮች ላይ ትርጉም ያለው ተሳትፎ እንዲኖር ላደረጉት ጠንካራ ተደጋጋሚ ውትወታ ምላሽ ነው።

በተመሳሳይ ግዜ፣ ከሚጫወቱት ወሳኝ ሚና የተነሳ ለሚያቀርቧቸው አገልግሎት ያለው ፍላጎት ካላቸው ሀብት እና አቅም እጅግ በልጦ በመገኘቱ የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት አብዛኛውን ጊዜ በከፍተኛ ጫና ውስጥ ናቸው፡ ፡ ስራቸውን በሚተገብሩበት ወቅት አብዛኛውን ጊዜ ሰርቫይቨሮችን ማእከል ያደረገ ድጋፍ የማቅረብ አቅማቸውን የሚገድቡ ጎጂ ባህላዊ ልማዶችን እና የስርዓተ ፆታ ደንቦችን፣ በደህንነት ስራቸውን የመስራት ስጋትን፣ እና በደካማ መልኩ የተቀረፁ የገንዘብ አሰራሮችን በጥንቃቄ እንዲያልፉ ጭምር ይገደዳሉ። ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ተፈጥሮ እና ከረጅም ጊዜ ተጽኖዎች አንጻር፣ የግለሰብ ድርጅቶች ሁሉንም የሰርቫይቨር ፍላጎቶች እንደ እነሱ አውድ ማሟላት ሊታግታቸው ይችላሉ። አንድ ሰርቫይቨር የወንጀል ተጠያቂነትን ሲፈልግ/



ስትፈልግ ሌላ ሰርቫይቨር የአእምሮ ጤና እና የስነልቦና ድጋፍ፣ የትምህርት እና የስራ እድሎችን ወይም ዳግም አለመፈፀም ላይ የሚያተኩሩ ጥረቶችን ሊያስቀድም/ልታስቀድም ይችላል/ትችላለች። ይልቅኑስ መተባበር ወይም የሪፈራል መረብ መዘርጋት እውነተኛ የተሟላ አካሄድ ለማሳካት አስፈላጊ ነው።

ለሰርቫይቨሮች ቀድሞ ደራሽ እና ጠበቃዎች በመሆናቸው እነዚህ የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት ከሚሰሩት እጅግ አስፈላጊ ስራ ጎን ለጎን ያሉ ጫናዎችን እውቅና በመስጠት GIJTR ይህንን መሳርያ ያዘጋጀው ለሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት ከእለት ተእለት ስራቸው አንድ እርምጃ ወደ ኋላ በመውሰድ የሰርቫይቭሮች አጠቃላይ ፍላጎት በአውዳቸው ውስጥ ምን ያህል በተጠቃለለ መልኩ እየተሟላ ስለመሆኑ መርሃግብሮቻቸውን ማስፋት ውይም ማስተካከል ይቻል እንደሆን ለማሰብ በአለመ መልኩ እንዲገመግሙ ተግባራዊ ሊደረጉ የሚችሉ መሳርያዎችን ለማቅረብ ነው። አስር ዓመታት በግጭት የተጎዱ ማህበረሰቦች ጋር አብሮ በመስራት በተገኘ እውቀት እና በ UNSCR 2467 እንደተንፀባረቀው የዚህ መርሃ ግብር ማእከል የሆነው የ GIJTR እምነት ነው፤ እሱም የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት በተለየ መልኩ እውነትን የማፈላለግ፣ የፍትህ እና የመፈወስ/የማዳን ጥረቶችን እና የሰርቫይቨሮችን አጠቃላይ ፍላጎት ለማሟላት በፍላጎቶቻቸው ልክ የተዘጋጁ አቀራረቦችን ስለሚደግፏቸው ማህበረሰቦች ላይ ባላቸው ጥልቅ መረዳት ላይ በመመስረት እንዲያዘጋጁ ስርቫይቨሮችን ማእከል ያደረጉ አሰራሮችን ለማስተዋወቅ ጥሩ ቦታ ላይ ናቸው።



## ስነ-ዘዴ


ይህ ሰነድ ከማህበረሰቡ ጋር በቅርበት የሚሰሩ ድርጅቶች ጋር በቅርበት እንደሚሰራ ዓለም አቀፍ ጥምረት መልካም ተሞክሮዎች እና ግብዓቶችን ለማሰባሰብ ከተለያዩ ሰፊ በሆኑ የተለያዩ ዐውዶች ወስጥ ሰርቫይቭሮችን ለመደገፍ በቀጥታ ከሚሰሩ ድርጅቶች እና ባለሙያዎች እንዲሁም ከ20 በላይ ጥልቅ የሆኑ ቃለ መጠይቆች እና ሰባት ጥናቶች የተሰበሰቡ ምልከታዎችን በማጥራት የGIJTRን ሰፊ የሆነ ግንኙነቶች እና እውቀት ይጠቀማል።

ይህ እራስን የመገምገሚያ የመሳርያ ጥቅል ከቤተሰቦች፣ማህበረሰቦች፣ቡድኖች እና ሀገራት በላይ የግለሰብ ሰርቫይቭሮችን መብቶች እና ደህንነትን ያስቀድማል እንዲሁም አጉልቶ ያሳያል። ይህ አዘጋጆቹ በፍላጎት ያደረጉት ውሳኔ ሲሆን መነሻውም በመረሃ ግብሩ የምርምር ደረጃ ወቅት በታዩ ሰርቫይቨሮች አንዳንድ ጊዜ ታሪካቸውን እንዲያጋሩ ወይም መርሃ ግብሮች ውስጥ በመሳተፍ ቤተሰብ፣ ማህበረሰብ፣ አገልግሎት ሰጪዎች ወይም እውነትን ይፋ ማድረግ፣ ፍትህን የመፈለግ ወይም በግጭት ወቅት የተፈፀሙ በደሎችን ከማሳየት ጋር የተያያዙ ሀገራዊ ግቦችን እንዲያገለሉ ይገደዳሉ ውይም ጫና ይደረግባቸዋል የሚሉ ስጋቶች ላይ በመመስረት ነው። ይህ ጫና ሰርቫይቭሮችን ማእከል ያደረገ አሰራር ቁልፍ አካል የሆኑትን ሰርቫይቨሮችን ማብቃት እና ውክልናን የሚያሳንስ ነው።

የመሳርያው አላማ የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት መርሃግብሮቻቸው እና ተግባራቶቻቸው የድርጅቶቹን ሀብት፣አቅም እና በአውዳቸው ውስጥ ያሉ ልዩ ተግዳሮቶችን እና መልካም እድሎችን ከግምት በማስገባት የሰርቫይቨሮችን ፍላጎት እና ቅድሚያ የሚሰጧቸውን ጉዳዮች ምላሽ ለመስጠት የተቀረፀ መሆኑን እንዲገመግሙ አጠቃላይ ማዕቀፍ እንዲኖራቸው ለማስቻል ነው።

ምንም እንኳ ሁሉም ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ሰርቫይቨሮችን የሚደግፉ መርሃግብሮች የሽግግር ፍትህ ሰፊ ሂደት አካል ሆነው የተቀረፁ ባይሆኑም ያለፉ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን ለመቁጠ፣ ያለፉ ጉዳቶችን እውቅና በሰጠ መልኩ እና ተመሳሳይ ጥሰቶች ዳግመኛ እንዳይከሰቱ ለማድረግ እንዲሁም ይበልጥ ፍትሃዊ መጪ ዘመንን ለመገንባት ምን እንደሚያስፈልግ በአገናዘበ መልኩ የተለያዩ የመፍትሄዎችን ለተጎጂዎች እና ሰርቫይቨሮች መደበኛም ሆነ ኢ መደበኛ የሽግግር ፍትህ ስልቶች ለማቅረብ ጠቃሚ የሆኑ መሳርያውችን እንደሚያያቀርብ የGIJTR ስራ አሳይቷል።

በዚህ እይታ ላይ በመጨመር የግምገማ መሳርያው እውነትን፣ፍትህን እና ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት መፈውስን በሽግግር ፍትህ መነፅር ይመለከታል፣ እውነትን ይፋ ማውጣት፣ ፍትህን፣ ዳግመኛ አለመከሰትን፣ ማካካሻ እና ማስታወሻን በሚመለከት የሰርቫይቨሮችን ፍላጎት ከግምት ለማስገባት የሚያስችል ማዕቀፍም ለሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት ያቀርባል።



# ይህን እራስን የመገምገሚያ መሳርያ እንዴት መጠቀም እንደሚገባ

## እራስን የመገምገሚያ የመሳርያ ጥቅሉ አጠቃላይ እይታ

**መሳርያው ለሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት በቀጣይ የተዘረዘሩትን ነጥቦች በጥያቄዎች፣ ሃሣብ የማሰባሰብ/የማፍለቅ መሳርያዎች እና ሰነዶች በመጠቀም እራስን የማየት ለተዋቀረ ሂደት እንዳያካሂዱ መሳርያዎችን ያቀርባል፡-**

- የሰርቫይቨሮች ፍላጎት በዐውዳቸው ውስጥ በምን ያህል መጠን እየተሟላ እንደሆነ እና እነዚህን ፍላጎቶች በተጠቃለለ መልኩ ለሟሟላት ያሉ ፈተናዎች እና መልካም እድሎች
- ለሰርቫይቨሮች ፍላጎት በምን ያህል መጠን ምላሽ እየሰጡ እንደሆነ እና በመረሃ ግብሮቻቸው እና ስትራቴጂዎቻቸው ምን ያህል ሰርቫይቨሮችን ማእከል ያደረገ አሰራር እየተገበሩ እንደሆነ
- ሰርቫይቨሮችን ማእከል ያደረገ አሰራር ለመተግበር እና የሰርቫይቨሮችን ፍላጎት በይበልጥ በአጠቃላይ መልኩ ለማሟላት ስለክፍተቶች፣ ፈተናዎች እና መልካም እድሎች ያደረጉት ግምገማ በምን ያህል የሰርቫይቨሮችን የራሳቸውን ግምገማ እንደሚያንፀባርቅ
- ሰርቫይቨሮችን ማእከል ያደረገ አሰራር ለመተግበር እና የሰርቫይቨሮችን ፍላጎት በይበልጥ በአጠቃላይ መልኩ ለማሟላት ለሚለዮዋቸው ክፍተቶች፣ፈተናዎች እና መልካም እድሎች ምላሽ አሁን ያሉዋቸውን መርሃ ግብሮችን ማስፋት ይችሉ እንደሆነ ወይስ አዳዲስ መርሃ ግብሮችን ያስጀምሩ እንደሆነ

ይህ መሳርያ የራስ ግምገማውን ለማዋቀር የሽግግር ፍትህ ማእቀፍን ይጠቀማል፤ በቀጣይ በሚከተሉት እርሶች ዙርያ የተዘጋጁ ጥያቄዎች፣ ሃሣብ የማሰባሰብያ/የማፍለቅያ መሳርያዎች እና ሰነዶችን ያካትታል፡-

- ከሰርቫይቨሮች ጋር ለመስራት ስነምግባር እና መልካም ተሞክሮ
- ሁሉን አቀፍ የድጋፍ አገልግሎት
- እውነትን ይፋ ማውጣት እና ስነዳ
- ፍትህ እና ተጠያቂነት
- ካሳ
- ለውጥ እና መከላከል
- ማስታወስ እና ትምህርት
- ማህበረሰብ እና አብሮ መቆም

መሳርያው የሚከተሉትን ያካትታል

- በእርሱ ላይ አጭር መግቢያ
- ስለዐውዳቸው እንዲጠይቁ ለድርጅቶች የተዘጋጀ ከእያንዳንዱ እርእስ ጋር የተገናኙ የግምገማ ጥያቄዎች — ለድርጅቶች እና ለሰርቫይቨሮች
- የሚመከሩ ሃሣብ የማሰባሰብያ/የማፍለቅያ፣ አስፈላጊ ሰነዶች እና ተጨማሪ የሚነበቡ ሰነዶች

የመሳርያው ተጠቃሚዊች ስለሽግግር ፍትህ በተለያየ የእውቀት ደረጃ እንደሚኖራችው እውቅና በመስጠት GIJTR በቁልፍ ቃላት እና በተለያዩ አውድ ውስጥ ያሉ መደበኛ እና ኢመደበኛ የሽግግር ፍትህ ሂደቶች ምሳሌዎች ላይ ተጨማሪ መረጃ የሚሰጥ እና ቅርፅ የሚሰጥ (ፍሬሚንግ ሰነድ) አዘጋጅቷል።

ጥናቶች እና በዚህ መሳርያ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ቁልፍ ቃላትን ትርጉም የሚያስቀምጠው ፍሬሚንግ ሰነድ እዚህ ማግኘት ይቻላል።

## የእራስ ግምገማን እንዴት መተግበር እንደሚገባ

ይህ የራስ መገምገሚያ መሳርያ አዳዲስ መርሃ ግብሮችን በፈፅመ ጊዜ ገና ከጅምሩ፣ መርሃግብሩ ከጀመረ በኋላ በየተወሰነ ጊዜ ወይም ከሌላ ድርጅት ወይም ድርጅቶች ጋር አዲስ የአጋርነት ግንኙነት በሚጀመርበት ወቅት ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል። ይህ መሳርያ ትእዛዝ የሚሰጥ መሳርያ እንዲሆን የታሰበ መሳርያ አይደለም፤ ስለሆነም በድርጅቶች የሚወሰኑ የራስ ግምገማ ማድረግ የሚያስፈልግባቸው ሌሎች ሁኔታዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ GIJTR የጠብቃል።

በጋራ ሲወሰዱ በዚህ የራስ መገምገሚያ መሳርያ ውስጥ ያሉት ርእሶች ለእውነት፣ ፍትህ፣ እና ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት መፈወስ ሁሉን ዓቀፍ አቀራረብ ይወክላሉ። ሆኖም ግን የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት በራሳቸው መርሃ ግብር ለእነዚህ ሁሉ ፍላጎቶች ምላሽ መስጠት ይችላሉ ወይም ይገባቸዋል ተብሎ አይጠበቅም።

ይልቁኑም የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት መሳርያውን ከሚከተሉት ከሦስቱ በአንዱ መንገድ ሊጠቀሙት ይችላሉ፤

1. ለራሳቸው መርሃ ግብር እና አውድ በጣም አስፈላጊ የሆኑ ጭብጦች ላይ በማተኮር ውስጣዊ ዩራስ ግምገማ ለማካሄድ

2. እውነት፣ ፍትህ፣ እና ከጥቃት መፈወስን በሌሎች የድጋፍ መንገዶች ወደፊት ለማራመድ ከሚሰሩ ሌሎች ድርጅቶች ጋር የሰርቫይቨሮች ፍላጎት በቡድኑ የተሰባሰበ ጥረት ምን ያህል ሁሉን አቀፍ በሆነ መልኩ እየተሟላ እንደሆነ የቡድን ግምገማ ለማድረግ በጋራ ለመስራት

3. ዩራስ ግምገማውን በሁለት ዙሮች ለማካሄድ፤ በመጀመርያ በራሳቸው መርሃግብሮች ላይ በማተኮር በመቀጠል እንደ ሁለተኛው ዙር አካል ከሌሎች ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት የደረሰባቸው ሰርቫይቨሮችን ከሚደግፉ ድርጅቶች ጋር የጋራ ግምገማ ለማካሄድ

በአንድ ድርጅት ውስጥ በመጀመርያ ሲካሄዱ የራስ ግምገማው ቁልፍ አላማዎች ከሰርቫይቨሮች ጋር በሚሰራው ስራ የድርጅቱን ክፍተቶች፣ ፈተናዎች እና መልካም እድሎች ላይ እይታን ለመፍጠር እና እነዚህን እይታዎች የወደፊት መርሃግብሮችን፣ ስትራቴጂዎችን እና የሪፈራል አጋርነቶችን በመረጃ እንዲደግፉ መጠቀም ናቸው፡ ፡ GIJTR በድርጅቱ ውስጥ ካሉ ቡድኖች የተወጣጡ ሰራተኞችን በማሰባሰብ ግምገማውን እንዲካሄድ ምክረ ሃሳብ ያቀርባል። ግምገማውን ለማካሄድ የሚያስፈልገው ጊዜ ምን ያህሉ የመሳርያ ጥቅሉ ክፍሎች ለድርጅቱ አስፈላጊ ናቸው በሚለው ላይ የሚወሰን ይሆናል፤ ሆኖም ግን GIJTR በእያንዳንዱ ክፍል ላይ ከ ሁለት እስከ አራት ሰዓታት ማሳለፍን ይመክራል።

በተመሳሳይ ዐውድ ውስጥ የሚሰሩ ድርጅቶች ስብስብ ውስጥ የራስ ግምገማውን ለማካሄድ በጥቅም ላይ በሚውልበት ወቅት የራስ ግምገማው ቁልፍ አላማ ድርጅቶች ምን ያህል አንዱ የሌላውን ስራ እንደሚያወቅ፣ ይህንንም እውቀት አገልግሎታቸውን ለሚጠቀሙ ሰርቫይቭሮች እንዴት እያስተዋወቁ እንደሚገኙ እና የሰርቫይቨሮችን ፍላጎት በተሻለ ለሟሟላት በጋራ ለመስራት እድሎች ስለመኖራቸው ድርጅቶች በጋራ እንዲያንፀባርቁ ነው።

ሁሉን አቀፍ የቡድን ግምገማን ለማረጋገጥ GIJTR በተቻለ መጠን መሳርያው በሚሸፍናቸው ጉዳዮች ላይ የሚሰሩ ድርጅቶችን ማሰባሰብን ይመክራል። በተወሰኑት ጉዳዮች ላይ የሚሰሩ ድርጅቶች ከሌሉ (ለምሳሌ







የማስታስ ውይም የማስተማር ስራዎች) የቡድን ግምገማው ላይ እንደ ክፍተት ሊያዝ ይችላል። GIJTR የቡድን ግምገማ ለማካሄድ የ አራት ቀናት ወርክሾፕ ይመክራል። ለወርክሾፕ የሚመከረው መንገድ የመሳርያው የሰነዶች ክፍል ይገኛል እንዲሁም ድርጅቶች ከራስ ግምገማ በፊት እና በሁዋላ የራስ ግምገማው በእነሱ አውድ ስለሰርቫይቨሮች ፍላጎት ያላቸውን መረዳት እንዴት እንደተቀየረ እንዲያንፀባርቁ እና ወደፊት የሚደረጉ መረሃግብሮችን እና ስራዎችን እንዲቀርፅ የሚሰሩት የ”ቴርሞ ሜትር ተግባ” በሰነዶች ክፍል ይገኛል። የመረጃ ሰነድ ክፍሉ የተሳታፊዎችን ደህንነትን ለመደገፍ የራስ ግምገማውን በሚያካህዱበት ጊዜ ለድርጅቶች የተጠቆሙ አእምሮን/ሃሳብ መሰብሰብ ተግባሮችን ይዟል::

## የእራስ ግምገማ ሂደት ወስጥ ስርቫይቨሮችን ማሳተፍ

እያንዳንዱ የመሳሪያ ጥቅሉ ክፍል የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት ስለ ዐውዳቸው እራሳቸውን (ስለራሳቸው መረሃግብሮች) እና ሰርቫይቨሮችን የሚጠይቁትን ጥያቄዎች ያካትታል። ለሰርቫይቨሮች የተዘጋጁ ጥያቄዎች የተካተቱት እውነትን፣ ፍትህን እና ፈውስን ለመፈለግ በሚደረጉ ማነኛውም ጥረቶች ከሰርቫይቨሮች ጋር መመካከር እና በጋራ መንደፍ አስፈላጊ መሆኑን ለማጉላት ሲሆን ይህም መርሃግብሮች እና ተግባራት ራሳቸው ሰርቫይቨሮች የገለፅዋቸው ፍላጎቶች እና ቅድሚያ የሚሰጧቸው ጉዳዮች ምላሽ መስጠታቸውን ለማረጋገጥ ነው። ከሰርቫይቨሮች ጋር ለማማከር እና አብሮ ለመንደፍ የበለጠ የዳበሩ መዋቅሮች ላሏቸው ድርጅቶች (ለምሳሌ በሰርቫይቨሮች ሪፈራል ቡድን በኩል) ጥያቄዎቹን እንደ እራስ ግምገማው አካል ማቅረብ ተገቢ ሊሆን ይችላል። ሆኖም ግን የዳበረ መዋቅር ለሌላቸው ድርጅቶች ሰርቫይቨሮች በመሳሪያ ጥቅል ውስጥ የሚገኙ ጥያቄዎችን መጠየቅ ተገቢ ላይሆን ይችላል በተለይም ይህን ማድረግ ሰርቫይቨሮች በግምገማው ውስጥ እንዲሳተፉ ማድረግን የሚያካትት ከሆነ ይህ በእነሱ ላይ ተጨማሪ ሸክም ሊፈጥር ስለሚችል ነው ። በመጨረሻም ድርጅቶች የእራስ ግምገማ በሚካሄድበት ወቅት ሰርቫይቨሮችን ማሳተፍ ተገቢ ስለመሆኑ ለመወሰን ድርጅቶች የራሳቸውን ፈቃድ መጠቀም ይኖርባቸዋል:: ተገቢ እንዳልሆነ ከወሰኑ GIJTR ሰርቫይቨሮችን በመርሃግብሮቻቸው ውስጥ ሌሎች ቦታዎች በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ግብረ መልስ ለመስጠት እድሉን የሚሰጡ እንደሆነ ለማገናዘብ ለሰርቫይቨሮች የሚቀርቡ ጥያቄዎችን እንዲገመግሙ ይመክራል።





## ለለጋሾች እና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ማስታወሻ

የዚህ እራስን መገምገሚያ መሣሪያ ጥቅል ዋና ተጠቃሚዎች የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት እንዲሆኑ የታቀደ ሲሆን GIJTR ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ከሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት ጋር በመተባበር ወይም መርሃግብሮችን ተግባራዊ ለማድረግ የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ ምላሽ በመሰጠት ላይ የሚሰሩ ለጋሾች እና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ተፈጻሚነት ሊኖረው እንደሚችል ይገነዘባል። ለጋሾች እና ዓለምአቀፍ ድርጅቶች ለገንዘብ ድጋፍ ወይም ለአጋርነት ማመልከቻ ሲያስገቡ ወይም ለድርጅቶች የገንዘብ ድጋፍ ወደሚያደርጉበት አዳዲስ መርሃ ግብሮች ጅምር ላይ የራስ ግምገማ ምዕራፍ አንዲያካትቱ ሲጠይቁ የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት ወደዚህ የመሳሪያ ጥቅል ለመምራት ሊያስቡ ይችላሉ።

# መቅድም

## በኅዳር 2023 በኮሎምቢያ የተሟጋቾች ኔትዎርክ አባል በሆኑ የተሞከሩ መሳሪያዎች።

ኮሎምቢያ ከ70 ዓመታት በላይ የተለያዩ ገጽታ ያላቸው የውስጥ ግጭቶችን ተቋቁማለች፤ ከ450,000 በላይ ኮሎምቢያውያን ሞተዋል፣ ከ50,000 በላይ ታፍነው ተወስደዋል፣ ከ7 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ደግሞ ተፈናቅለዋል። ባሁኑ ሰዓት በጣም ርቀው በሚገኙ የሀገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ ማኅበረሰቦች የታጠቁ ቡድኖች ከባድ ጥቃት እየፈጸሙባቸው ሲሆን የሰብዓዊ መብቶች የተሟጋቾች የግድያ ዒላማ ሆነው ቀጥለዋል። የሽግግር ፍትህ ሂደቶች ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃትን በማስወገድ ረገድ መጠነኛ እርምጃ ያደረጉ ቢሆንም ከ15 ዓመታት በላይ ሲከናወኑ ቆይተዋል። እ.ኤ.አ በ2022 የእውነት ኮሚሽን ባወጣው የመጨረሻ ሪፖርት መሰረት የትጥቅ ትግሉ በሴቶችና በልጃገረዶች ላይ ወሲባዊና የስነተዋልዶ ጥቃት አምጥቷል የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል። ይህም የስነተዋልዶ ነፃነታቸውንና ሰብዓዊ መብታቸውን የሚጥስ ነው። በ2023 ዓ.ም. የሰላም ልዩ ስልጣን (Special Jurisdiction for Peace) ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት፣ የወሲብና የስነተዋልዶ ጥቃትን እንዲሁም የታጠቁ ቡድኖች በሚፈፅሙት ጭፍን ጥላቻ ላይ የተመሰረቱ ሌሎች ወንጀሎችን የሚመረምር በሃገር አቀፍ ደረጃ “የትላልቅ ጉዳዮች”(“macro-case”) ምርምሯ አስጀመረ። ያም ሆኖ ከግጭት ጋር በተያያዘ ከሚፈጸም የጾታ ጥቃት ሰርቫይቨሮች የሚጠብቁት ነገር እንዲሟላላቸው የበለጠ ቁርጠኝነትና ፖለቲካዊ ፈቃድ ያስፈልጋል።



Organizations belonging to the Ruta Pacífica de las Mujeres network piloting the toolkit in Medellín in November 2023.



ለ27 ዓመታት ያህል፣ ሩታ ፓሲፊካ ደ ላስ ሙጀሬስ (የሴቶች ፓሲፊስት መንገድ) (the Pacifist Route of Women) - በኮሎምቢያ ያለውን የትጥቅ ግጭት በድርድር ለመፍታት የሚሰሩ የፌሚኒስት ድርጅቶች መረብ ሲሆን ከጾታ ጥቃት ሰርቫይቨሮች ፍላጎትና መብቶች ተሟግቷል። ሥራችን ለሴቶችና ማህበረሰቦቻቸው የስልጠናና የመረጃ መርሃግብሮችን ማዘጋጀት ላይ ያተኮረ ሆኖ በዚህም ሴቶች በእውነትን ይፋ ማድረግ፣ ፍትህ እና የመፈወስ ሂደት ውስጥ በፈለጉበት ወቅት ዝግጁ ሲሆኑ መሳተፍ እንዲችሉ ማስቻል ነው። በተጨማሪም ተቋማት ጋር ጉዳያቸውን እየወሰዱ ያሉ ሴቶችን ለማጀብ፣ ለማጠንከር እና ለመጠበቅ ስልቶችን በማዘጋጀት የሥነ ልቦና ድጋፍ እናደርጋለን። በ2013 ሩታ የኮሎምቢያ የሴቶች



Organizations working with survivors in the Central African Republic piloting the toolkit in Bangui in January 2024.

እውነት እና ትውስታ ኮሚሽንን (Colombian Women’s Truth and Memory Commission) የደመደመ ሲሆን ኮሚሽኑ የትጥቅ ግጭቱ በሴቶችና ልጃገረዶች ላይ የሚያደርሰውን ተፅዕኖ በግልጽ እንዲታይ ለማድረግ ያለመ፣ 150 የወሲብ ጥቃት ምስክሮችን ጨምሮ 1,000 የሴቶችን ምስክርነት መዝግቧል። በቀጣይነት እየተፈፀሙ ባሉ ጥሰት ምክንያት ስነዳ ቀጣይነት ያለው ስልት ሆኖ የሚቀጥል በመሆኑ እኛም ህጋዊ ድጋፍ የመስጠት ስትራቴጂ ያለን ሲሆን ይህም ለሴቶች የተለያዩ የሲቪል፣ የወንጀል፣ የህገ-መንግስታዊ እና ሌሎች መውሰድ በሚፈልጉት እርምጃዎች ላይ ህጋዊ ምክር መሰጠት ላይ ያተኮረ ነው።

ከግጭት ጋር በተያያዘ ከሚፈጸም ወሲባዊ ጥቃት ለሰርቫይቨሮች ሁለንተናዊ ድጋፍ ለመስጠት ያሉ ፈተናዎች እና እድሎችን በሚመለከት እራስን የመገምገም መሣሪያን በመጠቀም ለመገማገም በህዳር 2023 የሩታ ፓሲፊካ መረብ አባል የሆኑ ስምንት ድርጅቶች ቡድን በሜዴልሊን አንድ ላይ ተሰባስበዋል። መሳሪያውን የመጠቀም ልምድ እና በግምገማ ጥያቄዎቹ ላይ በቡድን ሆነው በጋራ መስራት የሚያስገኘው ጥቅም፣ በሌሎች ሃገሮች የሚገኙ ድርጅቶች ይህን ዘዴ ሰርቫይቨሮች ጋር የሚያከናውኑትን ሥራ ለማጠናከር እንዴት ሊጠቀሙበት እንደሚችሉ ለማስተዋል አግዟል።

ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃትን ለማስወገድ የሚደረግ ሁለንተናዊ አቀራረብ ሥነ ልቦናዊ ድጋፍ፣ ፍትሕ፣ እውነት መናገር፣ ካሳ፣ ትውስታን እና ትምህርትን ሊያካትት ይገባል። ሁልጊዜም ሰርቫይቨሮች መብት ላይ ያተኮረ፣ የራሳቸውን ጉዳይ በራሳቸው እንዲወስኑ የራሳቸውን ነፃነት እና ብቃት ያከበረ መሆን አለበት። በእነዚህ ምሶሶዎች ዙሪያ የታቀፈው ይህ መሣሪያ፣ እንደ ኔትወርክ የምናደርገውን የጋራ ጥረቶችቻንን ያንጸባርቃል። አዳዲስ ጥያቄዎችን ይሰጠናል፣ እንዲሁም በተደራጀ ራስን በማሰላሰል እና በመገምገም ሂደቶች ውስጥ መልሶችን የመፈለግ አጋጣሚ ይሰጠናል። በጋራ በምናከናውነው ሥራ አማካኝነት እየተለዋወጠ ለሚሄድ የጥቃት ሰለባዎች ፍላጎት ምን ምላሽ እየሰጠን እንደሆነ ለመገምገም ያስችለናል። ሰርቫይቨሮች የሚያስፈልጓቸው ነገሮች የተለያዩ በመሆናቸው እና ፍትሕን ለመፈለግ የሚደረገው ጥረት አንዳንድ ጊዜ አመቺ እና አንዳንድ ጊዜ ደግሞ መጥፎ ከሆኑት ሁኔታዎች ጋር መላመድ ስለሚኖርበት፣ ይህ ሥራ ለሰርቫይቨሮች ጥብቅ ወይም አስገዳጅ ዘዴዎችን ከመጠቀም በተቃራኒው የሚያስፈልጓቸውን ነገሮች አንድ ላይ የሚያቀናጅና የሚያሟላ ሁለንተናዊ አቀራረብ ይጠይቃል። ሙሉ በሙሉ ሲታይ፣ እራስን የመገምገም መሣሪያው ከግጭት ጋር በተያያዘ ከሚፈጸም ወሲባዊ ጥቃት ሰርቫይቨሮችን ለመርዳት እና ለሚሟገቱ ድርጅቶች ውጤታማ መሳሪያ ይሆናል።

ኤስተር ማሪና ጋሌኖ ዛፓታ

ብሔራዊ አስተባባሪ

ሩታ ፓሲፊክ ዲ ላስ ሙጄርስ ኮሎምቢአና

# 1. ከሰርቫይቨሮች ጋር አብሮ ለመስራት የሚያስፈልጉ ስነ-ምግባር እና መልካም ተሞክሮዎች

## መግቢያ

**እ.ኤ.አ. በ 2019 UNSC ለመጀመሪያ ጊዜ ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ላይ ሰርቫይቨሮችን ያማከለ አካሄድ የተጎዱት ሀገራት እና የዓለም አቀፉን ማህበረሰብ ምላሽ እያንዳንዱን አቅጣጫ መምራት እንዳለበት የሚያረጋግጥ አስደናቂ ውሳኔ አጽድቋል፦ UNSCR 2467:: ይህ የውሳኔ ሰርቫይቨሮች ለእነሱ የሚተገበሩ ስራዎችን ፅንሰ-ሀሳብ መቅረፅ ፣ ማዘጋጀት ፣ መቅረፅ እና አፈፃፀም ላይ ትርጉም ባለው መልኩ እንዲሳተፉ “ምንም ነገር ስለእኛ ያለኛ” በሚል መርህ ለብዙ ዓመታት ሲያቀርቡ ለነበረው ጥያቄ ምላሽ ሰጥቷል።**

በተግባር ከሰርቫይቨሮች ጋር የሚሰሩ ድርጅቶች ፈውሳቸውን የሚደግፍ አካባቢ በመፍጠር ሰርቫይቨሮችን በማበረታታት ላይ በማተኮር ሰርቫይቨሮችን ያአማከለ አካሄድ መተግበር ይችላሉ:: ለዚህ ዋናው ነገር ወደ እውነት፣ ፍትህ፣ ካሳ፣አና ፈውስ ረጅም ቢሆንም እንዲሁም ሰርቫይቨሮችን የሚደግፉ ድርጅቶች ሰርቫይቨሮች ግባቸውን ሙሉ በሙሉ አንዲያሳኩ መርዳታቸወን ማረጋግጥ ባይቻልም የሰርቫይቨሮችን ውክልና የሚመልስ፣ ፅናታቸውን የሚገነባ እና ልምዳቸውን በታሪክ ማህደር በሚያሰቀመጥ መልኩ ከሰርቫይቨሮች ጋር የሚሰራ ስራን መስራት ለወጥ የማምጣት ውጤት ይኖረዋል የሚለው መረዳት ነው::



ሰርቫይቨሮችን ያማከለ አካሄድ መተግበር የሚከተሉትን ይጠይቃል፦

1. **ሰርቫይቨሮች አንድ ወጥ የሆነ ቡድን ወይም የሰዎች ምድብ አለመሆናቸውን በመገንዘብ**
2. **የግል ፍላጎቶቻቸውን ለመገምገም እና መብቶቻቸውን እና ጥቅሞቻቸውን ለማስተዋወቅ ሰርቫይቨሮችን ማዳመጥ**
3. **ሥርዓተ-ጾታን ያገናዘበ አቀራረብን መውሰድ**
4. **የሰርቫይቨሮች በመረጃ የተደገፈ የግለሰብ ምርጫ የእውነት፣ የፍትህ፣ የካሳ እና የፈውስ ስራዎች ቁልፍ ገፊ ሃይሎች መሆን እንዳለባቸው መገንዘብ**
5. **መረጃ እና የጥበቃ እርምጃዎችን ለሰርቫይቨሮች በቀላሉ ተደራሽ እና ለመረዳት ቀላል መሆናቸውን ማረጋገጥ**
6. **ሊሳኩ የማይችሉ ተስፋዎችን ከመሰጠት መቆጠብ**

ሰርቫይቭሮችን ያማከለ አካሄድ “በ”ምንም ጉዳት አለማድረስ” በሚለው ደህንነት፣ ሚስጥራዊነት፣ ክብር እና አለማዳላትን ባካተተው መርህ የተመሰረተ ነው:: ከሰርቫይቭሮች ጋር የሚሠራ ማንኛውም ድርጅት እነዚህን መርሆዎች የማክበር ኃላፊነት አለበት-ይህ ኃላፊነት “የመጨረሻው ውጤት መንገዱን ያጸድቃል” በሚለው ክርክር ሊሻር የማይችል ነው። በተግባር ላይ ሲውል ይህ ማለት ከሰርቫይቭሮች ጋር የሚሰሩ ድርጅቶች ለድርጀቱ የበለጠ ጥቅም እንዳለው ወይም ለቤተሰባቸው፣ ለማህበረሰቡ ወይም ለሀገራቸው የላቀ ግብ ያገለግላል ብሎ

## ምንም ጉዳት አለማድረስ መርሆች

**ደህንነት**
የሰርቭይቨሮችን እንዲሁም የቤተሰባቸውን፣ ልጆቻቸውን እና የረዷቸውን ሰዎች ጨምሮ ደህንነት በማንኛውም ጊዜ ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው።

**ሚስጥራዊነት**
የሰርቭይቨሮችን (እና ቤተሰቦቻቸውን) ምስጢራዊነት ምንም አይነት መረጃ በማንኛውም ጊዜ ፣ ለማንኛውም አካል በሚመለከተው ሰው በመረጃ ላየ የተመሰረተ ፈቃድ ውጪ ባለመግለጽ ያክብሩ ። የሰርቭይቨሮችን እምነት እና መብቃትን ያረጋግጡ።

**ክብር**
ሁሉም ድርጊቶች ወይም ውሳኔዎች የሰርቫይቨሮችን ምርጫዎች፣ ምኞቶች፣ መብቶች እና ክብር በማክበር መመራት አለባቸው

**አለማዳላት**
ሰርቫይቨሮች ዕድሜያቸው፣ ወሲባዊ ዝንባሌያቸው፣ የስርዓተ ጾታ መለያቸው፣ የጾታቸው፣ ዘራቸው፣ የጋብቻ ሁኔታቸው ወይም ሌላ ማንኛውም ባህሪያቸው ምንም ይሁን ምን እኩል እና ፍትሃዊ አያያዝ ማግኘት አለባቸው።

**ሐቀኝነት**
ለራሳቸው የተሻለውን ውሳኔ ማድረጋቸውን ለማረጋገጥ ሰርቫይቨሮች ስለሚያገኟቸው አገልግሎቶች እና ስለ ተሳትፎ ስጋቶች እና ጥቅሞች ሙሉ በሙሉ ሊነገራቸው ይገባል።

ቢያምንም እንኳን አንድን የተወሰነ ግብ ወይም ውጤት ለማምጣት የሚያደርጉትን ጥረት በማንኛውም የሂደቱ ደረጃ የሰርቫይቭሮችን ውክልና፣ ክብርን ወይም ስልጣንን እንደማይጎዳ ማረጋገጥ አለባቸው። “በ”ምንም ጉዳት አለማድረስ” በሚለው መርህ ስር ሰርቫይቭሮችን ያማከለ አካሄድን መተግበር በየደረጃው ያሉ ሰራተኞች የየራሳቸውን አድሏዊነት እንዲገነዘቡ እና እንደ አገልግሎት አቅራቢዎች ያለማዳላት መርሆዎች እና ክብር ጋር የማይጣጣሙ አመለካከቶች ያሉዋቸው እንደሆነ እንዲመረምሩ ይጠይቃል።

# ድርጅቶች የሚያቀርቧቸው የግምገማ ጥያቄዎች

## ስለ ዐውዶቻቸው:-

### በማህበረሰባችን ወሲባዊ ጥቃት የደረሰበት ማን ነው?

- ወሲባዊ ጥቃት በማህበረሰባችን ያሉ ክፍሎች ላይ ማለትም ሴቶች፣ ወንዶች፣ ልጆች፣ LGBTQI+ ሰዎች፣ አካል ጉዳተኞች፣ የአገሬው ተወላጆች፣ እስረኞች፣ በውሲባዊ ጥቃት የተወለዱ ህጻናት፣ የቤተሰብ አባላት፣ ወዘተ በምን መልኩ ተጽዕኖ አሳድሯል?

### ከፍትህ እና ከተጠያቂነት አጠቃላይ አቀራረብ ጋር የተያያዙ የመረጃ ምንጮች አሉ? በማኅበረሰባችን ውስጥ ላሉ ሰርቫይቭሮች ተደራሽ ናቸው ?

- ቅድሚያ የሚሰጧቸውን ነገሮች ለመቅረጽ እና ግባቸውን ለመለየት እንዲችሉ የሚረዳቸው ተጨማሪ መረጃ ወይም ግብአት አለ?

### ሰርቫይቭሮችከእኛ ጋር ለመሥራት በመምጣታቸው ምን ዓይነት አደጋዎች ያጋጥሟቸዋል—አካላዊ፣ አእምሯዊ፣ ማህበራዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ?

- እነዚህ አደጋዎች ለተለያዩ ህዝቦች እንዴት ይለያያሉ?

### በማኅበረሰባችን ውስጥ ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ሰርቫይቭሮች እንዴት ይታያሉ?

- የተገለሉ ናቸው ወይስ አንዳንድ ጭፍን ጥላቻ ያጋጥሟቸዋል?
- አንዳንድ ህዝቦች የተለየ መገለል ወይም ጭፍን ጥላቻ ያጋጥማቸዋል?

### ሰርቫይቭሮች ከእኛ ጋር ለመሥራት ወይም ላለመሰራት ሲመርጡ ከማኅበረሰቡ ውስጥም ሆነ ውጪ ምን ዓይነት ጫናዎች ሊያጋጥሟቸው ይችላሉ?

- ግጭቱ እየቀጠለ ከሆነ፣ ከእኛ ጋር አብረው እንዲሠሩ ወይም እንዳይሠሩ የሚደርስባቸው ጫና ላይ እንዴት ተጽዕኖ ያሳድራል?

### ከዚህ ቀደም በተመሳሳይ መርሃግብሮች ላይ በመሳተፍ ሰርቫይቭሮች ሰዎች ቅር ተሰኝተዋል ወይም ተጎድተዋል?

### የሰርቫይቭሮች እና መረጃዎቻቸው ጥበቃ ምን ዓይነት አደጋዎች ያጋጥሟቸዋል?

### በዚህ አውድ ውስጥ ከሰርቫይቭሮች ጋር የሚሰሩት ሌሎች ተዋናዮች እነማን ናቸው?

- ምን አይነት መርሃግብሮች ይሰጣሉ እና የትኞቹን ማህበረሰቦች ያገለግላሉ?
- ምን አይነት መርሃግብሮች ይሰጣሉ እና የትኞቹ ማህበረሰቦች አሁን ካለው መርሃግብር ውጪ እየተደረጉ ነው?

### መርሃግብራችን ሊያሳውቀው የሚገባ ወጎች፣ ቅርሶች ወይም የጋራ ኩራቶች አሉ?

## ለራሳቸው:-

**ልንደግፋቸው ያሰብናቸው ሰርቫይቨሮች ስለፍላጎቶቻቸው፣ ተግዳሮቶቻቸው እና ቅድሚያ የሚሰጧቸው ጉዳዮችን ግልጽ የሆነ ግንዛቤ እንዲኖረን ለማድረግ የቅርብ ጊዜ የፍላጎት ዳሠሳ አካሂደናል?**

- በጾታ፣ በፆታ፣ በእድሜ፣ በትምህርት ደረጃ፣ "የኑሮ ደረጃ "፣ የወንጀል/ጥሰት አይነቶች፣ የተፈናቀሉ/ያልተፈናቀሉ፣ ብሔረሰቦች እና ሌሎች ቡድኖች፣ ገጠር-ከተሜ እና አካል ጉዳት ላይ በመመርኮዝ በተለያዩ ህዝቦች ፍላጎቶች፣ ተግዳሮቶች እና ቅድሚያዎችን ከፋፍለናል?
- ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት የተወለዱ ልጆችን ፍላጎት ተመልክተናል?

**የሥራችን ግቦች ምንድን ናቸው?**

- ጥረታችንን የሚገፋፉ ዋና ዋና ምክንያቶች ምንድን ናቸው?
- እነዚህ ግቦች ከሰርቫይቨሮች በተገኘ መረጃ የተቀረፁ ናቸው?

**ሰርቫይቨሮች የሥራችንን ፅንሰ-ሀሳብ በመቅረፅ፣ በማዳበር፣ በመቅረጽ እና በመተግበር ለእነሱ እና ከእነሱ ጋር በመሆን ሥራችንን በመተግበር ረገድ ሚና እንዲኖራቸው እንዴት እናረጋግጣለን?**

- ይህንን ለማቀላጠፍ ምን አይነት ስርዓቶች ተዘርግተዋል?

**ሰርቫይቨሮች ሊያካፍሉን የሚችሉትን ሚስጥራዊ መረጃ ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ የማከማቸት አቅም አለን?**

**ከእኛ ጋር ሲሰሩ ሰርቫይቨሮች ሊያጋጥሟቸው የሚችሉትን አደጋዎች ለመገምገም እና ለመቀነስ ምን አይነት ስልቶችን አስቀምጠናል?**

- እነዚህ ስልቶች የተለያዩ ህዝቦች ከእኛ ጋር ሲሰሩ የተለያዩ አደጋዎች ሊያጋጥሟቸው እንደሚችሉ ያንፀባርቃሉ?

**ድርጅታችን ከሰርቫይቨሮች ጋር ሲሰራ ሊያጋጥመው የሚችለውን ማንኛውንም አደጋ ለመገምገም እና ለመቀነስ ምን አይነት ስልቶች አሉን?**

**በመርሃግብራችን ውስጥ ሰርቫይቨሮች ሊኖሩ ስለሚችሉት አደጋዎች እና ጥቅሞች ግልጽ ግንዛቤ አላቸው?**

**መርሃግብራችን የምናገኛቸውን ሰርቫይቨሮች በምን አይነት መንገዶች ያበረታታል? በአቀራረባችን ውስጥ አለማዳላትን እንዴት በንቃት እየተለማመድን ነው?**

**አገልግሎታችን ከተገለሉ ቡድኖች ላሉ ግለሰቦች ተደራሽ መሆኑን ለማረጋገጥ ምን አይነት እርምጃዎችን ወስደናል?**

- መርሃግብሮቻችን የተወሰኑ ሰርቫይቨሮችን ካልደረሱ፣ እንዳናዳርስ የሚከለክሉን መሰናክሎች ምንድን ናቸው?

**የሰራተኞቻችን በመልካም ተሞክሮዎች መሰረት መርሃግብሮቻችንን ለመፈፀም የሚያስፈልገው እውቀት እና ልምድ አላቸው? ካልሆነስ እነዚህን ክፍተቶች ለመቅረፍ የሚያስችል የቅጥር ስልት አለን?**

**ሰራተኞቻችን ሥራቸው "ምንም ጉዳት አለማድረስ" የሚለውን መርህ የሚያጠቃልል መሆኑን ለማረጋገጥ ምን ዓይነት ሥልጠና ወስደዋል? ከሰርቫይቨሮች ጋር በመደበኛነት ለሚሰሩ ሰራተኞቻችን የአእምሮ ጤና እና የስነ-ልቦና ግብአቶች ይገኛሉ?**

**አብረናቸው ከምንሰራቸው ሰርቫይቨሮች የሚጠብቁትን ነገር በኃላፊነት ለመመጠን እና በእውነታ ላይ የተመሰረቱ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የምንችለው እንዴት ነው?**

**የረዥም ጊዜ አቅም እንዲኖረን እና የሰርቫይቨሮች ማእከላዊ ለመሆን ገንዘብ የማግኛ ማመልከቻዎች፣የትግበራ ዕቅዶቻችን፣ ድርጅታዊ ፖሊሲዎች፣ መደበኛ የአሠራር ሂደቶች፣ ወዘተ ምን ማካተት አለብን?**

- ወደፊት ከሰርቫይቨሮች ሊመጡ ለሚችሉ ጥያቄዎች (ለምሳሌ፡ መረጃቸውን እንደ መርሃግብሩ አካል ለመጠቀም ያላቸውን ፈቃድ ማሻሻልን በተመለከተ) ምላሽ ለመስጠት ዝግጁ ነን?

**በመርሃግብራችን ውስጥ የሚሳተፉት ሰርቫይቨሮች ፈቃደኛ ተሳታፊ መሆናቸውን እና ከእኛ ጋር እንዲተባበሩ ጫና እንደማይደረግባቸው እንዴት ማረጋገጥ እንችላለን?**

- ሰርቫይቨሮች በመርሃግብራችን መሳተፍ እንደማይፈልጉ ከወሰኑ ግልጽ የሆነ ሂደት አለን? በዚህ ሁኔታ ውስጥ ምን እርምጃዎች መውሰድ አለብን?

**በማኅበረሰባችን ውስጥ ካሉ ሰርቫይቨሮች ስለመርሃግብራችን እንዲያውቁ ለማድረግ የረጅም ጊዜ ግንኙነትን እንዴት እናስቀጥላልን?**

- እነሱን ለመድረስ የትኞቹ የግንኙነት ዓይነቶች ተስማሚ ናቸው (ቋንቋዎችን፣ ማንበብና መጻፍ ደረጃዎችን እና የቴክኖሎጂ ተደራሽነትን ከግምት ውስጥ በማስገባት)?
- ከተለዋዋጭ የደህንነት ሁኔታዎች አንፃር ወይም የደህንነት ጥሰት ካለ ሰርቫይቨሮችን ለማግኘት ዝግጁ ነን?

### ለሰርቫይቨሮች፦

**በመርሃግብራችን ለመሳተፍ ውይም አለመሳተፍን ለመወሰን እንዲረዳዎ ማወቅ የሚፈልጉት ተጨማሪ መረጃ አለ?**

**በመርሃግብራችን ውስጥ ምን ያህል ጊዜ እና በየትኞቹ መንገዶች መመከር/መሳተፍ ይፈልጋሉ?**

**በመርሃግብራችን ውስጥ መሳተፍ ስለሚያስከትላቸው ጉዳቶች እና ጥቅሞች ግልጽ የሆነ ግንዛቤ እንዳለዎ ይሰማዎታል?**

**ለማጋራት ፈቃደኛ የሆኑት መረጃ ምንድን ነው እና ለምን ዓላማዎች (የተለያዩ አማራጮችን እና አጠቃቀሞችን ይስጡ)?**

**ከዚህ ቀደም በማናቸውም ተመሳሳይ መርሃግብሮች ተሳትፈዋል?**

- ልምድዎ ምን ይመስል ነበር?
- ምን ጥሩ ሰርቷል?
- በምን ላይ ሊሻሻል ይችል ነበር?

**ከዚህ ቀደም ድጋፍ ለማግኘት ምን መሰናክሎች አጋጥመውዎታል?**

**በመርሃግበራችን የመሳተፍ ችሎታዎ ላይ የሚያሳስብዎት ነገር አለ?**


## ተጨማሪ ንባብ

**ከስነ ምግባር እና ከሰርቫይቨሮች ጋር አብሮ ለመስራት ምርጥ ተሞክሮዎችን የሚመለከቱ ምሳሌ የሚሆኑ የአደጋ ግምገማ እና በመረጃ ላይ የተመሰረተ ስምምነትን መሰብሰብያ ዝርዝርን ጨምሮ ግብዓቶች እና ተጨማሪ የንባብ ሰነዶች በመሳሪያ ጥቅሉ ተጨማሪ ንባብ ክፍል ውስጥ ይገኛሉ።**

# 2. ሁለንተናዊ የድጋፍ አገልግሎቶች

### መግቢያ

**ሰርቫይቨሮች በተለይ ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት መጥፎ ተጽህኖ የተለያዩ አገልግሎቶችን እንዲስፈልጋቸው ያደርጋል። ሰርቫይቨሮች የሚያስፈልጓቸው አገልግሎቶች የጤና ጥበቃ (የተሟላ የስርዓተ ጾታና የስነ-ተዋልዶ ጤና አገልግሎትን ይጨምራል)፣ የዐይምሮ ጤና፣ የስነ-ልቦና ድጋፍ፣ የሕግ ድጋፍ፣ የትምህርት፣ የምጣኔ ሃብት፣ የተሀድሶ ዕድሎችን እንዲሁም**



**የኑሮ ዘይቤ ድጋፎችን ያጠቃልላል። በጾታዊ ጥቃት ውስጥ የተወለዱ ህፃናት ከቤተሰብ እና ከማህበረሰብ ከሚኖር መገለል ጋር በተገናኘ እርዳታን ከሚሹት ውስጥ የሚካተቱ ሲሆኑ ከህግ ከሚኖራቸው መብት እና በሕግ በሚኖራቸው መብት ልክ ሊያገኙዋቸው የሚገባ እንደ ጤና እና ትምህርት ያሉ አገልግሎቶች ፍላጎትን ማሟላትን ይጨምራል።**

አካላዊ እና ስነ-ልቦናዊ ጭንቀት፣ የደህንነት ስጋት፣ የመጠለያ ማጣት እንዲሁም በማህበረሰቡ መገለል እየደረሰባቸው የሚገኙ ሰርቫይቨሮች አብዛኛውን ጊዜ ከመሠረታዊ የስነ-ልቦና እና የደህንነት ፍላጎታቸውን ለሟሟላት ይታገላሉ። እኚህ እንደ የጤና ጥበቃ፣ ምግብ ፣ ልብስ እና መጠለያ ያሉ መሰረታዊ ፍላጎቶች ድጋፍ የሰርቫይቨሮችን ጭንቀት እና እንደ ራስን ማጥፋት እና ለህይወት ግድ ማጣት በሀሪዎች እዲቀንሱ ጉልህ አስተዋጾ ይኖረዋል።

የአካላዊ እና የደንነት ፍላጎታቸውን ለማሟላት የሚደረጉ ድጋፎችን ተከትሎ ሰርቫይቨሮች ቀስ በቀስ ትኩረታቸውን ወደ ስነ-ልቦና ጤንነት፣ ማህበራዊ ግንኙነት፣ የደረሰባቸውን መጥፎ ድርጊት ተቀብለው ፍትሕ፣ ተጠያቂነት እና እውነታቸው እንዲነገር ቁርጠኛ ይሆናሉ። በዚህ መልኩ ከአለፉበት የአስጨናቂ የሕይወት ጉዞ በኋላ ሰርቫይቨሮች ወደ ነባሩ ማንነታቸውን ለማግኘት በሚሸጋገሩበት ደረጃ ላይ የስነ-ልቦና እና ማህበራዊ ድጋፍ እጅግ አስፈላጊ ይሆናል።



የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት ለሰርቫይቨሮች በቀጥታ የተሟላ የአገልግሎት ድጋፍ በመስጠት (የማድረግ አቅም ካላቸው) አልያም ሰርቫይቨሮች ከሦስተኛ ወገኖች ድጋፍ እዲያገኙ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ፍላጎቶችን ለማሟላት ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ። የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማቱ ሰርቫይቨሮች ጋር አብሮ ለማስራት ከዚህ ቀደም ድጋፍ ያገኙ መሆኑን ወይም ድጋፍ እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ የሚያውቁ መሆኑን በመገመት ሳይዘናጉ ሰርቫይቨሮች ሌላ ዓይነት ድጋፍ እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ መረጃ መስጠት አለባቸው። ተቋማቱ ቢያንስ የሚከተሉትን ማድረግ አለባቸው፡-

- ጥራት እና ክፍተታቸውን ጨምሮ ሊገኙ የሚችሉ የአገልግሎት ድጋፎችን ዝርዝር መያዝ
- ሰርቫይቨሮች እንዴት ወደ አገልግሎት ድጋፉ መምራት እንደሚችሉ ማወቅ እና የአገልግሎት ድጋፎቹን እንከን በሚገባ ማስረዳት
- ተቋሙ የሚሰጠውን አገልግሎት ሌሎች ተቋማት እንዲረዱ ማድረግ

የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት ታሪክ ለመንገር እና ከፍትሕ ጋር ለተገናኙ ጉዳዮች መረጃ በሚያጠናቅሩበት እንዲሁም በአዕምሮ ጤና፣ የስነልቦና እና የአኗኗር ድጋፍ በሚያቀርቡበት ወቅት ሰርቫይቨሮች ድጋፍ ለማግኘት በማሰብ የሚያቀርቡት ታሪክ ወይም ውንጀላዎች ተዓማኒነት የጎደላቸው ናቸው በማለት የሕግ ባለድረሻ አካላት ሊያቀርቡት የሚችሉትን ጥያቄ ተቋማቱ ሊያስከትልው የሚችለውን ስጋት ሊያውቁ እና ሊጠነቀቁ ይገባል። ይህንን ስጋት ለማስቀረት ተቋማቱ ሰርቫይቨሮች ከሌሎች የአገልግሎት ድጋፍ ሰጪዎች እርዳታ የሚያገኙበትን አመቺ መንገድ መምራት አለባቸው። ተደራሽ የድጋፍ መስጫ መንገድ ባለመኖሩ ወይንም ተቋሙ ድጋፍ ከመስጠት በተጨማሪ መረጃ የሚይዝበት ግዴታ በተቋሙ ድጋፍ ሰጪ አካላት የተቀመጠ ሲሆን ተቋማቱ የሚሰጡት አገልግሎት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሰርቫይቨሩ ድጋፍ ለማግኘት መረጃ የመሰጠት ግዴታ የሌለበት መሆኑን በሚገልጽ መልኩ አገልግሎታቸውን መቅረጽ አለባቸው።

**Organizations considering providing mental health and psychosocial support services, while also undertaking documentation for truth-telling and justice-related purposes, should conduct a thorough analysis of the risks and benefits involved in offering these services using the “Strengths, Weaknesses, Opportunities, and Threats” analysis tool**

# ድርጅቶች የሚያቀርቧቸው የግምገማ ጥያቄዎች

## ስለ ዐውዳቸው፦

**የጤና፣ የፍትህ እና የትምህርት ዘርፍ የህዝብ አገልግሎቶች ተግባራዊ ናቸው?**

- ከሆኑስ ሰርቫይቨሮች ለድጋፍ የትኞቹን የህዝብ አገልግሎቶች ማግኘት ይችላሉ?

**የትኞቹ ልዩ የድጋፍ አገልግሎቶች ለሰርቫይቨሮች ቀርበዋል (ህክምና፣ ስነ-ልቦናዊ፣ ህጋዊ፣ ስነ-ተዋልዶ፣ መተዳደሪያ፣ ትምህርታዊ፣ ሀይማኖታዊ፣ መንፈሳዊ፣ ባህላዊ፣ ሙያ፣ ሱስ አላግባብ መጠቀም እና ሱሰኝነትን እና መከላከያ አገልግሎቶችን ጨምሮ በፆታ ላይ የተመሰረተ ጥቃትን ከቤተሰቦቻቸው ጋር ማግኘት ይችላሉ)?**

- አገልግሎትን ለማግኘት ተጨማሪ እንቅፋቶችን ለሚያጋጥማቸው ሰርቫይቨሮች ድጋፍ የሚሰጡ አገልግሎቶች አሉ?

**ካሉት የድጋፍ አገልግሎቶች እኛ በምንሰራበት ዐውድ ውስጥ ላሉ ሰርቫይቨሮች ሁሉ ተደራሽ ናቸው ወይስ በአንድ የተወሰነ ጂኦግራፊያዊ ቦታ ላይ ያተኮሩ ናቸው?**

- እነዚህን አገልግሎቶች የሚያቀርበው ማነው? ሰራተኞቻቸው ከሰርቫይቨሮች ጋር ለመስራት ደህንነታቸው የተጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ተገቢውን የጀርባ ምርመራ አድርገዋል?
- ሰራተኞቻቸው የሰርቫይቨሮችን ፍላጎት ለማሟላት እና “ምንም ጉዳት አለማድረስ” በሚለው መርህ መስራታቸውን ለማረጋገጥ በቂ ስልጠና ወስደዋል? ሰርቫይቨሮች እነዚህን አገልግሎቶች ለማግኘት በሚሞክሩበት ጊዜ አካላዊ ወይም ዲጂታል አደጋዎች ሊያጋጥሟቸው ይችላሉ (ለምሳሌ፡ አገልግሎቶችን ለመቀበል በመጓዝ ላይ ያለ አካላዊ አደጋ፣ ማንነታቸው ሲገለጽ፣ ወይም መረጃቸው ተጠልፏል)?
  - ሰርቫይቨሮች እነዚህን አገልግሎቶች እንዳያገኙ የሚከለክሏቸው ሌሎች መሰናክሎች አሉ?
- ሰርቫይቨሮች እነዚህን አገልግሎቶች እንዲያገኙ አጃቢ የሚያቀርቡ ድርጅቶች አሉ?
- የድጋፍ አገልግሎቶችን ለማግኘት ሰርቫይቨሮች ማሟላት ያለባቸው የብቃት መስፈርቶች አሉ?
- የሰርቫይቨሩ አገልግሎቶችን የማግኘት ችሎታው በሌሎች መርሃገበሮች ተሳትፎ ላይ የተመሰረተ ነው?
- አገልግሎቶች ሰርቫይቨሮች በሚናገሩት ቋንቋ(ዎች) ይገኛሉ? ካልሆነ ትርጓሜ አለ?
- ሰርቫይቨሮች በመረጡት ጾታ ሰው አገልግሎቶችን ለመቀበል መምረጥ ይችላሉ?
- እነዚህ የድጋፍ አገልግሎቶች ከ ግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ምክንያት ለተወለዱ ልጆች ይገኛሉ?

**ሰርቫይቨሮች አገልግሎቶችን ለማግኘት ሲሞክሩ ምን ዓይነት መሰናክሎች ሊያጋጥሟቸው ይችላሉ (ለምሳሌ ቋንቋ፣ ወጪ፣ የአካል ጉዳት መዳረሻ፣ መጓጓዣ፣ የመንከባከብ ኃላፊነት፣ የአሳዳጊ ፈቃድ፣ ወዘተ.)?**

**በአካባቢያችን ሙያዊ እንክብካቤን ለማግኘት ምን አይነት አመለካከት አለ? ለምሳሌ የአእምሮ ጤና አገልግሎቶችን በመፈለግ ዙሪያ መገለል አለ?**

## ለራሳቸው፦

**ኢላማ ያደረናቸው ተጠቃሚዎቻችን እነማን ናቸው?**

**በቀጥታ ለማቅረብ የተመቻቹት አገልግሎቶች የትኞቹ ናቸው?**

- ሁለቱንም የድጋፍ አገልግሎቶች (የአእምሮ ጤና እና የስነ-ልቦና ድጋፍ፣ የኑሮ ድጋፍ፣ ወዘተ) እና እውነትን ከመናገር እና ፍትህ ጋር የተያያዙ አገልግሎቶችን (መሰነድ ወዘተ) እየሰጠን ከሆነ ይህን የማድረግ አደጋን በሚገባ ገምግመነዋል? ሰርቫይቨሮችን እርዳታ ለማግኘት ቃል እንዲሰጡ አላስፈላጊ ጫና እንደማይደረሰባቸው ምን እርምጃዎች እንዳሉን እናረጋግጣለን?
  - አገልግሎቶቻችንን ከማግኘት ጋር በተገናኘ ያሉ ስጋቶችን ለሰርቫይቨሮች በግልፅ አሳውቀናል?

**ሌሎች አገልግሎት ሰጪዎች የትኞቹን አገልግሎቶች ለማቅረብ የተሻሉ ናቸው?**

**ከድርጅታችን/ማህበራችን ውጪ ሰርቭይቨሮችን ወደ ድጋፍ ሰጪዎች እንዴት ሪፍፈር እናደርጋለን?**

- በአከባቢያችን የአገልግሎት አቅራቢዎች ካርታ ወይም ሪፈራል መንገድ አለን?
  - የእነዚህን አገልግሎት አቅራቢዎች ካርታ ስናዘጋጅ ወይም የሪፈራል መንገዶችን ስንለይ የተለያዩ ሰርቫይቨሮችን ፍላጎት ከግምት ውስጥ አስገብተናል?
- የኬዝ ማናጅመንት አለን? ካልሆነ ሪፈራልን ለመከታተል የተመደበ የስራ አባል አለን?
- ይህን መረጃ የማቆየት እና የማዘመን ሃላፊነት የተጣለበት ማነው? ምን ያህል ጊዜ መሻሻል ይደረግበታል?
- በሪፈራል መንገዶች ላይ ክፍተቶችን በምንለይበት ጊዜ እንዴት ይገለፃሉ?

**ከድርጅታችን/ማህበራችን ውጪ ያሉ የድጋፍ ሰጪዎችን ጥራት የምንገመግምበት ስርዓቶች አሉን?**

- ሰርቭይቨሮች እያገኙ ያለውን የድጋፍ ጥራት ላይ በምን ያህል ጊዜ ግምግማ እናካሂዳለን?

**ሌሎች ድርጅቶች የምንሰጣቸውን አገልግሎቶች ያውቃሉ?**

- ስለምናቀርባቸው መርሃግብሮች ግንዛቤን እንዴት ማሳደግ እንችላለን?
- ሌሎች ድርጅቶች እኛን ያምኑናል?

**አገልግሎቶቻችን የሰርቫይቭሮችን ፍላጎቶች እና የተደራሽነት መስፈርቶችን ለማሟላት እንዴት ተነድፈዋል?**

- እኛን ማግኘት ለማይችሉ ሰዎች ለመድረስ ተንቀሳቃሽ አገልግሎቶችን መተግበር እንችላለን?

**ከምንደግፋቸው አገልግሎቶች መካከል የማህበረሰብ ስሜት ለመፍጠር የምንደግፍባቸው አጋጣሚዎች አሉን?**

- ይህንን እንዴት ማመቻቸት እንችላለን?
- ማህበረሰቡ ያምነናል? ካልሆነ እምነትን እንዴት መገንባት እንችላለን?

**ሰርቭይቭሮች በእነዚህ መርሃግብሮች ላይ በሚያደርጉት ተሳትፎ ነገሮች ላይ ቁጥጥር እንዳላቸው እንዲሰማቸው ማበረታታት የምንችለው እንዴት ነው?**

**መርሃግብሮቻችን በማህበረሰባችን ውስጥ ስለ ከግጭት ጋር የተያያዙ ወሲባዊ ጥቃቶች የበለጠ ግንዛቤ እንዲኖር አስተዋፅዖ ያደርጋሉ?**

- መርሃግብሮቻችን ከግጭት ጋር የተያያዙ ወሲባዊ ጥቃቶችን ለመፍታት ማህበረሰባችን የመሪነት ሚና እንዲጫወት ያበረታታሉ?

## ለሰርቫይቨሮች፡-

**የማህበረሰባችሁ አባላት ስለ ሰርቭይቭሮች ፍላጎት በቂ ግንዛቤ አላቸው?**

**ለእርስዎ በጣም አስፈላጊ የሆኑት የትኞቹ አገልግሎቶች ናቸው/ የትኞቹ አገልግሎቶች ለመቀበል ይፈልጋሉ?**

- ከዚህ ቀደም እነዚህን አገልግሎቶች እንዳይያገኙ የከለከለዎት ማነቆዎች አሉ?

**ከዚህ በፊት ስላሉት አገልግሎቶች እንዴት ሊያውቁ ቻሉ?**

**ስላሉት አገልግሎቶች በቂ መረጃ እንዳለዎት ይሰማዎታል?**

**ሌሎች ለማግኘት የሚፈልጓቸው ግን ማግኘት ያልቻሏቸው አገልግሎቶች አሉ?**

**አገልግሎት ሰጪዎች ሙያዊ፣ ተግባቢ፣ እና ለፍላጎቶችዎ ምላሽ ሰጭዎች ነበሩ?**

- ባገኙት አገልግሎት ረክተዋል? ካልሆነ ለምን?

**ያገኟቸው አገልግሎቶች በሕይወታችሁ ውስጥ ምን ለውጦች አምጥተዋል?**

**እነዚህን ለውጦች በግለሰብ፣ በማህበራዊ እና በቤተሰብ ደረጃዎች ላይ ሃሳብ ሊሰጡ ይችላሉ?**

**ሰርቫይቭሮች ወይም የሰርቫይቨር ኔትወርኮች በእርስዎ ዐውድ ውስጥ ባሉ አገልግሎቶች አቅርቦት ላይ ምን ሚና እየተጫወቱ ነው?**

- ሁለንተናዊ የድጋፍ አገልግሎቶችን በማቅረብ ላይ እንዴት መሳተፍ ይፈልጋሉ?

**በሰርቫይቨሮች እርስዎን ስለ አገልግሎቱ ለመናገር ወይም ወደ አገልግሎቱ በመቀበል ላይ ተሳትፎ ነበራቸው?**

- ካልሆነ፣ ይህ በአገልግሎቱ እንድትሳተፉ ያበረታታዎት ነበር?

**ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ለተጎዱ ልጆችዎ ወይም ሌሎች በቤተሰብዎ አገልግሎቶች ቀርበዋል?**

- ካልሆነ እንቅፋቶቹ ምን ነበሩ?

**በማህበረሰብህ ውስጥ የእንክብካቤ ተደራሽነትን ለማረጋገጥ ወይም ለማስተዋወቅ እድሎችን የሚከፍቱ ባህሎች አሉ?**

## ተጨማሪ ንባብ

**ሪፈራል መንገዶችን ለመገንባት እና እንዳሉ ለማስቀጠል የምሳሌ የአካሄድ ቻርት እንዲሁም ስላሉት የተለያዩ የአእምሮ ጤና እና የስነ-ልቦና ድጋፍ ዓይነቶች አጠቃላይ እይታን ጨምሮ ሁለንተናዊ የድጋፍ አገልግሎቶች ጋር የተያያዙ ግብዓቶች እና ተጨማሪ የንባብ ሰነዶች በመሳሪያው ተጨማሪ ንባብ ክፍል ውስጥ ይገኛሉ።**

# 3. እውነት ይፋ ማድረግ እና ስነዳ

## መግቢያ

**በስነዳ ሂደት ውስጥ ለመሳተፍ የወሰነ ሰርቫይቨር እውቅና ለማግኘት፣ እንዲሁም ፈውስ እና ፍትህ ለማግኘት ወሳኝ መነሻ ነጥቦች ናቸው። ለተለያዩ ምክንያቶች ሰርቫይቨሩ ለመሳተፍ ፍቃደኛ ሊሆን ይችላል። በአንዳንድ ሁኔታዎች ታሪካቸውን የመናገር እድል ማግኘታቸው የመንፈስ መረጋጋትን እና ከሌሎች መሠል ጥቃት ከደረሰባቸው ሰዎች ጋር ህብረትን ለመፍጠር አጋጣሚ ይሆናል። በሌሎች ሁኔታዎች የሚሰጡት መረጃ በታሪክ**



**መዝገብ መያዙ የእውነትን ይፋ ጅምሮች፣ የእርቅ ሂደቶች እና በሽግግር ፍትህ ማህበረሰቡ ለዘላቂው ከአለፈ ታሪኩ ጋር ታርቆ መግባባትን እና ፈውስ እንዲያገኝ ባለው አስተዋጾ ተነሳስተው ሊሆን ይችላል። ሌሎች በፍትህ አደባባይ ተጠያቂነት እንዲሰፍን ታሪካቸው እንዲመዘገብ ሊፈልጉ ይችላሉ።**

ከሰርቫይቨሮች መረጃ ለማሰባሰብ ያቀደ ተቋም የመጀመሪያ ስራው መረጃውን የሚሰበስብበትን አላማ መለየት ይሆናል፡፡ ይህም ስለሚደረገው የመረጃ ማሰባሰብ አይነቶች ሰርቫይቨሮቹን በማሳወቅ እንዲሁም ስለተሳተፏቸው እና የመረጃውን አጠቃቀም በሚመለከት ግልጽ እና እውነተኛ መረጃ አግኝተው ውሳኔ እንዲወስኑ ያግዛል፡፡

ሰርቫይቨሮችን ቃለመጠይቅ ከማድረጉ አስቀድሞ ተቋሙ የሚሰበሰበው መረጃ ወይንም ዘገባ ደህንነቱ እንዲጠበቅ እና ሚስጥር ለመጠበቅ ተቋሙ የመረጃ አያያዝ አሰራሩን መፈተሽ አለበት፡፡ ተቋሙ ስራውን በጥንቃቄ፣ ስነ-ምግባር በተሞላበት እና በአግባቡ ለማከናወን የተቋሙ ሠራተኞች አስፈላጊዉን የመረጃ አያያዝ መስፈርት የሚያሟላ ስልጠና ማግኘት አለባቸው፡፡ በተጨማሪም ተቋሙ መረጃዎቹን የሚያጠናቅረው ለፍርድ ቤት ማስረጃ ለማቅረብ አላማ ከሆነ የተቋሙ ሠራተኞች ተገቢውን የማስረጃ ምዘና መስፈርትን መሠረት ያደረገ የማሰባሰብ ክህሎት ሊኖራቸው ይገባል፡፡

ተቋማቱ የተጎጂው መረጃን አስቀድሞ ሌላ ቦታ አለማስመዝገቡን ወይንም ጉዳዩን ለጋዜጠኞች አለመናገሩን ሳያረጋግጡ መረጃውን መመዝገብ የለባቸውም፡፡ መረጃውን አስመዝግቦ ከነበረ ተቋሙ ጉዳዩን በጥንቃቄ በማጤን መረጃውን በድጋሜ መመዝገቡ ተጨማሪ እሴት ሊኖረው እንደሚችል ካመነበት ብቻ ተጨማሪ ምዝገባውን ሊያከናው ይገባል፡፡ ለምሳሌ ከዚህ ቀደም በህግ ተመዝግቦ የነበረ ጉዳይ በሰለጠነ የፎሬንሲክ ባለሙያ እና በጤና ምርመራ ታግዞ በድጋሜ የሚመዘገብ ከሆነ የቀደመውን ምዝገባ ሊያጠናክረው ይችላል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ግን መረጃ በድጋሜ መመዝገብ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል፡፡

Organizations considering beginning a documentation initiative should consider conducting a thorough analysis of the goals, risks, and benefits—and their preparedness for doing so—using the "Strengths, Weaknesses, Opportunities, and Threats" analysis tool.

## ማን ለምን አላማ መረጃ ሊመዘግብ ይችላል?

### መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት እና የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት

- በዓለምአቀፍ ሕግ ስር ወንጀል የሆነ ጾታዊ ጥቃትን በመመዝገብ ለሀገር ውስጥ ወይንም ለዓለምአቀፍ ክስ እንዲቀርብ ለማስቻል ወይንም ወደፊት ለሚኖር የወንጀል ክስ ማስረጃ ጠብቆ ለማቆየት
- እንደ የተጎጂ ወኪሎች እና የሲቪል ቡድኖች ተጎጂዎችን በመወከል በሀገር ውስጥ፣በዓለም አቀፍ ወይም በቅይጥ ፍርድ ቤቶች ፊት ለመቆም፣
- የጾታዊ ጥቃትን በተመለከተ ለሚኖር የፍትሀ ብሔር ክስ ማስረጃ ለማሰባሰብ
- የጾታዊ ጥቃትን በተመለከተ ለሚኖር የሰብዓዊ መብቶች ክርክር እና ጥብቅና
- ለምርመራ ኮሚሽኖች፣ እውነት ለመናገር እና ለሌሎች የመረጃ ማጣራት መሳሪያዎች ጾታዊ ጥቃቶችን መዝግቦ ለማስቀመጥ
- ተጽህኖ እና ጉዳትን ለአስተዳደራዊ የካሳ ክሶች ለመመዝገብ
- የውትወታ ሥራ ለማከናወን የጾታዊ ጥቃቶች መረጃዎችን ለማሰባሰብ
- የጾታዊ ጥቃቶችን ስፋት፣ አካሄድ እና ተጽህኖ አረዳድን በማሻሻል ለጥናት እና ምርምር ግብዓት እንዲውል ለማድረግ፡፡

The International Protocol on the Documentation and Investigation of Sexual Violence in Conflict



## የሰለጠኑ የጤና ባለሙያዎች(የጤና ዶክተሮች እና የአዕምሮ ጤና ባለሙያዎች)

- የፎሬንሲክ እና የጤና መረጃ የሚመዘገበው፣ የሰለጠነ የጤና ባለሙያው የማሰቃየት እና/ወይንም ጾታዊ ጥቃት ተጎጂውን ዝርዝር ሙያዊ ቃለ መጠይቅ በመጠየቅ እና በመመርመር ሁሉንም Sequelae (የረጅም ጊዜ መጥፎ የሕይወት ጉዞ፣ አጋጣሚ ወይን ጉዳት ተጎጂውን ጉዳቱ ከደረሰ በኃላ ለብዙ አመታት የሚጎዳ ህመምን የሚገልጽ የጤና ሙያ ቃል) አካላዊ እና ስነ-ልቦናዊ ጥቃቶች በመመርመር ነው። የጤና መረጃ ቃለመጠይቁ የሕክምና ታሪክን እንዲሁም ስለ ቅድመ እና ድህረ መሠቃየት አካላዊ እና ስነልቦና ጤናን የተመለከቱ ጥያቄዎችን ይሸፍናል። ሰርቫይቨሮች የመሰቃየት ወይንም የጾታዊ ጥቃት ታሪክ ከመስማት በተጨማሪ የህክምና ዶክተሩ የሚነገረውን ታሪክ ከአካል እና ስነልቦና ምልክቶች ማስረጃ ጋር በማዛመድ የፎሬንሲክ ጤና ምርመራ በማድረግ እና የሚያዩትን እና የሚሰሙትን Sequelae እና አስፈላጊ ጠባሳዎችን እና ሌሎች አካላዊ ሁኔታዎችን ፎቶግራፍ በማንሳት በዘገባው ውስጥ ያካትታል። ቃለመጠይቁ፣ ምርመራው፣ ፎቶ ማንሳቱ እና ዘገባ መፃፉ ረጅም ሰዓት ይወስዳል።

## የሀገር ውስጥ የመንግስት አካላት

- ለፖሊስ ምርመራዎች እና አቃቤህጎች ከግጭት ጋር የተያያዙ ወሲባዊ ጥቃቶች ጉዳዩች ለመመርመር፣
- በዳኞች ለሚደረግ ምርመራ፣
- ለአቃቢያነ ሕግና ለጠበቆች የጾታዊ ጥቃት ወንጀሎችን ለመክሰስ የክርክር ስልታቸውን እንዲቀርጹበት
- ዳኞች ከግጭት ጋር የተያያዙ ወሲባዊ ጥቃት ጉዳዮችን ለማዳኘት
- ለሀገራዊ የእውነት ኮሚሽን የዓለም አቀፍ ሕግን የሚጥሱ የጾታዊ ጥቃት ወንጀሎችን ለመመዝገብ

The International Protocol on the Documentation and Investigation of Sexual Violence in Conflict

# ተጨማሪ ንባብ

**በመመዘኛው መሠረት መረጃ ለማሰባሰብ እና አጠቃቀም ቅደም ተከተል በሰነዱ ተጨማሪ ንባብ ክፍል ውስጥ ማግኘት ይቻላል።**



# ድርጅቶች የሚያቀርቧቸው የግምገማ ጥያቄዎች

## ስለ ዐውዳቸው:-

**የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ሰርቭይቨሮችን ታሪክ ለመሰነድ ጥረት ተደርጓል?**

ከሆነ:-

- ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ሰርቫይቨሮች በእነዚህ ጥረቶች ውስጥ በተከታታይ ተካተዋል?
- ዋና ሰናዶች እነማን ናቸው?
- ጥረቱ የተመራው በአለም አቀፍ ድርጅቶች ነው ወይስ በሀገር ውስጥ ድርጅቶች?
- የመሰነድ ጥረቶች ሁሉን አቀፍ፣ ሙያዊ፣ ሰርቫይቨሮችን ያማከለ፣ የሰሜት ቀወስን ያገናዘቡ እና ስርዓተ-ጾታን ያማከሉ ናቸው?
  - ይህንን ለመገምገም ምን ክትትል መንገዶች ተቀምጠዋል?
- ከተለያዩ የዕድሜ ቡድኖች እና ዘር፣ ብሔር፣ ጾታ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ጂኦግራፊያዊ እና ሃይማኖታዊ ዳራ የተወጣጡ ሰርቫይቨሮች ተካተዋል?

ካልሆነ:-

- ለአናሳ/የተገለሉ ቡድኖች ሰነዶችን የማግኘት ችሎታ ዋና እንቅፋቶች ምንድናቸው?
- በሰርቭይቨሮች የስነዳ ተነሳሽነቶች ውስጥ እንዲሳተፉ የሚያበረታቱ ወይም የሚከለክሉ “በር ጠባቂዎች”ን” (ለምሳሌ፣ የሃይማኖት ወይም የማህበረሰብ መሪዎች፣ የቤተሰብ አባላት፣ ሌሎች መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ወዘተ) ለይተናል?

**ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ሰርቫይቨሮችን እንደ የእውነት ኮሚሽን ወይም መደበኛ ባልሆነ/በማህበረሰብ የሚመራ እውነትን የፋ የማድረግ ስራዎች በመሳሰሉት ማንኛውም መደበኛ እውነትን ይፋ የማድረግ ሂደት ውስጥ እንዲሳተፉ ለሰርቫይቨሮች እድሎች አሉ /ነበሯቸው?**



ከሆነ:-

- በሂደቱ ቀረጻ እና ትግበራ ውስጥ ሰርቫይቨሮች ትርጉም ባለው መልኩ ተማክረው ነበር?
- ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ሰርቫይቨሮች ከመረጡ ማንነታቸው ሳይገለጽ የመሳተፍ ምርጫ ጋር ለመመስከር/ ታሪካቸውን ለማካፈል እድል ነበራቸው?
- ሂደቱ ልክ እንደ ከተገለሉ ዳራዎች የመጡ ሰርቭይቨሮችን አካታች ነበር (ለምሳሌ፣ አናሳ ብሄረሰቦች፣ LGBTQI+፣ ግለሰቦች)?
- ከሂደቱ የተገኙ ቁልፍ ግኝቶች ለህዝብ የተላለፉት እንዴት ነው?
- ከሂደቱ የተገኙ ምክሮች ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ሰርቫይቨሮችን ፍላጎቶች እና ቅድሚያ የሚሰጧቸውን ነገሮችን ከግምት ውስጥ ያስገባ ነበር?

ካልሆነ:-

- አካታች የሆነ እውነትን ይፋ የማድረግ ሂደትን ተግባራዊ ለማድረግ ዋና መሰናክሎች ምን ነበሩ፡
  - የእውነትን ይፋ የማድረግ ሂደት አላማ እና ጥቅሞችን አለማወቅ/አለመረዳት፣ የደህንነት ስጋቶች፣ የእውነትን ይፋ የማድረግ ሂደትን አላማ አለማወቅ/ አለመረዳት፣ ተደራሽነት አለመኖር (በማይደረስበት ቦታ ወይም ከጉዞ ጋር በተያያዙ ወጪዎች ምክንያት) ፣ መገለል?
  - እነዚህ እንቅፋቶች ለተለያዩ ሰርቫይቨሮች የሚለያዩት እንዴት ነው?
  - እነዚህን መሰናክሎች ለመቅረፍ ስልቶች በተሳካ ሁኔታ ተተግብረዋል?

- በመንግስት የሚመራ መደበኛ እውነትን ይፋ የማድረግ ሂደት በሌለበት መደበኛ ያልሆነ በሲቪል ማህበራት የሚመራ እውነትን ይፋ የማድረግ ሂደት ለማድረግ ይቻል ይሆን?
  - ከሆነ ይህ ምን ሊመስል ይችላል?


## ለራሳቸው:-

### የመሰነድ ሂደትን እያከናወኑ ላሉ ድርጅቶች:-

- መረጃን በአስተማማኝ ሁኔታ ለመሰብሰብ እና ለማከማቸት የሚያስችሉን ምን አይነት ስርዓቶችን ዘርግተናል?
  - ሰራተኞች በመረጃ አያያዝ ላይ መደበኛ ስልጠና እና ማስታወሻ ያገኛሉ?
- ሰነዶችን የምንሰበስበው ለምንድነው?
  - የመሰነድ አላማችን የምንሰበስበውን የመረጃ አይነት እንዴት ይቀርፃል?
- ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ሰርቫይቨሮችን ተሞክሮ ቃለ መጠይቅ ማድረግ የማይፈልጉ ጠቃሚ መረጃዎችን የምንሰበስብባቸው መንገዶች አሉን?
  - የሌሎች ድርጅቶች ሰነዶችን ለመሰብሰብ የሚያደርጉትን ጥረት ከመድገም ለመቆጠብ እና በስራችን አወንታዊ አስተዋጽዖ እያበረከተን መሆኑን እንዴት ማረጋገጥ እንችላለን? ለተለያዩ ድርጅቶች ብዙ ጊዜ ቃል ከመስጠት ጋር ተያይዘው ስለሚመጡ አደጋዎች ሰርቫይቨሮች በግልፅ እያሳወቅን ነው?
- ሰርቫይቨሮችን ያማከለ፣ በስነልቦና ቀውስን በአገናዘበ እና ስርዓተ-ፆታን በአማከለ መንገድ የመሰነድ ሂደቱን ለመምራት በቂ ብቃት ያላቸው ሰራተኞች አሉን?
  - ሰራተኞች ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ሰርቫይቨሮች መረጃዎችን ለመሰብሰብ በ ዓለምአቀፍ የስነምግባር ህግ ላይ ስለ ስልታዊ እና ግጭት-ነክ ወሲባዊ ጥቃት (ሙራድ ኮድ) የተቀመጡትን የመነሻ መረጃ የመሰብሰቢያ መስፈርቶችን ያውቃሉ?
  - ሰርቫይቨሮች ለቃለ መጠይቅ የሚያቀርብላቸውን ሰው ጾታ እንዲመርጡ እድል እንሰጣቸዋለን? ምርጫቸውን ለማክበር እንችላለን?
- በጂኦግራፊያዊ አካባቢያቸው፣ የደህንነት ስጋት፣ የቋንቋ እንቅፋቶች ወይም ሌሎች ምክንያቶች በመሰነድ ጥረቶች ላይካተቱ የሚችሉ ማህበረሰቦች/ቡድኖች የምንደርስበት መንገዶች አሉን?



- በስራችን ለመሳተፍ ተጨማሪ አደጋዎች የሚያጋጥማቸው የሰርቫይቨሮች ማህበረሰቦች/ቡድኖች ለማስቻል የጥበቃ ስልቶች አሉን?
  - እነዚህን የጥበቃ ስልቶች በማዘጋጀት ሰርቫይቨሮች እና የማህበረሰቡ አባላት ተሳትፈዋል?
- የሰርቫይቨሮችን ማንነት መጠበቃቸንን ለማረጋገጥ ምን አይነት ስርዓቶች አስቀምጠናል?
- በስነዳ ስራችን ላይ ለመሳተፍ በመረጃ የተደገፈ ፈቃዳቸውን ለመስጠት ለመወሰን ሰርቫይቨሮች የሚያስፈልጋቸውን መረጃ እየሰጠን መሆኑን ለማረጋገጥ ምን አይነት ስርዓቶች አስቀምጠናል?



- 

- በስነዳ ስራችን ውስጥ የሚሳተፉትን ሰርቫይቨሮች የሚጠብቁትን/ተስፋ የሚያደርጉትን ነገር በአግባቡ ለማስተካከል ምን እርምጃዎችን እየወሰድን ነው?
  - የስነዳ ስራውን የሚያከናውኑት ግለሰቦች ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ሰርቫይቨሮች ጋር በመሥራት ረገድ ተገቢውን ሥልጠና ወስደዋል?
  - ሰራተኞቻችን የስነዳ ሂደቱን ሙያዊ፣ ሁሉን አቀፍ እና ሰርቫይቨሮችን በአማከለ እና የሰሜት ቀውስን በአገናዘበ መልኩ መሆናቸውን ለመከታተል የሚያስችሉን ስርዓቶች አሉን?
- ቃል ከሰጡ በኋላ የሰርቫይቨሮችን ደህነት የምንደግፈው እንዴት ነው?
- የስነዳ ስራውን የሚያከናውኑ ሰራተኞቻችንን ደህንነት እንዴት ነው የምንደግፈው?
- ወደፊት ያካፈሉትን መረጃ ለመጠቀም ፈቃድ ለማግኘት ቃለ መጠይቅ ያደረግንላቸው ሰርቫይቨሮች ጋር ያለንን ግንኙነት ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ እንዴት እንቀጥላለን?
- በስነዳ ስራችን ውስጥ የተሣተፉ ሰርቫይቨሮችን እና ማህበረሰቦችን በስራችን ውስጥ እያደረግን ስለምንገኘው ማንኛውም ለውጥ እንዴት እናሳውቃቸዋለን?
- አቀራረባችን ለሰርቫይቨሮች የበለጠ ኃይል እንዲሰጥ ማድረግ የምንችለው ነገር አለ?
- በስነዳ ሰራችን የተማርነውን ስራችን ላይ እንዴት ተግባራዊ ማድረግ እንችላለን?

### በነባር እውነት ይፋ የማድረግ ሂደቶች ላይ ክፍተቶች የቱ ጋር ነበሩ?

- አሁን ያሉትን እውነት ይፋ የማድረግ ሂደት ተደራሽነትን ለማስፋት መርዳት እንችላለን?
- ይበልጥ አካታች ሂደት እንዲኖር ውትወታ የምናደርግባቸው መንገዶች አሉ?
- ታሪካቸውን ለማካፈል ገና እድል ላላገኙ ሰዎች የበለጠ የሚስማማ አካሄድ መንደፍ እንችላለን?
- ሰርቫይቨሮችን የበለጠ ምቾት እንዲሰማቸው ወይም እውነትን ይፋ የማድረግ ሂደት ላይ የባለቤትነት ስሜት እንዲያዳብሩ የሚረዱ በማህበረሰቦች ውስጥ የተረት ወጎች አሉ?
- እውነትን ይፋ የማውጣት ሂደት ውስጥ የተገኙ ግኝቶችን ወይም ምክረ ሃሳቦችን ወደፊት ማራመድ እና ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ቅድሚያ የሚሰጧቸውን እና ፍላጎቶችን የሚያንፀባርቁ መሆናቸውን ማረጋገጥ የምንችለው እንዴት ነው?

## ለሰርቫይቨሮች፡-

### በማናቸውም የሰነዳ ሥራ ጥረቶች ላይ ተሳትፈዋል?

ከሆነ፡-

- ከአንድ በላይ የስነዳ ባለሙያ/የስነዳ ባለሙያውች ቡድን ቃለ መጠይቅ አድርገውሎታል?
- የስነዳ ባለሙያዎቹ አክባሪዎች፣ አሳቢ እና በአካሄዳቸው ግልጽ እንደሆኑ ተሰምቶታል?
- ያጋሩት መረጃ ምን አይነት ጥቅም ላይ ሊውል እንደሚችል፣ በቃለ መጠይቁ ወቅት ፈቃድዎን የመስጠት/የመሰረዝ እድሎችን እና ከቃለ መጠይቁ በኋላ የስነዳ ባለሙያዎቹን እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ግልጽ መረጃ ተሰጥቶታል?
- ቃለ-መጠይቅ የምያቅርብሎትን ባለሙያ ጾታ ምርጫ ምን እንደሆነ ለመግለፅ እድል ነበረዎት? ከሆነስ ምርጫዎ ተከብሯል?
- ከስነዳ ባለሙያዎቹ ለሌሎች አገልግሎቶች ሪፈራል ጠይቀዋል/ወይም ተቀብለዋል?
- በቃለ-መጠይቁ ላይ እንዲሳተፉ በስነዳ ባለሙያዎቹ ውይም በሌሎች በማንኛውም መንገድ ጫናዎች ተሰምቶታል?

- ልምዱን ለእርስዎ የተሻለ ወይም የበለጠ የሚያበረታታ ሊያደርገው የሚችል ነገር ነበር?

ካልሆነ፡-

- ታሪክዎ እንዲሰነድ እድል ነበረዎ?
- ከነበሮት፣ ለምን ላለመሳተፍ መረጡ?

**በማንኛውም መደበኛ ወይም ኢ-መደበኛ እውነትን ይፋ የማውጣት ሂደት ውስጥ ተሳትፈዋል?**

ከሆነ፡-

- ልምድዎ ምን ይመስል ነበር?
- ስለተሞክሮዎ ምን አድነቀዋል?
- በተለየ ሁኔታ ቢደረግ የሚመኙት ነገር አለ?

ካልሆነ፡-

- ሰፋ ያለ እውነትን ይፋ የማውጣት ሂደት አካል ውስጥ ታሪክዎን የማካፈል ፍላጎት አለዎት?
- እርስዎ ተሳታፊ እንዲሆኑ ምን አይነት ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው (ለምሳሌ፡ ማንነታት ሳይገለጽ የመጋራት እድል፣ ወደ ሌላ ከተማ/ ክልል ሳይጓዙ በአካባቢ ደረጃ የመሳተፍ እድል፣ ወዘተ)?


# 4 ፍትህ እና ተጠያቂነት

## መግቢያ

**ይህ ሰነድ “ፍትሕ እና ተጠያቂነትን” እንደ ተጠያቂነት አይነቶች፣ እንደ መካስ እና በወንጀል ድርጊት ተበዳይ የሆኑ ሰዎች ሙሉ በሙሉ የሰብአዊ መብታቸው መጠቀም እንደ መቻል አድርጎ ይተረጉመዋል። ፍትህ እና ተያቂነት በተለያየ መልክ የሚይዙ እና በተለያዩ ዘዴዎች የሚገኙ ሲሆን በሽግግር ፍትህ መሳርያዎች፣ እውነትን ይፋ ማድረግ፣ በታሪክ ስነዳ፣ በካሳ፣ በውጤታማ መፍትሄዎች በመቀበል ወይንም ወንጀል እና መተላለፍን በማወቅ፣ በመደበኛ የፍትህ ብሔር ወይም የወንጀል ፍርድ ሂደት እና በኢ-መደበኛ እና ባህላዊ የፍትሕ አሰጣጥ ሂደቶችን ጨምሮ በተለያዩ መሳሪያዎች ሊረጋገጡ ይችላሉ።**



ፍትህ እና ተጠያቂነት በአብዛኛው አላግባብ የሚተረጎሙ ጽንሰ ሃሳቦች ሲሆኑ ከወንጀል ፍህት ስነ-ስርዓት ጋር ብቻ ያያይዙታል። ከዛም ባለፈ አብዛኛዎቹ ሀገራት ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ፍትህ አሰጣጥ ለማዘመን በዋናነት በወንጀለኛ የሕግ ተጠያቂነት ላይ ብቻ ትኩረት ያደርጋሉ። ይህ የትኩረት ነጥባቸው ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ወንጀል ምርመራን እና ክስ አመሰራረት መዘመን እና ለሥራው እውቀት እና ፍልስፍና መጎልበት ጉልህ አስተዋጾ አበርክቷል። ሆኖም ተጠያቂነት ብቻውን ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት በድጋሚ እነዳይፈጸም እና የችግሩ ስር መሰረት የሆኑትን፦ እነደ መዋቅራዊ የጾታ እኩልነት አለመስፈን፣ አድሎ፣ ጎጂ ባህልና ልማድን[1] ከመቅረፍ አንፃር ትንሽ አስተዋጽሆ እንዳለው በርካታ ማስረጃዎች ያመለክታሉ።



የተለያዩ ጥናታዊ ምርምሮች እንደሚያሳዩት ሰርቫይቨሮች በግጭትም ሆነ ያለግጭት ሁኔታ ውስጥ በወንጀለኛ ፍትህ ስነ-ስርአቱ አለመርካታቸውን የሚያሳዩ መሆኑን ተከትሎ የተለያዩ ሊህቃን እና የማህበረሰብ አንቂዎች የወንጀለኛ ፍትህ ስርዓቱን በተግባር በበቂ ሁኔታ ጾታዊ ጥቃቶችን ለመመከት ብዙ እንከኖች እንዳሉበት ለይተዋል። ይህ የጽሁፉ ክፍል ብዙ ሰርቫይቨሮች በፍትህ አሰጣጥ ስነ-ስርዓቱ የመናገር ነፃነታቸው እንደተነፈገ፣ በአግባቡ አለመወከላቸውን እንዲሁም በድጋሚ ለጥቃት የተጋለጡ መሆኑን ከግንዛቤ ያስገባል[2]።

ጥቃት አድራሾች ለፈፀሙት ወንጀል በመደበኛ ፍርድ ቤት ወይም በሌላ መደበኛ በሆነ መንገድ (ለምሳሌ፣ ማዕቀብ በመጣል) ተጠያቂ ሆነው ቅጣት ሲቀጡ ማየት ለሰርቫይቨሮች ያለው ጠቀሜታ እንደየ ዐውዱ እንዲሁም ከሰው ሰው ይለያያል። ለአንዳንዶች መደበኛ ፍርድ መሰጠቱ ለደረሰባቸው ጉዳት እውቅና መሆኑን የሚያረጋግጡበት ሲሆን ለሌሎች ደግሞ የጥፋተኝነት ውሳኔው ለማካካሻ ወይም መልሶ መቋቋም በር የሚከፍት ነው። ዝርዝር ስራዎች ከግምት ሳይገቡ የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት በመሰል ጉዳዮች ቁልፍ ሚና ሊጫወቱ የሚችሉ ሲሆን ሰርቫይቨሮች ለፍትህ እና ተጠያቂነት ለሚያቀርቡት ጥያቄ የህግ ክትትል የሚያገኙበትን አካል በማገናኘት፣ አማራጭ ፍትህ የማግኛ መንገዶችን እንዲለዩ በማድረግ፣ ከፉ ሰዎችን ስነ-ስርዓት ላማከለ አገልግሎት በመሟገት፣ በፍርድ ቤት ክርክር ሂደት የተደራሽነት ተግባራትን በማከናወን ሰርቫይቨሮችን የፍርድ ቤት ጉዳይ አብሮ በመከታተል እና ከፍትህ አሰጣት ሂደቱ በመካፈላቸው ሊኖር የሚችለውን ስጋት ለመቀነስ ስልቶችን በመቅረጽ ነው።

ሰርቫይቨሮችን ያማከለ የአሥራር ዘዴን መሠረት በማድረግ ይህ ሰነድ በጥቅሉ ፍላጎቶቻቸው ላይ የሚያጠነጥን ፍትህ እና ፈውስ በተለያየ መልኩ ሊኖር እና ሊረጋገጥ እንደሚችል የሚያምን መዕቀፍ ለሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት ያቀርባል። የተለያዩ የፍትህ እና ተጠያቂነት ዓይነቶች በሰነዱ ሌሎች ክፍሎች ተመልክተዋል ነገር ግን በዚህ ክፍል ጥያቄዎች እና ግብዓቶች ተጠያቂነት እና የበቀል ፍትሕን የሚፈልጉ ሰርቫይቨሮች ላይ የሚያተኩር ነው።

# ድርጅቶች የሚያቀርቧቸው የግምገማ ጥያቄዎች

## ስለዐ ውዳቸው፡-

**ከሚከተሉት የፍትህ የማግኘት ሂደቶችን የሚያመቻቹ አገልግሎቶች የትኞቹ በእኛ አውድ ውስጥ አሉ፡- ስለ ስነዳ ግንዛቤ ማሳደግ፣ የህግ አገልግሎት አቅርቦት እና ለሰርቫይቨሮች የፍትህ መንገድ፤ ማስረጃን ለመሰብሰብ የፎረዚክ የሕክምና ሰነዶች፤ የሰርቫይቨሮች ታሪካቸውን ለማካፈል እንዲዘጋጁ ለመርዳት የአእምሮ ጤና እና የስነ-ልቦና-ማህበራዊ ድጋፍ አገልግሎቶች፤ ለዓለም አቀፍ ወንጀሎች እና የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች በስነዳ እና በጉዳይ ግንባታ የሰለጠኑ ጠበቆች ማግኘት፤ ሴቶች እና ልጃገረዶች ወደ ፊት ለመምጣት ምቾት እንዲሰማቸው የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን በመመዝገብ እና በመመርመር ውስጥ የተሳተፉ ተጨማሪ የሴቶች ቡድን፤ የኑሮ ድጋፍ፤ ወይም ለሰርቫይቨሮች መጓጓዣ ወይም ድጋፍ ለመስጠት ወደ ገጠር ወይም ሩቅ አካባቢዎች የሚወጡ ተንቀሳቃሽ ድጋፍ ሰጪዎች?**

- ካለ፣ ሰርቫይቨሮች እነዚህን አገልግሎቶች እንዳያገኙ የሚከለክሉት ምንድን ነው?

**ከግጭት ጋር የተያያዙ ወሲባዊ ጥቃት ወንጀሎችን በአገር ውስጥ ፍርድ ቤት ለመክሰስ ፖለቲካዊ ፍላጎት አለ?**

**በሀገር ውስጥ የሕግ ሥርዓት ውስጥ ከግጭት ጋር የተያያዙ ወሲባዊ ጥቃት ወንጀሎችን ከዓለም አቀፍ ደረጃዎች ጋር በተጣጣመ መልኩ በግልጽ የሚተረጉሙ እና ወንጀል የሚያደርጉ ሕጎች አሉ?**

- ካለ የእነዚህ ህጎች ጠንካራ እና ደካማ ጎኖች ምንድን ናቸው?

**ሰርቫይቨሮች አንድአንድ አይነት ድጋፎችን ማለትም የጤና እንክብካቤ፣ የአእምሮ ጤና እና የሥነ ልቦና ድጋፍ፣ ማካካሻ ወዘተ የመሳሰሉትን እንዲያገኙ የሚያስችል በሀገር ውስጥ የሕግ ሥርዓት ውስጥ ሕጎች አሉ?**

- እነዚህን የድጋፍ አገልግሎቶች ለመደገፍ በቂ በጀት ተመድቧል?
- እነዚህን አገልግሎቶች ለማቅረብ በቂ የሰለጠኑ ባለሙያዎች እና ልዩ ባለሙያዎች አሉ?

**የሀገር ውስጥ ፍርድ ቤቶች ከግጭት ጋር የተያያዙ ወሲባዊ ጥቃት ወንጀሎችን ለመክሰስ ግብአቶች እና አቅሙ አላቸው?**

- በሀገር ውስጥ የሕግ ሥርዓት ውስጥ ቁልፍ ተዋናዮች (ዳኞች፣ ጠበቆች፣ ሕግ አስከባሪዎች) ሰርቫይቨሮችን በአማከለ ዳግም የስሜት ቀውስን በማያስከትል እና ማግለልን በማይጨምር መንገድ ከግጭት ጋር የተያያዙ ወሲባዊ ጥቃት ወንጀሎችን ለፍርድ ለማቅረብ በቂ ሥልጠና ወስደዋል?
- ከቁልፍ የፍትህ ተዋናዮች ጋር የተደረገን ስልጠና ተፅእኖ ለመገምገም ስርዓቶች ተዘርግተዋል?
- በቁልፍ ተዋናዮች (ዳኞች፣ ጠበቆች፣ ህግ አስከባሪዎች)መካከል እኩል የሆነ የፆታ ሚዛን አለ?

**ሌሎች መንግስታት ወይም ዓለምአቀፍ ተቋማት ከግጭት ጋር የተያያዙ ወሲባዊ ጥቃት ወንጀሎችን በወንጀል ችሎቶች ወይም አንድ አንድ በዋና ወንጀል አድራጊዎች ላይ የሚጣሉ ማዕቀቦችን የመሳሠሉ አማራጭ ዘዴዎች ለመደገፍ ፍላጎት አሳይተዋል?**

- ሀገሪቱ የዓለም አቀፉ የወንጀል ፍርድ ቤት (ICC) አባል ናት?
- ወንጀሎቹን በዓለምአቀፍ የዳኝነት ስልጣን ስር የመክሰስ እድል አለ?
- አገሪቱ ከግጭት ጋር የተያያዙ ወሲባዊ ጥቃት ወንጀሎችን ለመክሰስ ሊደግፍ የሚችል የክልልላዊ የሰብአዊ መብቶች ሥርዓት ውስጥ አባል ናት?
  - ልንማርባቸው የምንችልባቸው ከግጭት ጋር የተያያዙ ወሲባዊ ጥቃት ወንጀሎች የክስ ሂደቶች ነበሩ?

**ለሰርቫይቨሮች መፍትሄ ሊሰጡ የሚችሉ ባህላዊ የፍትህ ዘዴዎች አሉ?**

- በባህላዊ የፍትህ ዘዴዎች ውስጥ ቁልፍ ተዋናዮች እነማን ናቸው እናም ከግጭት ጋር የተያያዙ ወሲባዊ ጥቃት ሰርቫይቨሮች ለመደገፍ አቅም እና ፍላጎት ይኖራቸዋል?

**ወንጀለኞችን ለመፈወስ የሚረዱ ዘዴዎች አሉ?**

## ለራሳቸው፡-

**ለሰርቫይቨሮች ፍትህ ለማግኘት የምናደርገው ጥረት የት ላይ የተሻለ እንደሚሆን ለመረዳት በአውድአችን ውስጥ ስላሉት የተለያዩ የፍትህ አካላት ጥልቅ ትንታኔ አድርገናል?**

**ሰርቫይቨሮች የሕግ አገልግሎት እንዲያገኙ እንዴት መደገፍ እንችላለን (ለምሳሌ በማጣቀሻ ወይም በሂደቱ አብረናቸው በመሆን)?**

**በሂደት ላይ ያለ የሀገር ውስጥ ህጋዊ ሂደት ወይም የሀገር ውስጥ ችሎት ካለ ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ተጎጅዎች ተደራሽ መሆኑን የምናረጋግጠው እና ለፍላጎታቸው ምላሽ መስጠት የምንችለው እንዴት ነው?**

**ሰርቫይቨሮችን ያማከለ፣ የስነ-ልቦና ቀውስን ያገናዘበ እና የሥርዓተ-ጾታን ያማከለ አቀራረብ ላይ ለቁልፍ ሠራተኞች ሥልጠና ለመስጠት ዝግጁ ነን?**

- እነዚህን ስልጠናዎች እንዲሰጡልን ወይም እንዲደግፉ የምንጠቀማቸው አጋሮች አሉን?

**ፍትህን የማፈላለግ ሂደቱን የበለጠ አሳታፊ እና ሰርቫይቨሮችን ያማከለ ለማድረግ ልዩ ማሻሻያዎች እንዲደረጉ ውትወታ ማድረግ እንችላለን?**

**አጠቃላይ ህብረተሰቡን ለማስተማር እና መገለልን ለመቀነስ ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ወንጀሎች ላይ፣ ተጽእኖዎቻቸው እና የሰርቫይቨሮች ፍላጎት ላይ ግንዛቤን ማሳደግ እንችላለን?**




**የሀገር ውስጥ የፍርድ ሂደት በሌለበት ጊዜ ለፍትህ አማራጭ መንገድ (ለምሳሌ ዓለም አቀፍ ወይም ድብልቅ ፍርድ ቤት፣ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችን ክልላዊ ማስፈጸሚያ ወይም ማዕቀቦች) ልንወተውት የምንችላቸው የውጭ ግዛቶች ወይም ተቋማት አሉ?**

## ለሰርቫይቨሮች :-

**ፍትህ ለእርሶ ምን ማለት ነው?**

- ፍላጎቶችዎን በተሻለ ሁኔታ የሚያሟላ የተለየ ሂደት አለ (ለምሳሌ የወንጀል ችሎት፣ የፍትህ ሂደት፣ ወይም የማካካሻ ፕሮግራም)?

**የህግ አገልግሎቶችን ወይም በማንኛውም የፍትህ ወይም የተጠያቂነት ሂደቶች ውስጥ ተሳትፈዋል?**

ከሆነ:-

- ተሞክሮዎ ምን ይመስል ነበር?
- ስለ ሂደቱ ምን አደነቁ?
- ክፍተቶቹ ምን ላይ ነበሩ?

ካልሆነ

- እርስዎ እንዳይሳተፉ ያደረጉ ዋና ዋና መሰናክሎች ምን ነበሩ?

## ተጨማሪ ንባብ

**ለጅምላ ጭፍጨፋ ፍትህን ለማግኘት የሚጠቅሙ የህግ ማዕቀፎችን አጠቃላይ እይታን ጨምሮ ከፍትህ እና ተጠያቂነት ጋር የተያያዙ ግብአቶች በመሳሪያ ጥቅሉ ተጨማሪ ንባብ ክፍል ውስጥ ይገኛሉ።**

# 5 ማካካሻ

## መግቢያ

**ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ሰርቫይቨሮች እንደ ማካካሻ፣ መልሶ የመቋቋም፣ የመንፈስ እርከታ፣ ተሃድሶ እና ድጋሜ ያለመጠቃት ዋስትናን ጨምሮ የተለያዩ መፍትሔዎች እና ካሳዎች የማግኘት መብት አላቸው። ይህ መብት የዓለም አቀፍ የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች ስምምነት በተባበሩት መንግስታት ድርጅት (ተ.መ.ድ) ጠቅላላ ጉባኤ እ.ኤ.አ በ1966 መጽደቁን ተከትሎ በወጡ እንደ የማሰቃየት እና ሌሎች የጭካኔ፣ ኢ-ሰብአዊ የሆነና ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት ለማስቀረት የተደረገ ስምምነት (በእ.ኤ.ኣ በ1984 በተ.መ.ድ ጠቅላላ ጉባኤ የወጣ) እንዲሁም ሁሉንም ሰዎች ከአስገድዶ ስወራ ለመጠበቅ የተደረገ ስምምነት (በእ.ኤ.ኣ በ2010 በተ.መ.ድ ጠቅላላ ጉባኤ የወጣ) ተመልክቷል። በእ.ኤ.ኣ 2005 የተ.መ.ድ ጠቅላላ ጉባኤ ለከፍተኛ የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ሕግ ጥሰት እና ከባድ የዓለም አቀፍ የጦርነት ሕግ ጥሰት ተጎጂ ለሆኑ ሰዎች የእርምት እና የጉዳት ካሳ መሰረታዊ መርሆች እና መመሪያዎች አጽድቋል፤ ይህ መርሆ ለዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሕግ ጥሰት ተጎጂዎች "ፍትሐዊ እና ውጤታማ ፍትህ" የማግኘት መብትን ሀገራት የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑ ላይ ያተኩራል። ይህም" በቂ፣ ውጤታማ እና ፈጣን የጉዳት ካሳን" ይጨምራል።**

ሌሎች እንደ ናይሮቢ ዲክላሬሽን፣ በዋና ጽህፈት ቤቱ የወጣ በማካካሻ እና ከግጭት ጋር የሚገናኙ ጾታዊ ጥቃቶች የቅደም ተከተል ማስታወሻ፣ በሴቶች ላይ የሚደረግ ማንኛውንም አድሎአዊ ልዩነት ለማስወገድ በተደረገ ስምምነት ኮሚቴ የሰጠው ጠቅላላ አስተያየት፣ እንዲሁም እንደ የተ.መ.ድ የፀጥታው ምክር ቤት የተሰጡ ውሳኔዎች ያሉ አስገዳጅ ያልሆኑ ህጎች የወጡ ሲሆን እነዚህ ሕግጋት ሰርቫይቨሮች ውጤታማ መፍትሔ እና የማካካሻ የማግኘት መብት ተቀባይነት እንዲያገኝ መንገድ አመቻችተዋል።

የስር ነቀል ለውጥ ዘዴ ከጾታዊ ጥቃት ሰርቫይቨሮች የጉዳት ማካካሻ በሚመለከት ጉዳቶችን በተናጠል በመካስ ብቻ ሳይገደብ ጥቃቱ እንዲደርስ መጀመሪያውኑ የፈቀደው አድሎአዊ የሆነው መዋቅራዊ ሁኔታዎችን መቀየር እንደሚያስፈልግ ያስቀምጣል። ይህ ዘዴ እ.ኤ.ኣ በ2007 የሴቶች እና ልጃገረዶች የመፍትሄ እና ማካካሻ መብት ላይ በወጣው የናይሮቢ ዲክላሬሽን (Nairobi Declaration on Women's and Girls' Right to a Remedy and Reparation) ላይ የተጠነሰሰ ሲሆን፣ እ.ኤ.ኣ በ2009 በኢንተር አሜሪካ የሰብአዊ መብቶች ፍርድ ቤት በነበረ ኮተን ፊልድ እና ሜክሲኮ (Cotton Field v. Mexico) በተባለ መዝገብ ላይ ተንጸባርቋል። ከአድሎ ጋር በተገናኘ የሚኖሩ የጉዳት ካሳዎች በመልሶ ማቋቋም ሳይሆን "የሴቶችና ልጃ ገረዶችን ህይወት ቅርጽ በሚያሲዙ ከግጭት በኋላ የሚኖሩ የማህበራዊ እና ባህላዊ ኢ-ፍትሐዊነትን፣ ፖለተካዊ እና መዋቅራዊ እከልነትን የሚነፍጉ ተግባራትን ስር ነቀል መፍትሔ ሊሰጥ እንደሚገባ" በሁለቱም ውሳኔዎች ላይ ተንጸባርቋል።



እ.ኤ.ኣ በ2021 የኢንተር አሜሪካ የሰብአዊ መብቶች ፍርድ ቤት የኮሎንቢያ ሀገረ መንግስት እ.ኤ.ኣ በ2000 ጂነተህ በዶያ ሊማ ለተባለች ጋዜጠኛ መጠለፍ፣ መደፈር እና መሰቃየት ኃላፊነት እንዳለበት በመወሰን፣ ሀገረ መንግስቱ ጉዳዩን በመመርመር ለወንጀሉ ተጠያቂ የሆኑ ግለሰቦችን በመክሰስ እንዲቀጣ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡ ፡ ሀገረ መንግስቱ በጋዜጠኝነት ሥራ ለጾታዊ ጥቃት ሰለባ ለሆኑ ሴት ጋዜጠኞች ክብር የመታሰቢያ መዕከል እንዲያቋቁም፣ በሴት ጋዜጠኞች እና ሰብአዊ መብቶች ተሟጋቾች ላይ የደረሰን ጾታዊ ጥቃት እና ማስፈራሪያን የተመለከቱ የተሰባጠረ መረጃዎችን ይፋ እነዲያደርግ እና ሌሎች ለየት ያሉ የጉዳት ካሳ አይነቶችን ፍርድ ቤቱ ወስኗል።

ለስር ነቀል የጉዳት ማካካሻ አስተዋጽኦ ካማድረግም በላይ የመንግስት መር አስተዳደራዊ የጉዳት ካሳዎች፣ በፍርድቤት ከሚወሰኑ የጉዳት ካሳዎች ይልቅ የበለጠ ቁጥር ያላቸውን ተጎጂዎች የመጥቀም አቅምም አላቸው፡ ፡ ነገር ግን እንደ ኢራቅ፣ ፔሩ፣ እና ኮሎምቢያ ያሉ የሀገር ውስጥ የጉዳት ካሳ መርሐግበር የተደራጁ ቢሆንም አገራቱ በቂ፣ ሙሉ እና ፈጣን የጉዳት ማካካሻ ለሰርቫይቨሮች ለማድረስ ያልተቀረፉ ብዙ ተግዳሮቶች ይቀራሉ፡ ፡ በኮሎምቢያ በ እ.ኤ.ኣ በ2011 በወቅቱ ትልቅ አላማ አለው ተብሎ የታመነበት የሀገር ውስጥ የጉዳት ካሳ በሕግ ቁጥር 1448 ተቋቁሞ ነበር። መርሐ ግብሩ ከግጭት ጋር የተያያዙ ወሲባዊ ጥቃት ተጎጂ እና በጦርነት ውስጥ የተወለዱ ህፃናትን ይጨምራል። የጉዳት ማካካሻ ስር ነቀል ለውጥ የሚያመጣ እና ጾታን ያማከለ መሆን እንዳለበት ይቀበላል። ከመልካም አላማው ባሻገር መርሐ ግብሩ ተግባራዊ ከተደረገ አስር አመታት ቢያልፉም አሁንም ሰርቫይቨሮች እንደ መልሶ መቋቋም ያሉ የጉዳት ማካካሻዎችን ለማግኘት በጥበቃ ላይ ናቸው።

# ድርጅቶች የሚያቀርቧቸው የግምገማ ጥያቄዎች

## ስለ ዐውዳቸው፡-

**ከግጭት ጋር የተያያዙ ወሲባዊ ጥቃት ሰርቫይቨሮችን ጨምሮ ለሰብአዊ መብቶች ጥሰት ሰርቫይቨሮች ካሳ የመስጠት ፖለቲካዊ ፍላጎት እና አቅም አለ?**

ከሆነ፡-

- ምን ዓይነት የማካካሻ ዘዴዎች አሉ?
- ሰርቫይቨሮች ለማካካሻ ብቁ ለመሆን ምን መመዘኛዎችን ማሟላት አለባቸው? ይህን ውሳኔ የሚወስነው ማን ነው?
- ይህ ሂደት የተገለሉ ማህበረሰቦችን ጨምሮ ከግጭት ጋር የተያያዙ ወሲባዊ ጥቃት ሰርቫይቨሮችን ተደራሽ ነው?
  - ሂደቱ ለሰርቫይቨሮች ሁሉ ተደራሽ ካልሆነ በተለያዩ ቡድኖች (በጎሳ፣ ጾታ፣ ጾታዊነት፣ ሃይማኖታዊ ወዘተ) በመከፋፈል እንዳይደርሳቸው የሚከለክሉት መሰናክሎች ወይም እንቅፋቶች ምንድን ናቸው?
  - ሰርቫይቨሮችን ቅደም ተከተል የመስጠት አሰራር አለ?
- ከግጭት ጋር የተያያዙ ወሲባዊ ጥቃት ሰርቫይቨሮችን መርሃግብሩን በመንደፍ ፣ ትግበራ፣ ክትትል እና ግምገማ ላይ ትርጉም ባለው መልኩ ተማክረዋል?
- ይህ በገጠር/እሩቅ አካባቢ ላሉ የአካል መሰናክሎችን ሰዎች የትምህርት ደረጃን እና ከግምት ውስጥ በማስገባት የተገለሉ ሰዎችን ይጨምራል?
- የፖለቲካ ፈቃደኝነት የማካካሻ ስርዓቱን እንዴት ተጽእኖ ያደርጋል? አዲስ መንግስት ወደ ስልጣን ሲመጣ ሊዳከም ወይም ሊበታተን ይችላል የሚል ስጋት አለ?

ካልሆነ፡-

- ከግጭት ጋር የተያያዙ ወሲባዊ ጥቃት ሰርቫይቨሮች ካሳ የመስጠት ፍላጎት እና አቅም ያላቸው የውጭ ተቋማት አሉ? ለምሳሌ በጊዜያዊ የማካካሻ እርምጃዎች አሉ?
- በICC ውስጥ ያለው የተጎጂዎች ትረስት ከግጭት ጋር የተያያዙ ወሲባዊ ጥቃት ተጎጂዎች ድጋፍ እያደረገ ነው?

## ለራሳቸው፡-

**የማካካሻ መርሃግብር ካለ - ወይም የማካካሻ መርሃ ግብር የመኖር እድሉ ካለ ለሰርቫይቨሮች ተደራሽ እንዲሆን እና ለፍላጎታቸው ምላሽ እንዲሰጥ በንድፉ ላይ እንዴት ተጽዕኖ ማድረግ እንችላለን?**

- ለተወለዱ ወይም ለጦርነት ልጆችም ተደራሽ መሆኑን እንዴት ማረጋገጥ እንችላለን?
- የመርሃግብሩን ትግበራ ለማረጋገጥ እና ለመከታተል የሚረዱ ዘዴዎች አሉ? እንዴት ይሠራሉ?

**ለቁልፍ ሠራተኞች በተለያዩ ዓይነት የማካካሻ ዓይነቶች እና ሰርቫይቨሮች ያማከለ አቀራረብ ላይ ሥልጠና ለመስጠት ዝግጁ ነን?**

- እነዚህን ስልጠናዎች እንዲሰጡ ወይም እንዲደግፉ የምንጠራቸው አጋሮች አሉን?

**መርሃግብሩ የበለጠ አካታች፣ ተደራሽ እና ምላሽ ሰጪ እንዲሆን የተመረጡ ማሻሻያዎች ወይም ለውጦች እንዲደረጉ ውትወታ ማድረግ እንችላለን?**

- ሰርቫይቨሮችን ማቀዳደም ካለ ወደፊት ግጭት እንዲፈጠር ሊያባብስ የሚችል ኢፍትሃዊ ስሜት እንዳይፈጠር አካታችነት እና አድሎአዊ አለመሆን ላይ ውትወታ አድርገናል?

**ስለ ማካካሻ መርሃ ግብር አስፈላጊነት እና ዓላማ በማህበረሰቡ ውስጥ ግንዛቤ ማሳደግ እንችላለን?**

- ማካካሻ ለሚያገኙ ግለሰቦች፣ ቤተሰቦች እና ማህበረሰቦች በራስ የመወሰን መብታቸውን ሳንጥስ የማካካሻ ሀብታቸውን እንዴት በተሻለ መንገድ መጠቀም እንደሚችሉ ትምህርት ለመስጠት መመሪያ እና ድጋፍ መስጠት እንችላለን?

**መደበኛ የማካካሻ መርሃግብር በሌለበት ጊዜ ሰርቫይቨሮችን አስቸኳይ እና የረጅም ጊዜ ፍላጎቶቻቸው ምላሽ የሚሰጥ መርሃ ግብር ወይም ተነሳሽነት ለመንደፍ አብረናቸው ልንሠራ እንችላለን?**

## ሰርቫይቨሮችን ፦-

**መጠገን ለእርሶ ምን ማለት ነው?**

**የማካካሻ መርሃግብር ካለ በሂደቱ እና በፖሊሲው ዝግጅት ላይ ተሳትፈዋል?**

ከሆነ፦-

- ተሞክሮው ለእርሶ ምን ይመስል ነበር?
- ስለ ሂደቱ ምን አድንቀዋል?
- ክፍተቶቹ ምን ነበሩ?

ካልሆነ

- እርስዎ እንዳይሳተፉ የከለከልዎት ዋና መሰናክሎች ምን ነበሩ?
- በሂደቱ ውስጥ እንዴት መሳተፍ ይፈልጋሉ?

**የማካካሻ መርሃግብር ካለ ካሳ ጠይቀዋል?**

ከሆነ፦-

- ተሞክሮው ለእርሶ ምን ይመስል ነበር?
- ስለ ሂደቱ ምን አድንቀዋል?
- ክፍተቶቹ ምን ነበሩ?
- መርሃግብሩ ለፍላጎትዎ እና ቅድሚያ ለሚሰጧቸው ነገሮች ምላሽ ሰጥቷል?

ካልሆነ

- እርስዎ እንዳይሳተፉ የከለከልዎት ዋና መሰናክሎች ምን ነበሩ?
- ነባር የማካካሻ መርሃግብር በማይኖርበት ጊዜ የትኛው ዓይነት ማካካሻ ለእርስዎ በጣም ጠቃሚ እንደሚሆን ይሰማዎታል (ለምሳሌ፡ የግለሰብ የገንዘብ ማካካሻ፣ ልዩ አገልግሎቶች ፣ የሙያ ስልጠና፣ የመታሰቢያ መፍጠር፣ ወዘተ)?
- በሂደቱ ውስጥ እንዴት መሳተፍ ይፈልጋሉ??

## ተጨማሪ ንባብ

**ሰርቫይቨሮች የማካካሻ መርሃግብሮችን ንድፍ እንዴት እንደሚቀርጹ እና ለውጥ የሚያመጡ ማካካሻዎች ላይ መመሪያዎችን ጨምሮ ተጨማሪ መረጃን ጨምሮ ከማካካሻ ጋር የተያያዙ ግብዓቶች በመሳሪያው ተጨማሪ ንባብ ክፍል ውስጥ ይገኛሉ።**


# 6. ለውጥ እና መከላከል

## መግቢያ

**ፖሊስ፣ ወታደራዊ እና የፍትህ አካላትን ጨምሮ ደካማ ወይም የተጋለጡ ህዝባዊ ተቋማት ብዙውን ጊዜ ግጭት ባለባቸው ሀገራት የህግ የበላይነትን ማስከበር እና የዜጎችን መብት መጠበቅ ስለሚሳናቸው ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት እና ሌሎች ጥሰቶች የመከሰት እድልን ያባብሳሉ። እነዚህ ተቋማት ነፃነት፣ገለልትኛነት እና ተጠያቂነት ሲጎድላቸው፣ የጭቆናና የሥርዓታዊ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት መሣሪያ ሊሆኑ ይችላሉ።**

የመንግስት ተቋማት ሰብአዊ መብቶችን እንዲያከብሩ፣ የህግ የበላይነት እንዲኖር እንዲያደርጉ እና ለዜጎች ተጠያቂ እንዲሆኑ የመንግሰት ተቋማትን የመለዋወጥ ሂደት ተብሎ የሚተረጎመው ተቋማዊ ለውጥ ብዙውን ጊዜ ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ፍትህ እና ተጠያቂነትን ለማምጣት በሚደረገው ትግል ውስጥ ለሚሳተፉ ድርጅቶች ቁልፍ ዓላማ ነው። ይህ አካሄድ የማሻሻያ ተግባራት ላለፉ በደሎች ተጠያቂነት እና እርምት ከማስገኘት ባለፈ ጥሰቶቹ እንዲፈጠሩ ያስቻሉ ሁኔታዎች እንዲኖሩ አስተዋጽኦ ያደረጉ መዋቅሮችን እና አስተሳሰቦችን በማፍረስ ወደፊት የሚፈጸሙ ጥሰቶችን ለመከላከል እንደሚረዳ ይገነዘባል።

ሌላው ድርጅቶች ሊወስዱ የሚችሉት ቁልፍ እርምጃ ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ወንጀለኞችን ወንጀለኛ ለማድረግ እና ሰርቫይቨሮችን ፣ ቤተሰቦቻቸውን እና ለለውጥ የሚከራከሩትን ለመጠበቅ የህግ ማዕቀፎች እንዲሻሻሉ ሊሆን ይችላል። እንደ ሴቶች፣ ልጃገረዶች፣ መበለቶች፣ የተለያየ ወሲባዊ ዝንባሌ ያላቸው ግለሰቦች፣ የፆታ ማንነት ወይም መገለጫዎች እና የፆታ ባህሪያት (SOGIESC) እና አናሳ እና ተወላጅ ማህበረሰቦችን የመሳሰሉ የተወሰኑ ቡድኖችን አድልዎ የሚያደርጉ ህጎች ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃትን ለመፍታት የሚደረገውን ጥረት ሊያደናቅፉ ይችላሉ።



እነዚህ አድሎአዊ የህግ ማዕቀፎች ፅንስን ድህንነቱ በተጠበቀ መልኩ የማቋረጥ መብትን የሚገድቡ እና ሴቶች ለልጆቻቸው ዜግነት የመስጠት መብትን የሚከለክሉ ህጎችን በተለይም በጾታዊ ጥቃት ለተወለዱ፣ ወይም ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ጋብቻዎችን የሚከለክል ህግ አለመኖሩን ያጠቃልላል። በዚህ መንገድ አንዱ አካሄድ ደጋፊ የሆነ የሕግ ማዕቀፍን(አካባቢን)ማሳደግ ነው። በሴቶች እና ሴት ልጆች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን በሚመለከት ህግ ላይ የተደረጉ ለውጦች በጣም ውጤታማ የሆኑት ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን በመፈረም እና በማፅደቅ እንዲሁም የሴቶች መብት ተሟጋች ድርጅቶች፣ የሴቶች ንቅናቄ እና እንደ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች፣ ምክር ቤቶች እና ኮሚቴዎች ያሉ ለሴቶች ጉዳዮች የተለዩ የመንግስት ተቋማት ባሉበት መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ። ሆኖም ግን ከህጎች ሙሉ አፈፃፀም ጋር ካልተጣመረ በስተቀር ጠንካራ የህግ ማዕቀፍ መኖር ብቻውን በቂ አይደለም እንዲሁም መደበኛ ማዕቀፉ እንደ ፖለቲካዊ ፍላጎት ፣ የተመደበ በጀት ፣ የመንግስት ባለስልጣናትን አቅም ግንባታ (የህግ አስከባሪ እና ፍርድ ቤት ጨምሮ)፣ በስርዓተ-ፆታ ላይ የተመሰረቱ ጥቃቶች የተለየ የፍትህ ሂደት ፣ የሲቪል ማህበራት ክትትል እና ሃገራት ህግን ለማስፈጸም የገቡትን ቃል እንዲፈጽሙ ተጠያቂ ለማድረግ በሲቪል ማህበራት ውትወታ በማድረግ ነው።

# ድርጅቶች የሚያቀርቧቸው የግምገማ ጥያቄዎች




## ስለ ዐውዳቸው:-

**ከግጭቱ በፊት እና/ወይም በግጭቱ ወቅት የተወሰኑ ህዝቦችን በተለይ ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ወንጀሎች በተለየ መልኩ ተጋላጭ ያደረጓቸው ቀደምት መዋቅራዊ ኢፍትሃዊነት ወይም ባህላዊ ደንቦች ነበሩ?**

**የተወሰኑ ህዝቦች (ለምሳሌ፣ ዘር፣ ጎሳ፣ ወይም ሀይማኖት ቡድኖች ወይም የተወሰነ የጾታ ዝንባሌ ያላቸው ግለሰቦች) ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ወንጀሎች ኢላማ ነበሩ?**

**ከግጭቱ በፊት፣ ወሲባዊ እና ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃት (SGBV) ወንጀሎች በብሔራዊ የሕግ ሥርዓት ውስጥ ከዓለም አቀፍ መስፈርቶች ጋር በተጣጣመ መልኩ ተገልጸው እና ተፈጻሚነት ኖሯቸው ነበር?**

- ከሆነስ ወንጀሉን የፈጸሙ አካላትን አጣርቶ ለህግ ለማቅረብ በተሳካ ሁኔታ ተግባራዊ ሆነዋል?
    - ካልሆኑስ የቅጣት ተጠያቂነት እንዳይኖር የምያስቀጥሉ ዋና ዋና ነገሮች ምንድን ናቸው?

**ከተወሰነ ዳራ የመጡ ግለሰቦች ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ወንጀሎችን እንዳያመለክቱ ወይም ፍትህ እንዳይፈልጉ የሚያደርጉ ቀደም ሲል የነበሩ መዋቅራዊ ኢፍትሃዊነት ወይም የባህል ደንቦች ነበሩን ( ለምሳሌ ተመሳሳይ ጾታ ባላቸው ግለሰቦች መካከል የሚፈጸሙ ወሲባዊ ድርጊቶችን ወንጀል የሚያደርግ ሕግ ወይም የሰርቭይቨሮች መገለል)?**

**ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ወንጀሎችን ስጋት የጨመሩ ወይም የሰርቫይቨሮች ወደ ፊት እንዳይመጡ የሚከለክሉ የስጋት መንስኤዎችን ለመፍታት ወይም ፖሊሲዎችን ለመለወጥ የተደረገ ጥረት አለ?**

**ማናቸውም ወንጀለኞች ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ፈጻሚዎች በህጋዊ መንገድ (ለምሳሌ እንደ ተመረጡ ባለስልጣናት) ወይም በህገወጥ መንገድ (ለምሳሌ እንደ መንግስታዊ ያልሆኑ የታጠቁ ቡድኖች አባላት) በስልጣን ላይ አሉ?**

**ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት እና ወሲባዊ እና ፆታዊ ጥቃት ሰርቭይቨሮች ጋር አብሮ ስለመስራት እና ስለመደገፍ ስልጠና የሚያስፈልጋቸው የተለዩ ተቋማት (ለምሳሌ ህግ አስከባሪ፣ ወታደራዊ፣ የፍትህ ስርዓት) አሉ?**

**ዘመቻዎች ስለ እና ወሲባዊ እና ፆታዊ ጥቃት ግንዛቤ እንዳይጨምሩ የሚከለክሉ ልዩ ተቋማት (ለምሳሌ ትምህርት ቤቶች፣ የእምነት ተቋማት፣ ወዘተ) አሉ?**

**በመከላከል እና በማሻሻያ ላይ የሚሰሩ እርስዎ በአገር ውስጥም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ በመተባበር አብረው ሊሰሩ የሚችሉባቸው ሌሎች ድርጅቶች አሉ?**

## ለራሳቸው:-

**ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ወንጀሎችን ሊያስከትሉ የቻሉ ወይም ለማስቀረት ያልቻሉ የፖሊሲ ውድቀቶችን ወይም መዋቅራዊ ኢፍትሃዊነትን የሚፈቱ ልዩ ማሻሻያዎች እንዲደረጉ ልንወተውት እንችላለን?**

**ወንጀለኞችን ከሥልጣን የሚያስነሱ ልዩ ለውጦች እንዲደረጉ መወትወት እንችላለን?**

**እነዚህን ለውጦች ለመደገፍ ወይም ለማጽደቅ ልንተባበራቸው የምንችላቸው (ለምሳሌ፡ ሌሎች ድርጅቶች ወይም የፖለቲካ አጋሮች) አሉ?**

**አንዳንድ ሰዎችን ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ወንጀሎች ተጋላጭ ያደረጓቸውን ወይም እነሱን ሪፖርት ለማድረግ እንዲፈሩ ያደረጉ አስተሳሰቦችን ለመቀየር የግንዛቤ ማስጨበጫ ወይም ትምህርታዊ ዘመቻ ይረዳል?**

- ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ እውቀት በሌላቸው ማህበረሰቦች ውስጥ ለመስራት ምን አይነት ስልቶችን ልንከተል እንችላለን?

**የወሲባዊ እና ፆታዊ ጥቃት እና ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ሰርቭይቨሮችን የሚመለከቱ ጎጂ ባህላዊ ደንቦች ውይም አመለካከቶችን ለመከላከል በጋራ ሊሰሩ የሚችሉ ተፅዕኖ ፈጣሪዎች እና ተግባቢዎች (ለምሳሌ የሃይማኖት መሪዎች፣ ጋዜጠኞች፣ አርቲስቶች ወይም አስተማሪዎች) ጋር ለመተባበር እድሎች አሉን?**

**ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት እና የወሲባዊ እና ፆታዊ ጥቃት ሰርቫይቨሮች ጋር በሚሰሩ ቁልፍ ተቋማት ውስጥ ለግለሰቦች ስልጠና ለመስጠት አቅሙ እና እውቀቱ አለን?**

- እነዚህን ስልጠናዎች እንዲሰጡ ወይም እንዲደግፉ ልንጠይቃቸው የምንችላቸው አጋሮች አሉን?



## ለሰርቫይቨሮች፡-

**የጥበቃ ተዋናዮች የሚፈጸሙት የዓመፅ ጥቃት ምን ይመስሎታል?**

**በሃገራዊ ፖሊሲዎች፣ የህብረተሰብ ኢፍትሃዊነት ሆነ የባህል ልማዶች ውስጥ ምን አይነት ለውጦች ቢደረጉ ወደፊት ትውልዶች ተመሳሳይ ጥቃት እንዳይደርስባቸው ለመከላከል በጣም አስፈላጊ እንደሆኑ ይሰማዎታል?**

**ህብረተሰቡ ሰርቭይቭሮችን በሚንከባከብበት ወይም በሚደግፍበት መንገድ ላይ ምን አይነት ለውጦችን ማየት ይፈልጋሉ?**

**በለውጥ ሂደቶች ውስጥ እንዴት መሳተፍ ይፈልጋሉ?**

**እርስዎን ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ወንጀሎችን እንዳያመለክቱ ወይም ለማመልከት እንዲያቅማሙ ያደረግዎት ማንኛውንም ፖሊሲዎች፣ ባህላዊ አመለካከቶች ወይም ልማዶችን መጥቀስ ይችላሉ?**

# ተጨማሪ ንባብ

**በአካባቢ ደረጃ እና በሀገር አቀፍ የሽግግር የፍትህ ሂደቶች ውስጥ ተሳትፎን ለማጠናከር የባለሙያዎች መመሪያን ጨምሮ ከተሃድሶ እና መከላከል ጋር የተያያዙ ግብአቶች በመሳሪያው ተጨማሪ ንባብ ክፍል ውስጥ ይገኛሉ ::**

# 7. ማስታወሻ እና ትምህርት

## መግቢያ

**መታሰቢያ/ማስታወሻ በGIJTR ሥራ ውስጥ የግለሰቦችን ወይም ክስተቶችን ትውስታ የምንጠብቅባቸው እና እነዚያን ትዝታዎች እንደ አንድ የተለየ ማህበረሰብ፣ ክልል ወይም ሀገር ወደፊት የምናስቀጥልባቸውን በርካታ መንገዶችን በሚያጠቃልል በሰፊው መልኩ እንረዳዋለን ። ይህ እንደ ኤግዚቢሽኖች፣ ትዝታን ለማስተዋወቅ የተነደፉ የጋራ ተግባራትን፣ የተጎጂዎችን ታሪኮች የያዙ ቡክሌቶችን ማተምን፣ የቲያትር ትርኢቶችን፣ እንደገና የመቀበር ስነስረአት፣ ታሪካዊ ስፍራዎችን መጠበቅ እና አውድ መስጠት እና የማህበረሰብ የስነ ጥበብ መርሃ ግብሮች የመሳሰሉ ብዙ የተለያዩ መርሃግብሮችን እና የተለያዩ ቅርጾችን ጨምሮ ለዘለቄታው ያልተነደፉትን ሊያካትት ይችላል።**

በአሳቢነት እና በጥንቃቄ ሲያዙ የመታሰቢያ/የማስታወሻ ውጥኖች ያለፉትን ትምህርቶች ለማሰላሰል የሚያስችል ቦታን ሰጥተው ለግለሰቦች በጣም አሰቃቂ የሆኑትን ትውስታዎች ለማስታወስ እና ለማቆየት ደህንነቱ የተጠበቀ ቦታዎችን የመስጠት አቅም አላቸው።ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ፍትህን እና ተጠያቂነትን ለመፈለግ እንደ አጠቃላይ መንገድ የመታሰቢያ/ማስታወሻ ሥራ ብዙ የተለያዩ ሚናዎችን መጫወት ይችላል። የማስታወሻ/የመታሰቢያ ስራዎች ቀደም ስል የጠፉትን ወይም የተጎዱትን እያስታወሰ እየተካሄዱ ያሉ ኢፍትሃዊነቶች እና ሰርቫይቨር ፍላጎት ላየ ትኩረት እንዲኖር የማድረግ አቅም አላቸው:: ታሪኮችን ለመለዋወጥ እና የማህበረሰብ ስሜትን ለመገንባት ፈጠራ የተሞላባቸው መንገዶችን በመፍጠር በተመሳሳይ ጊዜ ሰርቫይቨሮች ራሳቸውን እና ቤተሰባቸውን ለመደገፍ ሥራ ለመስራት የሚረዳቸውን ክህሎት እንዲሰለጥኑ በማደረግ እንደ ብርድ ልብስ ሥራ እና የቅርጫት ሽመና ቴክኒኮችን በመጠቀም ሰርቫይቨሮችን የማስታወሻ/ የመታሰቢያ ስራዎች ላይ በቀጥታ የሚያሳትፉ መርሃ-ግብሮች በተለየ መልኩ ተጽኖ ሊፈጥሩ ይችላሉ።

እንደ የፍርድ ሂደቶች፣ የእውነት ኮሚሽኖች እና የማካካሻ መርሃ ግብሮች አይነት መደበኛ የሽግግር የፍትህ ሂደቶች ጎን ለጎን የማስታወሻ/የመታሰቢያ መርሃ ግብሮች ሰርቫይቨር እውቅና የማግኘት ስሜት ሊፈጥሩ ይችላሉ- ህመማቸው እውቅና እንደተሰጠው እና እነደታየ - የግድ ስላጋጠማቸው ጉዳይ በይፋ እንዲመሰክሩ ሳያስፈልጋቸው በጉዳያቸው ላይ የህዝብ ድጋፍ ለመገንባት ያስችላል:: የማስታወሻ/ የመታሰቢያ አንዱ ጥንካሬ በርካታ እና ብሎም እርስ በርስ የሚጋጩ አመለካከቶች ጎን ለጎን እንዲኖሩ እና በፍርድ ሂደት ወይም በእውነት ኮሚሽን ጠንከር ባሉ ገደቦች ውስጥ የማይገቡ አስተያየቶች እና ትርክቶች እንዲኖሩ ማድረጉ ነው። በመጨረሻም እንደ ‘ቦዲ ማፒንግ’ ያሉ ፈጠራ የተሞላባቸው አሳታፊ ሂደቶች ከፍትህ ስሜት ጋር ሊመሳሰሉ የሚችሉ ለሰርቫይቨር በግለሰብ ደረጃም ሆነ በማህበረሰብ ደረጃ የረዥም ግዜ ፈውስ አስተዋትዖ በማድረግ የማፅዳት አቅም ይኖራቸዋል::

በተመሳሳይ ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃትን ጨምሮ ያለፉ ግጭቶች እና የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ላይ የሚያተኩሩ ትምህርታዊ መርሃግብሮች የግጭቶችን መሰረታዊ መንስኤዎች ለመፍታት ይችላሉ፤ መዋቅራዊ እኩልነት ላለመኖር መሰረት የሆኑ በስርዓተ ጾታ፣ በዘር ወይም በብሔር ላይ የተመሰረቱ ጎጂ አመለካከቶችንም ያፈርሳሉ። እንደ ሀገር አቀፍ ሥርዓተ ትምህርትም ሆነ በሲቪል ማህበራት የሚመራ የሰብአዊ መብቶችን ባህል ለማሳደግ ያለመ መደበኛ ያልሆነ መርሃግብር ትምህርታዊ ስራዎች ወጣቶች እርስ በርስ የሚጋጩ መረጃዎችን እንዲገመግሙ የሚያስችል ክህሎት እና ከጎጂ አባታዊ ደንቦች ይልቅ በእኩልነት ስሜት የተመሰረቱ ባህሪያትን እንዲለማመዱ ያስችላቸዋል።



# ድርጅቶች የሚያቀርቧቸው የግምገማ ጥያቄዎች

## ስለ ዐውዳቸው:-

**አሁን ያለው የመታሰቢያ ገጽታ ምንድን ነው?**

- ምን ዓይነት መታሰቢያዎች ወይም ትውስታዎች አሉ?
- የማንን ታሪኮች ይናገራሉ? የማን ታሪኮች ቀርተዋል?
- በብሔራዊ፣ በክልል እና በአካባቢ ደረጃ የተለያዩ ታሪኮች ይነገራሉ? በተለያዩ ማህበረሰቦች መካከል?
- ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ተጠቂዎች እና ሰርቫይቨር ታሪኮች በማንኛውም የመታሰቢያ/የማስታወሻ ስራዎች ውስጥ ተካተዋል?
- ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ተጠቂዎች እና ሰርቫይቨር መካከል የአንዳንዶች ታሪክ ከሌሎች በበለጠ ይነገራል (ለምሳሌ፣ ከተለያዩ ዘር፣ ብሔር፣ ሀይማኖት ወይም ጾታዎች የመጡ)?
- ሚዲያ ከ ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ጋር የተያያዘ ማስታወሻ ግንባታ ረገድ ምን ሚና ይጫወታል?
  - ይህ ግንባታ የሰርቫይቨሮችን ተሞክሮዎች ያሳያል?
  - ማንኛውም የሰርቫይቨር ቡድኖች እንዳይታዩ ተደርገዋል?
- የትኞቹ ማህበረሰቦች በማስታወሻ/መታሰብያ ስራዎች ላይ ትኩረት ተደርጎባቸዋል? የትኞቹ ናቸው የተገለሉ ወይም ተደራሽነት ያላኙት?
- የማስታወሻ/መታሰብያ ስራዎቹ የታቀዱት ታዳሚዎች ማን ናቸው (ለምሳሌ የውጭ ቱሪስቶች፣ የሀገር ውስጥ ቱሪስቶች፣ ማህበረሰቡ)?

**ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ወንጀል የተፈፀመባቸው ቦታዎች አሉ?**

- የሲቪል ማህበራት ወይም ሰርቫይቨር ቡድኖች ወደነዚህ ቦታዎች መሄድ ይችላሉ?

**ለምሳሌ በጭቆና፣ በቀል፣ ማግለል፣ ወዘተ ምክንያት ሰርቫይቨሮች እና/ወይም የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች መታሰቢያ/ማሰታወሻ በመፈለጋቸው ማንኛውንም ስጋቶች ያጋጥሟቸዋል?**

**ተማሪዎች በመደበኛ የትምህርት ሥርዓት ውስጥ ስለግጭቱ ምን እየተማሩ ነው?**

- የግጭቱን የምያስቀጥሉ እና ተፅእኖዎች የሚዳስሱ መደበኛ ያልሆኑ የትምህርት መርሃግብሮች አሉ?
- ከእነዚህ መርሃግብሮች ውስጥ መደበኛ ወይም መደበኛ ያልሆነ ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ወንጀሎችን ይመለከታሉ?

**ወሲባዊ እና ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ወይም ጎጂ የሥርዓተ-ፆታ ደንቦችን የሚመለከቱ የሰብአዊ መብቶች ማዕቀፍ ውስጥ የሚመለከቱ ትምህርታዊ መርሃግብሮች አሉን?**

**ለውትወታ ልንጠቀምባቸው የምንችላቸው የመታሰቢያ ቀናት አሉ (ለምሳሌ፣ ዓለም አቀፍ ቀናት፣ ብሔራዊ ቀናት ወይም እውቅና ያልተሰጣቸው)?**

## ለራሳቸው:-

**አዳዲስ እይታዎችን በማካተት ወይም እውቅና ያልተሰጣቸውን ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ተጎጂዎች እና ሰርቫይቨሮችን ታሪክ በማጋራት የመታሰብያ/ማስታውሻ ገፅታ ላይ አስተዋፅዎ የምናደርግባቸው መንገዶች አሉን?**



### የዓመፅ ድርጊቶችን ብቻ ሳይሆን የመትረፍ፣ የመቋቋም እና ጽናትን ማስታወስ/ማሰብን እንዴት ልናበረታታ እንችላለን?

- ይህ በተጎዳ ማህበረሰብ ውስጥ የተፈጠረውን አለመተማመን እና ስጋት ለመዋጋት እንዴት መጠቀም ይቻላል?

### ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ሰርቫይቨሮች በማህበረሰባችን ውስጥ በሚደረገው የመታሰቢያ/የማስታወሻ ሥራ ላይ እንዲሳተፉ ጊዜው ትክክል ይሆናል?

ከሆነ፡-

- ግቡ(ግቦቹ) ምን ይሆናሉ? ለሰርቫይቨሮች እውቅና የማግኘት ስሜትን ለመፍጠር? ስለተፈጸሙ ጥሰቶች ግንዛቤ ለማስጨበጥ? ለሐዘን ወይም ለፈውስ ቦታ ለመስጠት? ጎብኝዎችን ሰለ ግጭት መሰረታዊ መንስኤዎች ለማስተማር?
- ሰርቫይቨሮች በመርሃግብሩ ንድፍ እና ትግበራ ወቅት እንዴት ማሳተፍ እና ትርጉም ባለው መልኩ ማማከር ይቻላል?
- ለመታሰቢያ/ማስታወሻ መርሃግብራችን በጣም ተስማሚ የሆነው መገናኛ መንገድ የትኛው ነው? እኛ ዒላማ ለማድረግ ያሰብነውን ተመልካቾችን የሚስብ ልዩ አቀራረብ ወይም ሰርቭይቭሮች መታሰቢያውን በመፍጠር በንቃት እንዲሳተፉ እና በግንባታው ላይ የኩራት ስሜት እንዲሰማቸው የሚያስችል የፈጠራ መንገድ አለ?
- እርስ በርሱ የሚጋጩ ትርክቶችን እንዴት እንይዛቸዋለን - የመታሰቢያ መርሃግብሩን በመፍጠር ሂደት ውስጥ ወይም ለሕዝብ ከተከፈተ በኋላ?



- ከሰርቫይቨር ጋር ባለን ግንኙነት ስለግጭቱ እና ስለ ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ወንጀሎች ትምህርት በአዎንታዊ መልኩ ማበርከት እንችላለን?
- ልንተባበራቸው የምንችላቸው አስተማሪዎች ወይም የትምህርት ድርጅቶች/ተቋማት አሉ?
- ሰርቫይቨሮች የትምህርት ይዘትን መልእክት እና ንድፍ በመቅረጽ ረገድ ሚና የሚጫወቱት እንዴት ነው?
- በትምህርታዊ ወይም በመታሰቢያነት ተነሳሽነት ውስጥ ሌሎች ምን አይነት ግብአቶች/ባለስልጣኖች (ለምሳሌ የታሪክ ምሁር፣ የሥርዓተ-ትምህርት ዲዛይነር፣ አርቲስት፣ ወዘተ) ውስጥ መሳተፍ ያስፈልጋቸዋል?

## ለሰርቫይቨሮች፡-

### መጪው ትውልድ ስለዚህ ግጭት እና ስለተከሰተው ግጭት ምን እንዲማር ወይም እንዲያስታውስ ይፈልጋሉ?

### ከዚህ በፊት በማስታወሻ/የመታሰቢያ ወይም በትምህርታዊ ሥራ ላይ ተሳትፈዋል?

ከሆነ፡-

- ስለ መርሃግብሩ (መርህግብሮቹ) ምን አድንቀዋል?
- በተለየ ሁኔታ ምን ሲደረግ ማየት ይፈልጋሉ?
- ታሪክዎን ለማጋራት ሊሰሩባቸው የሚችሉ የሚፈልጉዋቸው የተለዩ መንገዶች አሉ (ለምሳሌ ፊልም፣ ዘፈን፣ ዳንስ፣ ቲያትር፣ የእጅ ስራ ወይም የእይታ ጥበብ)?

## ተጨማሪ ንባብ

**ከለውጥ እና መከላከል ጋር የተያያዙ ግብዓቶች አጠቃላይ “ከማስታወስ ወደ ድርጊት” (Memory to Action) የመሳሪያ ጥቅል ጨምሮ በመሳሪያው ተጨማሪ ንባብ ክፍል ውስጥ ይገኛሉ።**

# ፰. ማህበረሰብ እና አንድነት



## መግቢያ

**ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ሰርቫይቨር ኔትወርኮች ሰርቭይቨሮች ታሪካቸውን ከሌሎች በተመሳሳይ ሁኔታዎች ውስጥ ያለፉ ሰዎች ጋር እንዲያጋርሩ እና ጥረቶቻቸውን በማጣመር የበለጠ ተፅኖ ለመፍጠር እንዲችሉ የእምነት እና የእንክብካቤ ግንኙነቶችን በማጎልበት ወሳኝ ድጋፍ ይሰጣሉ። የእነዚህ ኔትወርኮች መፈጠር እና ጥገና ግን ሁልጊዜ ቀላል አይደለም። ለእናቶች፣ ለአባቶች፣ ወንድ ልጆች፣ ሴት ልጆች፣ አጋሮች፣ ባለሙያዎች እና የተለያዩ የባህል እና የኃይማኖት ዳራዎች ላላቸው ግለሰቦች፣ አንዳንዶቹ እራሳቸውን ተጎጂ ወይም ሰርቭይቨር እንደሆኑ ሊገልጹ ይችላሉ፣ ሌሎች ደግሞ በተለያዩ ምክንያቶች እንዲህ ያለውን መለያ ሊቃወሙ ይችላሉ። ብዙዎች ሰርቭይቨር መሆናቸውን የምያወሳስቡ ሌሎች የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች አጋጥሟቸው ይሆናል ሌሎች ደግሞ ከወሲባዊ ጥቃት ጋር ተያይዞ የሚመጣውን መገለል ለማስወገድ ይፈልጉ ይሆናል። በሰርቭይቨሮች መካከል በብሔር ወይም በሃይማኖት ማንነት ላይ የተመሰረተ ወይም ከግብአት እጥረት እና በቡድኖች መካከል ካለው የፉክክር ስሜት የመነጨ መከፋፈል ሊኖር ይችላል። በነዚህ ሁሉ ምክንያቶች፣ ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት እና ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃት ሰርቫይቨር ኔትወርኮች በአወቃቀራቸው በእጅጉ ይለያያሉ; እንዲሁም ብዙውን ጊዜ መጀምርያ በሌላ መልክ ይፈጠራሉ ይህም ለምሳሌ ከአንድ አንድ የተወሰነ ማህበረሰብ የተውጣጡ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ሰርቭይቭሮች ጥምረት ወይም የጋራ የአእምሮ ጤና እና የስነ-ልቦና-ማህበራዊ ድጋፍ ተግባራት ላይ የተሰማራ ቡድን አባሎቻቸው ወሲባዊ ጥቃትን እንደ ተልእኳቸው አካል ወይም የተቋቋሙበት ምክንያት ብለው ለመቀበል አባሎቻቸው ምቾት ሳይሰማቸው በፊት ሊሆን ይችላል።**

ሆኖም ግን እነዚህ ኔትወርኮች አንዴ ከተመሰረቱ ከወሲባዊ ጥቃት ወይም ሰርቭይቭሮች ወይም ሰፋ ያለ ስልጣን እና ኃላፊነት የዝምታ፣ የስሜት ቀውስ እና ራስን መወንጀል አዙሪቶችን ለመስበር ወሳኝ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ። አባሎቻቸው ያጋጠሟቸውን ጥሰቶች መሰረት የሆኑ ሰፊ መዋቅራዊ እኩልነት አለመኖርን እንዲገነዘቡ በመርዳት እና በፈውስ ተግባራት እና የጋራ ስራዎች ላይ እንዲሳተፉ በማድረግ የሰርቫይቨር ኔትወርኮች ለአባሎቻቸው የሞራል ድጋፍ እና የአብሮነት ስሜት ሊሰጡ ይችላሉ - ይህ እርዳታ በተለይ በቤተሰባቸው፣ በጓደኞቻቸው ወይም በሰፊው ማህበረሰብ መገለል ወይም ዝም እንዲሉ በተገደዱ ግለሰቦች በተለይ ሊደነቅ ይችላል።ለአባሎቻቸው ጥረታቸውን የሚያስተባብሩበት እና የጋራ ግቦችን እንዲያሳድጉ መድረክን በመፍጠር የሰርቭይቨር ኔትወርኮች የየራሳቸውን አባላት ድምጽ ማጉላት እና የውትወታ እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ጥረቶቻቸውን ውጤታማነት ማሳደግ ይችላሉ። እነዚህ ድርጅቶች በዓለም አቀፍ፣ በሀገር አቀፍም ሆነ በክልል ደረጃ የሚንቀሳቀሱ የተገለሉ ወይም የተጣሉ ግለሰቦችን በስልጣን ላይ ካሉት ጋር ያገናኛሉ። ጥንካሬያቸው የሚመነጨው ከሰርቫይቨሮች ጥምረት በመሆኑ እነዚህ ኔትወርኮች ከየትኛውም የውጭ አካል አቅም በላይ በረዥም ጊዜ ውስጥ የሰርቭይቭሮችን ፍላጎት ለመሙላት በመስፋት እና በመቀያየር የመቀጠል አቅም አላቸው።

# ድርጅቶች የሚያቀርቧቸው የግምገማ ጥያቄዎች

## ስለ ዐውዳቸው:-

**በሀገራችን/ክልላችን/ማህበረሰባችን ውስጥ የወሲባዊ ጥቃት ሰርቫይቨሮች ኔትወርኮች አሉ?**

o ከሆነ:-

- ከእነዚህ ኔትወርኮች መካከል ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ላይ የሚያተኩሩ አሉ?
- ከእነዚህ ኔትወርኮች መካከል በሌሎች የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ላይ የሚያተኩሩ አሉ?
- ኔትወርኮች ከተለያዩ ዘር፣ብሔር፣ ኃይማኖት እና የጾታ ማንንነት ያላቸው ሰርቫይቨሮችን ያካተቱ ናቸው ወይስ የተገለሉ ቡድኖች አሉ?
- በተለምዶ ምን ዓይነት ሥራ ወይም ተግባር ይሠራሉ?
- እነዚህ ኔትወርኮች ምን ሚና ይጫወታሉ?
  - ለፍትህ እና ተጠያቂነት፣ እውነትን ይፋ ለማድረግ፣ ማካካሻ ወይም ለሌሎች የሽግግር የፍትህ ስልቶች ውስጥ ምን ሚና ይጫወታሉ?
- ከእነዚህ ኔትወርኮች በሃገር ውስጥ ባለሥልጣናት እውቅና አግኝተዋል?
- ኔትወርኮቹ ከማንኛውም የውጭ ምንጮች ድጋፍ ያገኛሉ (ለምሳሌ ለጋሾች፣ ዓለም አቀፍ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የሲቪል ማህበራት፣ ወዘተ)?

ካልሆነ:-

- ሰርቫይቨሮች ኔትወርኮች እንዳይቀላቀሉ ወይም እንዳይፈጥሩ የሚከለክሉት ዋና ዋና እንቅፋቶች ምንድን ናቸው (ለምሳሌ፣ የግባት እጥረት፣ የመገለል ፍርሃት፣ ከተለያየ ዳራ የመጡ ሰርቫይቨሮች መካከል ያለ መከፋፈል፣ ወዘተ.)?

o ብዙ ኔትወርኮች ካሉ:-

- ኔትወርኩቹን ምን ይለያቸዋል (ለምሳሌ በተለያዩ ጂኦግራፊያዊ ክልሎች ላይ ያተኮረ ከተለያዩ ሃይማኖቶች ለመጡ ሰርቫይቨሮች ወዘተ)?
- እነዚህ ኔትወርኮች በማንኛውም መንገድ ይገናኛሉ ወይም ይተባበራሉ?
  - በእነዚህ ኔትወርኮች መካከል ትብብር ለመፍጠር ምን ተግዳሮቶች እና እድሎች አሉ?

## ለራሳቸው:-

**በመርሃግብራችን አማካኝነት ግንኙነትን፣ ማህበረሰብ መገንባት እና የሰርቫይቨሮችን የአብሮነት ስሜት በተሻለ መደገፍ የምንችልባቸው መንገዶች አሉ?**

**በመርሃግብራችን አማካኝነት በሰርቫይቨሮች መካከል የውድድር ስሜት ወይም ያለመተማመንን የምናደርግባቸው መንኛውም መንገዶች አሉ?**

**ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ሰርቫይቨሮችም ተለይቶም ሆነ ወይም በአጠቃላይ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ሰርቫይቨሮች የሰርቫይቨሮች ኔትወርክ ወይም በርካታ ኔትወርኮች ካሉ ከእነሱ ጋር የምንተባበርበት፣ በመርሃግብራችን የምንደግፍበት ወይም የጋራ የፍላጎት ነጥቦች የምንፈልግባቸው መንገዶች አሉ ?**

**ኔትወርኮች ከሌሉ ሰርቫይቨሮች እንዳይደራጁ እየከለከሏቸው ሊሆኑ የሚችሉ እንቅፋቶች መፍታት የምንችልባቸው መንገዶች አሉ?**

## ለሰርቫይቨሮች፦

**ከከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ሰርቫይቨሮች ኔትወርክ ወይም የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ሰርቫይቨሮች ኔትወርክ አባል ነዎት?**

ከሆነ፦

- ኔትወርኩ በሕይወትዎ ውስጥ ምን ሚና ይጫወታል? የኔትወርኩ አባል በመሆንዎ ምን ያደንቃሉ?
- የእርስዎ ኔትወርክ የተደራጀው እንዴት ነው? ለምሳሌ አባላቱ በግለሰብ አባላት ወይም ድርጅቶች ናቸው?
- የኔትዎርክ አባል በመሆንዎ ምን ምን ያደንቃሉ?
- መለወጥ የሚፈልጋዋቸው የኔትወርኩ ገጽታዎች አሉ?
- የእርስዎ ኔትዎርክ ምን ተግባራትን ያከናውናል? የእርስዎ ኔትዎርክ ሰርቫይቨሮች ሁለንተናዊ ፍትህ እና ተጠያቂነት እንዲያገኙ እንዴት ይደግፋል?
- ከሰርቫይቨሮች ጋር ለመተባበር ወይም ለመሥራት የሚፈልጉባቸው ሌሎች መንገዶች አሉ?

ካልሆነ፦

- ኔትወርክ ለመቀላቀል ወይም ለመመሥረት ፍላጎት አለዎት?
- ኔትወርክ የመቀላቀል ጠቀሜታ ይታይዎታል?
- በማኅበረሰባችሁ ውስጥ የሰርቫይቭሮች ኔትወርክ ምን ሊያደርጉ ወይም ሊሠሩ ይችላሉ ብለው ያስባሉ?
- ከዚህ ቀደም ኔትወርክን ከመቀላቀል ወይም ከመፍጠር የከለከለዎት ነገር አለ?

# ተጨማሪ ንባብ

**ከማህበረሰብ እና ከአብሮነት ጋር የተያያዙ ግብዓቶች በመሳሪያው ተጨማሪ ንባብ ክፍል ውስጥ ይገኛሉ። የሰርቫይቨር ኔትወርክ ለመመስረት ፍላጎት ያላቸው ድርጅቶች ወይም የግለሰቦች ቡድኖች የ"ስድስት የማሰብያ ኮፍያዎች" ተግባ አንዳንድ የተለያዩ ጥቅሞችን እና ተግዳሮቶችን ለመዳሰስ ጠቃሚ ሆኖ ሊያገኙት ይችላሉ።**

# ተጨማሪ ንባብ

# 1. እራስን ማንጸባረቅ, ትንተና እና የአእምሮ ማጎልበት መሳሪያዎች

## 0.1 የራስ ግምገማ ለማካሄድ ምሳሌ አጀንዳ

### ዓላማዎች፡-

- በዐውዳችን ውስጥ የሰርቫይቨሮችን ፍላጎቶች ምን ያህል እየተሟሉ እንደሆነ እና እነዚህን ፍላጎቶች በበለጠ ለማርካት ያለውን ተግዳሮቶች እና እድሎች ለመገምገ።
- ለሰርቫይቨሮች ፍላጎት ምን ያህል ምላሽ እየሰጠን እንዳለን ለመገምገም እና በመርሃግብሮቻችን እና በስልቶቻችን ውስጥ ሰርቫይቨሮችን ያማከለ አካሄድ ተግባራዊ ለማድረግ።
- ሰርቫይቨሮችን ያማከለ አካሄድ ለመተግበር እና የሰርቫይቨሮችን ፍላጎት ለሟሟላት ክፍተቶች፣ ተግዳሮቶች እና እድሎች ምን ያህል ሰርቫይቨሮች የራስ ግምገማ የሚያንፀባርቁ መሆናቸውን ለመገምገም።
- ለችግሮች፣ ተግዳሮቶች እና እድሎች ምላሽ ለመስጠት ነባር መርሃግብሮችን ለማስፋፋት ወይም አዳዲስ ለማስጀመር እንችል እንደሆነ ለመመርመር እና የተረጂዎችን ፍላጎት በበለጠ ሁኔታ ለማሟላት።

### አጀንዳ፡-

**ቀን አንድ**

| ሰዓት | ክፍለ ጊዜ |
|---|---|
| 9:00 – 9:45 | መክፈቻ እና እንኳን ደህና መጡ መልእክት<br>• የአጀንዳ አጠቃላይ እይታ<br>• መግቢያዎች<br>• መሰረታዊ ህጎች እና ሎጅስቲክስ<br>• አእምሮን/ሃሳብን ለመሰብሰብ የሚያስችል ልምምድ |
| 9:45 – 12:45 | የስራ ክፍለ ጊዜ፦ **ስነ-ምግባር እና መልካም ተሞክሮዎች** |
| 12:45 – 13:45 | ምሳ |
| 13:45 – 16:45 | የስራ ክፍለ ጊዜ፦ **አጠቃላይ የድጋፍ አገልግሎቶች** |
| 16:45 – 17:00 | ቀን 1 ማጠቃለያ እና መዝጊያ |

**ቀን ሁለት**

| ሰዓት | ክፍለ ጊዜ |
|---|---|
| 9:00 – 9:45 | መክፈቻ እና እንኳን ደህና መጡ መልእክት<br>• የቀን 1 ነጸብራቆች<br>• አእምሮን/ሃሳብን ለመሰብሰብ የሚያስችል ልምምድ |
| 9:45 – 12:45 | የስራ ክፍለ ጊዜ፦ **እውነትን ይፋ ማድረግ እና ሰነዳ** |
| 12:45 – 13:45 | ምሳ |
| 13:45 – 16:45 | የስራ ክፍለ ጊዜ፦ **ፍትህ እና ተጠያቂነት** |
| 16:45 – 17:00 | ቀን 2 ማጠቃለያ እና መዝጊያ |

ተጨማሪ ንባብ

## ቀን ሶስት

| ሰዓት | ክፍለ ጊዜ |
|---|---|
| 9:00 – 9:45 | መክፈቻ እና እንኳን ደህና መጡ መልእክት<br>• የቀን 2 ነጸብራቆች<br>• አእምሮን/ሃሳብን ለመሰብሰብ የሚያስችል ልምምድ |
| 9:45 – 12:45 | የስራ ክፍለ ጊዜ፦ **ማካካሻ** |
| 12:45 – 13:45 | ምሳ |
| 13:45 – 16:45 | የስራ ክፍለ ጊዜ፦ **ለውጥ እና መከላከል** |
| 16:45 – 17:00 | ቀን 3 ማጠቃለያ እና መዝጊያ |

## ቀን አራት

| ሰዓት | ክፍለ ጊዜ |
|---|---|
| 9:00 – 9:30 | መክፈቻ እና እንኳን ደህና መጡ መልእክትe<br>• የቀን 3 ነጸብራቆች<br>• አእምሮን/ሃሳብን ለመሰብሰብ የሚያስችል ልምምድ |
| 9:30 – 12:30 | የስራ ክፍለ ጊዜ፦ **ማስታወሻ እና ትምህርት** |
| 12:30 – 13:30 | ምሳ |
| 13:30 – 16:00 | የስራ ክፍለ ጊዜ፦ **ማህበረሰብ እና አብሮነት** |
| 16:00 – 17:00 | ስለ ቁልፍ መንገዶች፣ ድርጊቶች እና ቀጣይ እርምጃዎች ውይይት |
| 13:45 – 16:45 | Working Session: **Justice and accountability** |
| 16:45 – 17:00 | Day 2 Wrap-Up and Closing |



## 1.2 ለቡድን ስብሰባዎች የታለሙ አእምሮን/ሃሳብን ለመሰብሰብ የሚያስችሉ ልምምዶች፦

የመገምገሚያ መሳርያው ከሚነካቸው ጉዳዮች ባህሪ ምክንያት ራስን መገምገም ስሜትን የሚያዳክም ወይም ከባድ ሊሆን ይችላ፤ በተለይም ተገምጋሚዎቹ ከግጭት ጋር የተያያዙ ወሲባዊ ጥቃቶች ሰላባ ሲሆኑ ወይም በሌላ መንገድ በግጭት የተጎዱ ግለሰቦች ይህ አይነቱ ግምገማ ከባድ ሊሆንባቸው ይችላል። ለድርጅቶች ወይም ለጣምራ ድርጅቶች ቡድኖች የእራስ ግምገማ ሲያካሂዱ የተሳታፊዎችን ደህንነት በመደገፍ ላይ መሰረት ያደረገ መሆኑ አስፈላጊ ነው። በክፍለ-ጊዜዎች ውስጥ የሃሳብ መሰብሰቢያ ልምምዶችን መጠቀም ከተሳታፊዎች ጋር ጥልቅ የሆኑ ግንኙነቶችን ለመፍጠር፣ ተመስጦ የተሞላበት ክፍለ ጊዜዎችን ለማከናወን እና ጠንካራ መስተጋብር ለመፍጠር ጥሩ መንገድ ነው። በክፍለ-ጊዜው መጀመሪያ ላይ የሃሳብ መሰብሰቢያ ልምምዶችን ማካተት ለተሳታፊዎች የመረጋጋት እና የመዝናናት ስሜትን ሊያላብስ ይችላል ወይም ስራ በበዛበት ቀን መካከል የቡድኑን መነቃቃት ሊያድስ ይችላል። እራስን መገምገም በሚያደርጉበት ጊዜ ለመጠቀም ወይም ለመለማመድ አንዳንድ ምሳሌዎች ከዚህ በታች አሉ።

### ለክፍለ ግዜዎቹ ፍላጎቶችን/አላማዎችን ማስቀመጥ

ከራስ ግምገማው የተፈለገውን ውጤት ለማግኘት በሚከናወነው ተግባር ላይ ያሉ ተሳታፊዎች ስለ አላማዎች እና የተፈለገውን ውጤት ግልጽ ግንዛቤ ሊኖራቸው ይገባል። ቀደም ሲል የሚታየው ምሳሌ አጀንዳ እራስን ለመገምገም የተጠቆሙ ዓላማዎችን ያካትታል። ግልጽ ዓላማዎች ከመያዝ በተጨማሪ፣ ለክፍለ-ጊዜዎች ዓላማዎችን ማዘጋጀት ተሳታፊዎች ጠለቅ ብለው እንዲያስቡ እና ግላዊ እና የጋራ ተመስጦን ለማምጣት ይረዳል።

ተሳታፊዎች እንዲያሰላስሉ እና ለክፍለ-ጊዜው ያላቸውን የግል አላማ እንዲለዩ ያበረታቷቸው። ለምሳሌ፣ አንድ ተሳታፊ፣ “ዓላማዬ ከልምዳቸው ለመማር የሌሎችን አስተዋጾ በጥልቅ ማዳመጥ እና በግልፅ የማላውቃቸውን ጉዳዮች ማብራሪያ ለመጠየቅ ላለመፍራት ነው” ብሎ ሊያስብ ይችላል።

የቡድኑን ቆይታ የበለጠ ውጤታማ ለማሳድረግ ለክፍለ-ጊዜው የቡድን/የጋራ ዓላማ ማዘጋጀትን ያስቡበት። ይህ የቡድን አላማ “የእኛ የጋራ አላማ አንድነታችንን አጠናክረን ፣ የትኩረት እና ርህራሄ ስሜትን በማዳበር ክፍለ ግዜውን መጨረስ ነው” አይነት ሊሆን ይችላል።

ግላዊ እና የቡድን አላማዎችን በማጥራታቸው ተሳታፊዎች በክፍለ ጊዜው ውስጥ ጥልቅ የሆነ የግንኙነት እና የዓላማ ስሜትን ማዳበር ይችላሉ። ይህ አንድ የሚያደርጋቸው ዓላማዎች፣ “የእኛ የጋራ ሀሳባችን በአንድነት ጊዜያችን የመገኘት፣ በትኩረት እና ርህራሄ ስሜትን ማዳበር ነው” አይነት ሊሆን ይችላል።

## በጥልቅ ለመተንፈስ የደረጃ በደረጃ መመሪያ

በጥልቅ የመተንፈስ ተግባር በጣም ጠንካራ ዘና የማለት መንገድ ሲሆን የአንድን ሰው የነርቭ ስርዓት ለመቆጣጠር እና ከሰውነት ጋር ያለውን ግንኙነት ለማጠናከር የሚረዳ ዘዴ ነው። ይህንን ልምምድ ወደ ክፍለ ጊዜዎ በማካተት ተሳታፊዎች የበለጠ ተመስጦ ያለበትን ሁኔታ በመፍጠር ተሳታፊዎች የበለጠተጠቃሚዎች የሚሆኑበትን ሁኔታ መፍጠር ይችላሉ።

- ተሳታፊዎችን ዘና እና ቀጥ ብለው ተመቻችተው እንዲቀመጡና አንድ እጃቸውን ደረታቸው ላይ ሌላውን በሆዳቸው ላይ እንዲያደርጉ ይጋብዙ።
- በአፍንጫቸው ጥልቅና ቀስ ብለው ትንፋ ለአምስት ሰከንድ እንዲወስዱ እዘዛቸው፣ አየሩ ሆዳቸውን እንዲሞላ በማድረግ በሆዳቸው ላይ ያለው እጅ ከፍ እንዲል ያድርጉ፣ በተመሳሳይ ሰዓት ደረታቸው ላይ ያለው አንድ እጃቸው እዛው ይቆይ።
- ትንፋሽ ስበው ከፍተኛ ደረጃ ላይ ሲደርሱ የመረጋጋት እና የመዝናናት ስሜትን በመጠበቅ ለአምስት ሰከንዶች ያህል ትንፋሽን እንዲይዙ ይጠይቋቸው።
- አየሩን ቀስ በለው በአፋቸው በኩል በአምስት ሰከንዶች ውስጥ ያስወጡ፣ በዚህ ጊዜ በሆዳቸው ላይ ያለው እጃቸው ዝቅ እያለ አየሩ ሲወጣ እንዲታወቃቸው ምራቸው።
- ትንፋሹን አስወጥተው ከጨረሱ በኋላ ሂደቱን እንደገና ከመጀመራቸው በፊት ቆም እንዲሉ እና ትንፋሻቸውን ለአምስት ደቂቃ እንዲይዙ አበረታቷቸው።
- በዚህ የአተነፋፈስ ስርዓት ውስጥ ተሳታፊዎች ለበርካታ ዙር እንዲፈፅሙት ያድርጉ፣ ይህም እራሳቸውን በሚያረጋጋ የትንፋሽ ዜማ ውስጥ ሙሉ በሙሉ እንዲመሰጡ ያደርጋቸዋል።

### እንቅስቃሴ እና የሰውነትን ግንዛቤ፦

በተለይ ተሳታፊዎች ረዘም ያለ ጊዜ ተቀምጠው በሚያሳልፉበት ጊዜ ስብሰባዎችን በእንቅስቃሴዎች እረፍት መደገፍ ጠቃሚ ነው።

- የቡድኑ አባላት እንዲቆሙ፣ ዓይኖቻቸውን እንዲጨፍኑ እና ትንሽ ጊዜ ወስደው በጥልቀት ትንፋሽ እንዲያስገቡ እና እንዲያስወጡ ያድርጉ፣ በተመሳሳይ ግዜም ቡድኑ በአካላዊ ስሜታቸው ላይ በማተኮር አካላቸውን እንዲያዳምጡ ያድርጉ። የመንቀሳቀስ ችግር ላጋጠማቸው የቡድኑ አባላት፣ ወንበራቸው ላይ እንዲመቻቸው እና ከዚያ ሆነው በአተነፋፈስ ላይ እንዲያተኩሩ አበረታቷቸው።
- የሚሰሙዋቸውን ስሜቶች ያዳምጡ(ትኩረት ይሰጡ) ዘንድ ያበረታቱዋቸው፣ ስሜቶቹ አዎንታዊም ይሁኑ አሉታዊ ቢሆኑ ያለምንም ፍርድ ይመልከቱ። የሰውነታቸው ሁኔታ በጥሞና ማሰላሰሉ ተሳታፊዎች የበለጠ ሃሳባቸው እንዲሰበሰብ እና ትኩረት እንዲያገኙ ይረዳቸዋል።



- በመጨረሻም፣ መተንፈሳቸውን በሚቀጥሉበት ጊዜ፣ ለቀሪው ክፍለ ጊዜ ለማስቀጠል የሚፈልጉትን ዓላማ ግምት ውስጥ በማስገባት የአዕምሮ "ዳግም ማስጀመር" እንዲያደርጉ ይጋብዙ። ይህ አጭር የእንቅስቃሴ እና የአላማ ማስተካከል እንቅስቃሴ ተሳታፊዎችን ክፍለ-ጊዜው ሲቀጥል ትኩረታቸውን እና ተሳትፏቸውን ማነቃቃት ይችላል።

## 1.3 ጥንካሬዎች፣ ድክመቶች፣ እድሎች እና ስጋቶች መተንተኛ መሳሪያ

የጥንካሬዎች፣ ድክመቶች፣ እድሎች እና ስጋቶች ትንተናዎች(የ ጥ.ድ.እ.ስ. ትንተና ወይም SWOT Analysis) ለተቋማት ስላጋጠማቸዉ ጉዳዮች ግልጽ የሆነ እይታ እና አሁን ላይ ያሉ ስልቶች እንዴት እየሰሩ እንደሆነ ግንዛቤ ለመስጠት ይረዳል። የ SWOT ትንተና ማካሄድ የድርጅቱን ጥንካሬዎች፣ ድክመቶች፣ እድሎች እና ስጋቶች ለማወቅ ይረዳል። የ SWOT ትንታኔን ማካሄድ ጠቃሚ ሊሆን የሚችልባቸው ሁኔታዎች፣ የአዲስ መርሃግብር ዝግጅትን፣ የጉትጎታ ዘመቻ ስኬትን መገምገምን ወይም በድርጅቱ ውስጥ የሥልጠና ፍላጎቶችን መለየትን ሊያካትቱ ይችላሉ።

### የ ጥ.ድ.እ.ስ. (SWOT ) ትንተና




ተጨማሪ ንባብ

**የ ጥ.ድ.እ.ስ. (SWOT )ትንተና የሚከናወንበት ተግባራዊ መመርያዎች፦**

በእቅድ አዉደ ጥናት ዉስጥ፣ ከላይ የተመለከቱት መደበኛ አብነቶች/እስታንዳርድስ ለጋራ የአእምሮ ማጎልበቻ ሲባል በ አራት ትላልቅ የመገለጫ ቻርቶች ወይም የፒን ቦርዶች ሊከፈሉ ይችላሉ።


- **ጥንካሬዎች** ግቦችዎን ለማሳካት ልዩ ጠቀሜታ ያላቸዉ በተቋሙ ወይም በአጋሮች ውስጥ ያሉ ዉስጣዊ ምክንያቶች ናቸዉ፣ ለምሳሌ በደንብ የሰለጠኑ ሰራተኞች፣ ወደ የአእምሮ ጤና እና የሳይኮማህበራዊ ድጋፍ አገልግሎቶች ጠንካራ የሪፈራል መንገዶች እና ተዛማች የመንግስት ዉሳኔ ሰጪዎችን ማግኘት። በአንድ ወርክሾፕ ውስጥ “በምን ላይ ጥሩ ነን?” እና “የምንኮራበት ነገር ምንድን ነዉ?” የሚሉት ጥያቄዎች እነዚህን ነገሮች ለማንፀባረቅ ይረዳሉ።
- **ድክመቶች** አላማዎችዎን ከግብ የማድረስ ችሎታዎትን የሚገቱ ዉስጣዊ ምክንያቶች ናቸው። ከሰርቫይቨሮች ጋር ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ለመስራት የሰለጠኑ ሰራተኞች እጥረት፣ የገንዘብ ውስንነት እና የደህንነት ስጋቶችን ለመቆጣጠር የአቅም ማነስን ያጠቃልላል ሊሆን ይችላል።
- **እድሎች** ብዙውን ጊዜ ውጫዊ ሁኔታዎች ናቸዉ፣ ለምሳሌ በህብረተሰብዎ ወይም በማህበረሰብዎ ውስጥ ለስራዎ ድጋፍ ሊሰጡ የሚችሉ ሁኔታዎች። እነዚህም አዎንታዊ የሚዲያ ትኩረትን ወይም ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት በይበልጥ እንዲታይ በሚያደርግ ክስተት ውስጥ የተፈጠረ ነባር የማህበረሰብ ውይይትን ሊያካትቱ ይችላሉ። አለፍ ሲልም ብሔራዊ ፓርላማዊ የጸረ ስቃይ ኮንቬንሽን (Convention against Torture) ወይም ሌላ ተዛማች ስምምነት መፅደቁን፣ ምቹ ብሔራዊ ፖሊሲ መኖሩን ወይም ከዓላማዎ ጋር የሚስማማ አቋም ያለው የመንግስት ሚኒስትር መሾምን ሊያካትት ይችላል። እንዲሁም እርስዎ ሊጠቅሱት እና ድጋፍ ሊያገኙበት የሚችሉትን ቀጣይነት ያለዉ ወይም የታቀደ ትልቅ ሀገራዊ ወይም ዓለም አቀፋዊ ጥረት (ለምሳሌ የተባበሩት መንግስታት ወይም ብሔራዊ ዘመቻዎች) ሊሆን ይችላል።
- **ስጋቶች** በዘመቻዎ ላይ አሉታዊ ተጸኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ውጫዊ ሁኔታዎች ወይም ከቁጥጥርዎ ዉጪ የሆኑ ነገሮች ሲሆኑ ግብ እና አላማቸዉን ለማሳካት ተግዳሮት ሊሆኑ የሚችሉ ናቸዉ ለምሳሌ የደህንነት ጉዳዮች፣ ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ሰርቫይቨሮች ላይ የተቃጣ ማህበራዊ የጥላቻ አመለካከት፣ የመንግስት ለውጥ ወይም ብሔራዊ ቀዉሶች።

ይህ ተግባር ጠቃሚ መረጃዎችን እንዲያቀርብ ከተፈለገ፣ ጥንካሬዎች፣ ድክመቶች፣ እድሎች እና ስጋቶች በተቻለ መጠን በተጨባጭ መልኩ መገለጽ አለባቸዉ። ‘ያልተረጋጋ የፖለቲካ ሁኔታ’- የሚሉ እና መሰል ረቂቅ ፅንሰ-ሀሳቦችን ከመጠቀም ይታቀቡ። ይልቁንስ በዚሁ ምሳሌ ውስጥ የትኞቹ የፖለቲካ ገጽታዎች ያልተረጋጉ እንደሆኑ እና እያንዳንዱ ገጽታ ግቦችዎን እና አላማዎትን እንዴት እንድሚነኩ ይግለጹ።



## 1.4 “ስድስት የአስተሳሰብ ኮፍያዎች” ተግባር

“ስድስት የአስተሳሰብ ኮፍያዎች“ ተግባር እያንዳንዱን ሰዉ የተለየ ኮፍያ በማልበስ ቡድኖች ሁኔታዎችን ከተለያየ አቅጣጫ እንዲመለከቱ የሚያግዝ ዘዴ ነዉ። ይህም ዘዴ ቡድኖች ሁኔታዎችን ከተለያየ አቅጣጫ እንዲፈትሹ በማስቻል የአንድን ሁኔታ ጠቃሚ ገፅታዎች ችላ እንዳይሉ እና እያንዳንዱ የቡድኑ አባል ወደ ሁኔታዉ ተመሳሳይ በሆነ አድልዎ ወይም እይታ የሚቀርብበትን አጋጣሚ ለማስወገድ ይረዳል። ይህም ቡድኖች ሊከሰቱ የሚችሉ አወንታዊ እና አሉታዊ ውጤቶችን ከሚዛን ውስጥ ያስገባ ውሳኔ እንዲያሳልፉ ይረዳል።




“ስድስቱ የአስተሳሰብ ኮፍያዎች“ የሚከተሉት ናቸዉ፦

**ቢጫ ኮፍያ ስለ አዎንታዊነት ነዉ።** የዚህን ውሳኔ ጥቅሞች እና ምን ምን እድሎችን እንደሚከፍት ለማየት ይሞክሩ።

**አረንጓዴ ኮፍያ ፈጠራን ይወክላል።** አእምሮዎ በነጻነት እንዲሮጥ በመፍቀድ ሃሳቦችን ሳንሱር ሳያደርግ ያምንጭ። የፈጠራ አማራጮችን እና መፍትሄዎችን ለማምጣት ይሞክሩ።

**ቀይ ኮፍያ ስለ ስሜቶች ነዉ።** ስለዚህ ጉዳይ ምን ይሰማዎታል? መንፈስዎን እና ካንጀት የሚመነጭ ስሜቶን ይጠቀሙ። ሌሎች በስሜታዊነት እንዴት ምላሽ ሊሰጡ እንደሚችሉ ለማየት ይሞክሩ። ስሜትን ወደ ሌላ ምክንታዊ ሂደት ለማምጣት ጥሩ መንገድ ነዉ።

**ነጭ ኮፍያ በመረጃዉ ላይ እንዲያተኩሩ ያደርግዎታል።** ያለዉን ዳታ እና አካሄዱን ይተንትኑ። ይህ በጣም ምክንያታዊ አቀራረብን ይወክላል።

**ጥቁር ኮፍያ ዝቅታን መመልከትን ይወክላል።** በጣም መጥፎዎቹ ሁኔታዎች ምንድናቸዉ? የመከላከል ዘዴን ይምረጡ፣ አሉታዊ ሊሆኑ የሚችሉ ውጤቶችን በመገመት ላይሰራ የሚችለዉን ይመልከቱ።

**ሰማያዊ ኮፍያ ሂደቱን ለመቆጣጠር ነው።** እነሱም አስተሳሰቡን ወይም ዉይይቱን ወደ ሌላ ኮፍያ/አመለካከት በማዛወር አብሮ ማንቀሳቀስ ነዉ።

**<u>“ስድስት የአስተሳሰብ ኮፍያዎችን“ እንዴት መጠቀም እንደሚቻል፡-</u>**

- የቡድን አወያይ ይመድቡ እና ሰማያዊ ኮፍያ እንዲለብሱ ያድርጉ።
- ለእያንዳንዱ ኮፍያዎች ካርድ ያድሏቸውና ኮፍያዎቻቸውን ይዘዉ ምን ዓይነት አመለካከት ሊኖራቸዉ እንደሚገባ ለተሳታፊዎች ያስረዷቸው።
- ተሳታፊዎች በወቅቱ የትኛዉን ኮፍያ እንደለበሱ በግልፅ የሚያሳዩበት መንገድ በማዘጋጀት ሃሳባቸዉን የሚመዘግቡበት መንገድ እንዳላቸዉ ያረጋግጡ።

የተግባራዊ እንቅስቃሴ ምሳሌ፡-

ተቋምዎ የሰርቫይቨር ሁኔታን አስመልክቶ መንግስት ለሰርቫይቨሮች አገልግሎትን እንዲያቀርብ የሚጠይቅ ረቂቅ ህግን እንዲደግፍ ተጠይቋል። ዉሳኔዉ ሁሉንም ሊከሰቱ የሚችሉ ማዕዘኖችን ከግምት ዉስጥ ያስገበ መሆኑን ለማረጋገጥ የስድስት አስተሳሰብ ኮፍያ መሳሪያን ይጠቀሙ።

ከ**ቢጫ** ኮፍያ በመጀመር፣ መንግስት ለሰርቫይቨሮች አገልግሎት እንዲሰጥ በማስገደድ ረገድ ህጉ ሊጫወተዉ የሚችለዉን አወንታዊ ሚና ይወያዩ። ለእነዚህ አገልግሎቶች ተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ ሊያስፈልግ ቢችልም እንኳ መንግስት ግዴታዉን እንዲወጣ ህጉ ተጠያቂ ያደርገዋል።

ከዚያም ዝቅታዉን ለመመልከት ወደ **ጥቁር** ኮፍያ ይቀይሩ፡- ረቂቅ ህጉ “ሰርቫይቨሮችን“ በጠባቡ ስለተሮገመ በጾታዊ ጥቃት የተወለዱ ህጻናትን አያከትትም። ረቂቅ ህጉን መደገፍ መንግስት በወሲባዊ ጥቃት ለተወለዱ ህጻናት አገልግሎት እንዲሰጥ የመገፋፋት ጉዳይን ለወደፊቱ ሊያዳክም የሚችል መሆኑን እና ከጾታዊ ጥቃት ለተወለዱ ህጻናት በሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት ፍላጎታቸዉ አነስተኛ የሆነ የቅድሚያ ግምት እየተሰጠዉ መሆኑን የሚያሳይ ምልክት ሊያስተላልፍ ይችላል።

**ነጭ** ኮፍያ የለበሰዉ ሰዉ ሰርቫይቭሮችን በሚመለከት በወጣዉ ህግ ዉስጥ ያልተካተቱን አጠቀላይ የወሲብ እና የስነ ተዋልዶ ጤና እና የመብት አገልግሎቶች ላይ ቋንቋን የማጥበቅ ሚናን እንደሚያሳድር ይጠቁማል።

በዚህ ረቂቅ ህግ ጉዳይ ላይ ቋንቋን ለማካተት ምንም አይነት ድጋፍ ካሌለ **አረንጓዴ**ዉን ኮፍያ ለብሰው ከጾታዊ ጥቃት ለተወለዱ ህጻናት እንዴት መሟገት እንደሚቻል ሃሳቦችን ያመነጫሉ።

ስብሰባዉ ለተወሰኑ ግዜያቶች እንደቀጠለ ስለሆነ **ሰማያዊ** ኮፍያ የለበሰዉ አስተባባሪ ዉሳኔዉ ለሌላ ጊዜ ተላልፎ ሌሎች ሰርቫይቨሮች እና በጾታዊ ጥቃት የተወለዱ ህጻናትን የሚደግፉ ተቋማትን ማማከር እንዳለባቸዉ ሀሳብ ይሰጣል።

ሁሉም ሰዉ ስለዚህ እቅድ ምን እንደሚሰማዉ ለማየት ቡድኑ **ቀዩ**ን ኮፍያ ለመልበስ ወሰነ። ሰዎች ከፍተኛ ዉሳኔ እንደሆነ ስለሚሰማሙ ውሳኔ ከማስተላለፋቸዉ በፊት ስጋቱን መቀነስ ትክክል እንደሆነ ይሰማቸዋል። አሁን ስለሱ ብዙም አይጨነቁም።

በዚህ ምሳሌ፣ ቡድኑ ይህን ውሳኔ በማድረግ ምክንያታዊ የሆነ ቀጣይ እርምጃ ላይ ደርሷል። ስድስቱን የአስተሳሰብ ኮፍያዎች በመጠቀም እያንዳንዱ እይታ የተሰማ ሲሆን ዉጤቱም በተለያዩ አመለካከቶች ላይ በመወያየት የተገኘ ነዉ።


## 1.5 የተቋማት የቴርሞሜትር ተግባር

የህ ልምምድ፣ እራስን መገምገምያ መሳርያ ኪቶችን ከመጠቀማችን በፊት እና ከመጠቀምችን በኋላ መከናወን አለበት።

እንዲህ አይነቱ ተግባር በተናጥል ድርጅቶች ወይም ለቡድን ድርጅቶች በእነርሱ አረዳድ ሰርቫይቭሮች የእውነት፤ የፍትሕ እና የፈውስ ፍለጋ ሂደቶችን በሚደግፉ የተለያዩ አከባቢዎች ላይ ሰርቫይቭሮች ፍላጎቶች ምን ያህል በጥሩ ሁኔታ እየተሟሉ እንዳሉ ገለጻ ለማድረግ እንዲሁም እጅግ በጣም ያልተሟሉ ፍላጎቶችን ለመለየት ያስችላችዋል።

በቴርሞሜትሩ ላይ የሚገኙት ከ 0 – 10 ያሉ ልኬቶች፣ ተቋሙ አሊያም ደግሞ ቡድኑ በእያንዳንዱ አከባቢ ተተግብሯል ብሎ የሚያስበውን የሰርቫይቭሮች ፍላጎቶች የመሟላት መጠንን የሚወክሉ ሲሆኑ፣ የ 0 ልኬት “በጭራሽ እንዳልተሟላ“ ሲያመለክት፣ የ 10 ልኬት ደግሞ “ሙሉ በሙሉ መሟላቱን“ ያመላክታል። ከእራስ-ግምገማ በፊት እና በኋላ የተሰራዉን ቴርሞሜትር በማነፃፀር፣ ተሳታፊዎች በተለያዩ አከባቢዎች የሰርቫይቭሮች ፍላጎቶች እንዴት እንደሚሟሉ ያላቸዉ ግንዛቤ በራስ የመገምገም ሂዳት እንዴት እንደተለወጠ መገንዘብ ይችላሉ።

ራስን መገምገም ከተጠናቀቀ በኋላ የሚገኘዉ ቴርሞሜትር በጣም ያልተሟሉ ፍላጎቶች ያላቸውን ቦታዎች (ለምሳሌ በቴርሞሜትር ከ 0 እስከ 5 መካከል) በመለየት የተቋማቱን ሥራ ለመምራት እና በእነዚያ አካባቢዎች የሰርቫይቨሮች (Survivors) ድጋፍ ለማጠናከር እርምጃዎችን ለማዘጋጀት ይረዳል(ለምሳሌ፣ አዳዲስ ሪፈራል መንገዶችን በመፍጠር ላይ በማተኮር፣ አዳዲስ ተግባራትን መርሃግብር በማስተዋወቅ፣ ሰርቫይቨሮች ለመደገፍ የሚያገለግል እውቀት/ልምድ ካላቸዉ ሌሎች ድርጅቶች ጋር አዲስ ትብብር መገንባት ወዘተ.)፡፡




(10=completely; 0=not at all)

## 1.6 ከ ሰርቫይቨሮች ጋር የሚሰራ የተቋማት የቴርሞሜትር ተግባ፡-

ይህን መልመጃ ተቋማት የሰርቫይቨሮች ፍላጎቶች በአውዳቸው ውስጥ ምን ያህል እየተሟሉ ነዉ በሚለዉ ላይ (ተቋማት ቀደም ሲል የተዘረዘሩትን መመሪያዎች በመጠቀም ማከናወን ይችላሉ) ዩራሳቸውን ትንተና ለማሟላት ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡፡

የቴርሞሜትር ልምምዱን ከሰርቫይቨሮች ጋር የማካሄዱ አላማ፣ ተቋማቱ የሰርቫይቨሮች ፍላጎቶች በአውዳቸው ውስጥ ምን ያህል እንደተሟሉ ያላቸውን ግንዛቤ ከሰርቫይቨሮች የግል ግምገማ ጋር እንዲያወዳድሩ ለማስቻል ነው፡፡ ይህም ተቋማት ሰርቫይቨሮች ቅድሚያ የሚሰጧቸውን ጉዳዮች እና ፍላጎቶች በተመለከተ ያላቸዉ ግንዛቤ እራሳቸው የገለጹትን አመለካከት የሚያንፀባርቅ መሆኑን በማረጋገጥ መርሃግብሮቻቸውን እና ተግባራቶቻቸውን በዚህ መሰረት ማበጀት እንዲችሉ ያግዛል፡፡

ተቋማት የራስ-ግምገማውን ካጠናቀቁ በኋላ እና ሁለተኛውን ቴርሞሜትር ካዘጋጁ በኋላ ከሰርቫይቨሮች ጋር ልምምድ ማድረግ አለባቸው፣ ይህም በራስ ግምገማ ውጤቶች ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በመቀጠልም፣ ተቋማት የሰርቫይቨሮችን አመለካከት የሚያንፀባርቅ ቴርሞሜትር ለማዘጋጀት እና ይህንን ቴርሞሜትር ከራሳቸው ጋር ለማነፃፀር ከሰርቫይቨሮቹ ጋር ልምምዱን ማከናወን አለባቸው፡፡

**በሐሳብ ደረጃ፣ የአንድ ተቋም የራሱ ቴርሞሜትር ከሰርቫይቨሮች ቴርሞሜትር ጋር በቅርበት ይመሳሰላል፣ ይህ የሚያሳየው ተቋሙ በዐውዳቸዉ ውስጥ የሰርቫይቨሮች ፍላጎቶች እንዴት እንደሚሟሉ ጥሩ ግንዛቤ እንዳለው ነዉ፡፡** ነገር ግን፣ ቴርሞሜትሮቹ በጣም የተለያዩ ከሆነ፣ ድርጅቱ የሰርቫይቨሮች ፍላጎቶች እንዴት እየተሟላ እንደሆነ ያለው ግንዛቤ ከሰርቫይቨሮች አመለካከት ጋር ያልተመሳሰለበትን ምክንያት በበለጠ ማጣራት እና ይህንንም ለመቀነስ እርምጃዎችን መውሰድ ያስፈልገዋል ( ለምሳሌ፣ ከሰርቫይቨሮች በአገልግሎታቸው ላይ ያላቸዉን ግብረ መልስ ለመቀበል ሰባል የግብረመልስ ምልልስ በአገልግሎታቸው ላይ በመገንባት፣ ስላሉት ሌሎች የድጋፍ አገልግሎቶች ተጨማሪ መረጃ በመስጠት ወዘተ.)

ተቋማት ይህንን ልምምድ ከሰርቫይቨሮች ጋር ማከናወን ያለባቸው አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ብቻ መሆኑ ልብ ሊባል የሚገባው ጉዳይ ነው፣ ለምሳሌ ከሰርቫይቨሮች ጋር ለማማከር እና ለጋራ ንድፍ ፕሮግራሞች አስቀድመው አወቃቀሮችን ያዘጋጁ ሲሆን፡፡ እንደዚህ አይነት አወቃቀሮች ለሌላቸው ድርጅቶች፣ ይህንን ተግባ ማከናወን ተገቢ ላይሆን ይችላል፣ በተለይም በመልመጃው ውስጥ የሚሳተፉ ከሰርቫይቨሮች ማፈላለግ የሚያካትት ከሆነ፣ ይህን ማድረግ በእነሱ ላይ ተጨማሪ ሸክም ስለሚፈጥር አስፈላጊ ላይሆን ይችላል፡፡



ተጨማሪ ንባብ

## 2. ከሰርቫይቨር ጋር አብሮ ለመስራት ስነ-ምግባር እና መልካም ተሞክሮዎች- የምሳሌ ግብአቶች

### 2.1 የስጋት ግምገማ ምሳሌ፦

ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ሰርቫይቨሮች ጋር ለሚሰሩ ድርጅቶች የስጋት ምዘናዎችን መፍጠር የሰርቫይቨርንም ሆነ የሰራተኞችን ደህንነት እና ሰላም መሆንን ለማረጋገጥ ወሳኝ እርምጃ ነው። ይህ አጠቃላይ አብነት መሆኑን እና ከድርጅትዎ ልዩ ፍላጎቶች እና አውድ ጋር እንዲስማማ መስተካከል እንዳለበት ማስታወስ ይኖርቦታል። ደካማ በሆኑ አውድ ውስጥ የሚሰሩ ድርጅቶች ሁኔታው በፍጥነት ሊለወጥ ስለሚችል የስጋት ግምገማቸውን በየጊዜው መከለስ እና ማዘመን አለባቸው።

**ድርጅት፦** [የድርጅቱ ስም]

**ቀን፦** [የስጋት ግምገማ ቀን]

**የስጋት ግምገማ ቡድን፦**

[የቡድን አባል ስም 1]

[የቡድን አባል ስም 2]

[የቡድን አባል ስም 3]

# I. አውዳዊ ትንተና፦፦

## ሀ. አካባቢ እና አውድ፦፦

የሰርቫይቨሮች እና የሰራተኞችን ደህንነት እና አጠቃላይ ጤንነት ላይ ተጽእኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ማናቸውንም ሁኔታዎችን በማጉላት ድርጅቱ የሚሠራበትን ጂኦግራፊያዊ አካባቢ ይግለጹ።

## ለ. ቁልፍ ባለድርሻ አካላት፦፦

የአካባቢ ባለስልጣናትን፣ ህግ አስከባሪዎችን፣ የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎችን እና አጋር ድርጅቶችን ጨምሮ ቁልፍ ባለድርሻ አካላትን መለየት እና የድርጅቱን ስራ ለመደገፍ አመለካከታቸውን፣ አቅማቸውን እና ፍላጎታቸውን መገምገም።

# II. ስጋት መለየት፦

## ሀ. የስጋት ምድቦች፦፦

- **ደህንነት (ሴፍቲ እና ሴኪዩሪቲ)፦** አካላዊ ደህንነትን፣ ትንኮሳን እና ሊከሰቱ የሚችሉ ስጋቶችን ጨምሮ በሰራተኞች እና በሰርቫይቨሮች የሚደርሱትን የደህንነት ስጋቶች ይገምግሙ።
- **ሚስጥራዊነት እና ግላዊነት፦** ሚስጥራዊነትን መጣስ እና የሰርቫይቨሮችን ማንነት እና መረጃ መጠበቅ ስጋትን ይገምግሙ።
- **ስነ ልቦናዊ ማህበራዊ ስጋት፦፦** በስራው አይነት ምክንያት በሰራተኞች እና ሰርቫይቨሮች ላይ ያለውን ስሜታዊ እና ስነ-ልቦናዊ ተፅእኖ ግምት ውስጥ ያስገቡ።
- **የአሠራር አደጋዎች፦፦** በድርጅታዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ሊከሰቱ የሚችሉትን አደጋዎች እንደ የገንዘብ ድጋፍ ተግዳሮቶች፣ የሀብት ውስንነቶች እና የሎጂስቲክ ጉዳዮችን መርምሩ።
- **ባህላዊ እና ማህበራዊ ስጋቶች፦** ባህላዊ እና ማህበራዊ ደንቦች የሰርቫይቨሮችን ስራ እና ደህንነት እንዴት እንደሚነኩ ይተንትኑ።

## ለ. ልዩ ስጋቶች፦፦

ለእያንዳንዱ የስጋት ምድብ በዐውድ እና በድርጅቱ እንቅስቃሴዎች ላይ ተመስርተው ዝርዝር ስጋቶችን እና ተጋላጭነቶችን ይለዩ።

# III. የስጋት ግምገማ እና ቅነሳ፦

## ሀ. ደህንነት (ሴፍቲ እና ሴኪዩሪቲ)፦

**ስጋት፦** በሰራተኞች እና በሰርቫይቨሮች ላይ ሊከሰት የሚችል አካላዊ ጉዳት።

**ቅነሳ፦**

- የሰራተኞች ስልጠና እና ግንዛቤን ጨምሮ ጥብቅ የደህንነት ፕሮቶኮሎችን ይተግብሩ።
- ሚስጥራዊ መረጃ ከሰርቫይቨሮች ጋር ሲወያዩ ጥቅም ላይ የሚውሉ ደህንነታቸው የተጠበቀ እና ሚስጥራዊ ቦታዎችን መለየት።

## ለ. ሚስጥራዊነት እና ግላዊነት፦

**ስጋት፦** የሰርቫይቨሮችን ሚስጥራዊነት መጣስ።

**ቅነሳ፦**

- ጥብቅ የመረጃ ጥበቃ እርምጃዎችን እና ኢንክሪፕሽን ይተግብሩ።
- ሚስጥራዊነትን ስለመጠበቅ አስፈላጊነት ለሰራተኞች ስልጠና ማቅረብ።
- የተሳታፊ ዝርዝሮችን የያዙ ማናቸውንም ሰነዶች እንደ የይለፍ ቃል ጥበቃ ያሉ እርምጃዎችን ያካትቱ።
- መደበኛ የዲጂታል ደህንነት ሴሚናሮችን እና "የቱን አፕስ" - ተግባራዊ መመሪያ እና መሳሪያዎችን ለመፈተሽ ክፍለ ጊዜዎች ማቅረብ።

## ሐ. ስነ ልቦናዊ ማህበራዊ አደጋዎች፦

**ስጋት፦** በሰራተኞች እና በሰርቫይቨሮች ላይ ስሜታዊ እና ስነ ልቦናዊ ጭንቀት።

**ቅነሳ፦**

- ለሰራተኞች እና ለሰርቫይቨሮች የድጋፍ አገልግሎት መስጠት ከሚችሉ ድርጅቶች ጋር የሪፈራል መንገዶችን ማዘጋጀት።
- ሰርቫይቨሮች ልምዳቸውን እንዲያካፍሉ አስተማማኝ ቦታዎችን ይፍጠሩ።
- ሰራተኞች እና ሰርቫይቨሮች ሁለተኛ የስሜት ቀውስ የማስጠንቀቂያ ምልክቶችን እና እንዴት ማቃለል እንደሚችሉ እንዲያውቁ የስሜት ቀውስ ላይ ስልጠና መስጠት።

## መ. የአሠራር አደጋዎች፦፦

**ስጋት፦** በገንዘብ ወይም በንብረት ውሱንነት ላይ ያሉ መቆራረጦች።

**ቅነሳ፦**

- የገንዘብ ምንጮችን ማብዛት እና የድንገተኛ ፈንድ ማዘጋጀት።
- ጠንካራ ድርጅታዊ መዋቅር እና ስጋት አስተዳደር እቅድ ማዘጋጀት።

## ሠ. የባህል እና ማህበራዊ አደጋዎች፦፦

**ስጋት፦** ጾታዊ ጥቃትን ለመቅረፍ ባሕላዊ ተቃውሞ

**ቅነሳ፦**

- ባህልን ከግምት ያስገቡ የማዳረሻ ቁሳቁሶችን እና መርሃግብሮችን ማዘጋጀት።
- ከአካባቢው ማህበረሰብ መሪዎች ጋር አብሮ መስራት እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘመቻዎችን ማድረግ።

# IV. የስጋት ክትትል እና ግምገማ፦፦

- የስጋት መከላከያ እርምጃዎችን ውጤታማነት ለመገምገም እና አስፈላጊ ማስተካከያዎችን ለማድረግ መደበኛ ግምገማ ሂደትን ያስቀምጡ።

# V. የአደጋ ጊዜ ምላሽ ዕቅድ፦፦

- ወሳኝ ለሆኑ ጉዳዮች ምላሽ ለመስጠት ሰርቫይቨሮችን እና የሰራተኞችን ደህንነት አጠቃላይ ድህነነትን ለማረጋገጥ ዝርዝር እቅድ ያውጡ።

# VI. ሪፖርት ማድረግ እና ግንኙነት፦፦

- ሰራተኞቹ አደጋዎችን እና ክስተቶችን እንዲዘግቡ እና ከባለድርሻ አካላት ጋር ክፍት እና ግልጽ ግንኙነት እንዲያደርጉ ግልጽ የሆነ የሪፖርት ማሰራጫ መንገዶችን ያቋቁሙ።

# VII. የሰራተኞች ስልጠና፦

- ስለ አደጋ ቁጥጥር፣ ደህንነት እና ስነምግባር ጉዳዮች ለሰራተኞች አጠቃላይ ስልጠና መስጠት።

# VIII. በጀት እና ሀብቶች፦፦

- ለአደጋ መከላከያ እርምጃዎች እና ለአደጋ ጊዜ ምላሽ ሀብቶችን እና በጀት ይመድቡ።

# IX. ማጽደቅ እና መተግበር፦፦

- ይህ የስጋት ግምገማ በከፍተኛ አመራሩ መጽደቅ እና በድርጅቱ ውስጥ መተግበር አለበት።

## 2.1.2. በመረጃ ላይ የተመሰረተ የፍቃድ ማረጋገጫ ዝርዝር ምሳሌ፣ በ ሲነርጂ ፎር ጀስተስ ኤንድ ሎየርስ ኤንድ ዶክተርስ ፎር ሂዩማን ራይትስ (Synergy for Justice and Lawyers and Doctors for Human Rights (LDHR) )የቀረበ:-

| ደረጃ | መመሪያ | ✓ |
|---|---|---|
| **እራስን ማስተዋወቅ:- ማን እንደሆኑ፣ የ LDHR ምንነትን እንዲሁም አላማዉ እና የስራዉ ባህሪ ምን እንደሆነ።** | እኔ ዶክተር ______ ነኝ፣ ከ ____ ዩኒቨርሲቲ በ ____ አመት የተመረቅኩ ሀኪም። በ ____ ሙያዬ መስራት የጀመርኩት በ____ የዓመቱ መጀመሪያ ላይ ነዉ። በኢስታንቡል ፕሮቶኮል መሰረት ለሰብአዊ መብት ጥሰት የባለሙያ/ኤክስፐርት የህክምና ሰነዶች ከተቋቋመዉ የሶሪያ ዶክተሮች እና ጠበቆች መረብ ከሆነዉ ከጠበቆች እና ዶክተሮች ለሰብአዊ መብቶች (LDHR) ጋር እሰራለሁ። የኢስታንቡል ፕሮቶኮል ማሰቃየትን እና ሌሎች የጭካኔና ኢሰብአዊ ወይም አዋራጅ ቅጣትን ወይም አያያዝን ለመመርመር እና ለመመዝገብ የሚያገለግል አለም አቀፍ ፕሮቶኮል ነው። እንደ ሀኪም ከ ____ አመት በላይ የስራ ልምድ ያለኝ ሲሆን በተለይም ደግሞ ከሰብአዊ መብት ጥሰት ጋር የተያያዙ የህክምና ግምገማዎችን በማካሄድ ላይ ስልጠና የወሰድኩ ነኝ። እንደ LDHR አባል ____ የሚያህሉ የሜዲካል እና የህግ ግምገማዎችን አድርጌያለሁ። LDHR አለም አቀፍ ደረጃዎችን የሚያሟሉ እና ለወደፊቱ በማንኛዉም የወንጀል ፍርድ ቤት ተቀባይነት ያላቸዉን የህክምና ሪፕርቶች ለማቅረብ ያለመ ነዉ። | |

| ደረጃ | መመሪያ | ✓ |
|---|---|---|
| **የግምገማ ሂደት** | የሕክምና ግምገማን እንዴት እንደምናከናዉን ትንሽ እንዳብራራ ይፍቀድልኝ። እነዚህን የመጀመሪያ ዉይይቶች ከጨረስን በኋላ፣ እና ለመቀጠል ከፈለጉ፣ ስለ እርሶ አንዳንድ የግል መረጃዎችን ያካተተ ግምገማን እንጀምራለን። ከዚያ ከመታሰርዎ በፊት ባለዉ ጊዜ ውስጥ የነበረዉን የእርስዎን የህክምና ታሪክ ሁኔታዎች እናገኛለን። በመቀጠል፣ በእስር ጊዜዎ እርስዎ ላይ ምን እንደደረሰ በዝርዝር እንነጋገራለን። የሆነውን ነገር መረዳቴን ለማረጋገጥ አንዳንድ የማጣርያ ጥያቄዎችን ልጠይቅ እችላለሁ። ስለዚህ ነገር ማውራት ከባድ እንደሆነ አውቃለሁ፣ ነገር ግን ከሌሎች ጋር ለመወያየት ስለሚከብዱ ዝርዝር ጉዳዮች ልጠይቅዎት ይገባል። ቢሆንም፣ እሄን ማድረጌ ጠቃሚና አስፈላጊ ነዉ። የሕክምና ግምገማዬን ለማጠናቀቅ፣ ከእነዚህ ዝርዝሮች ውስጥ አንዳንዶቹን መረዳት አለብኝ። ወደፊትም የእርሶ ምስክርነት የወንጀል ድርጊቱ ፈጻሚዎችን ተጠያቂ ለማድረግ በሚቀርበው ክስ ላይ ጥቅም ላይ እንዲዉል ከተፈለጉ ፍርድ ቤቱን መርዳትም አስፈላጊ ይሆናል። ስለማያስፈልገኝ ስለማናቸውም ነገር አልጠይቅም። | |

| ደረጃ | መመሪያ | ✓ |
|---|---|---|
| **የግምገማ ሂደት** | ከቃለ መጠይቁ በኋላ ለእርሶ የአካል ምርመራ ማድረግ አለብን። [ይህን የምናደርገው ግላዊነትዎን በሚጠብቅና ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ ነው። ይህ የበለጠ ምቾት እንዲሰማዎት የሚያደርግ ከሆነ ወንድ ወይም ሴት የሥራ ባልደረባዬን ይዤ መጥቼ ምርመራ ማድረግ እችላለሁ።] ቅር የማያሰኞት ከሆነ የጉዳቱን ፎቶግራፍ መውሰድ ይኖርብኛል። እነኚህን ፎቶግራፎች ማንነታችሁን በሚደብቅ መልኩ እና ማንነታችሁን የሚጠቁሙ ምልክቶች እንዳያርፉበት አድርጌ ማንሳት እችላለሁ። በሪፖርቱ ውስጥ ያሉት እነዚህ ፎቶዎች የአካል ጉዳት ስለ መድረሱ ማስረጃዎችን ለማስቀመጥ ነዉ። እናም ፎቶዎቹ የተካተቱት ለዚህ ነው። ከዚያም፣ በግምገማው ወቅት እና ከዚያ በኋላ የስነ-ልቦና ግምገማ ተደርገዎሎት ሲያበቃ፣ በእስር ጊዜ፣ ከተለቀቁ በኋላ እና አሁን ስላጋጠሙዎት የአእምሮ ሁኔታ ዝርዝር ነጥቦች ይወሰዳሉ።<br><br>የመጨረሻው ክፍል የግምገማው ደምዳሚው እኔ እሆናለው። ያለዎትን ማንኛቸውንም ጥያቄዎች እመልሳለው፣ እናም ለእርስዎ ጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ የድጋፍ አገልግሎቶችን መጠቆም እችላለሁ። ግምገማውን ለመቀጠል ቢወስኑም ባይወስኑም ይህንን መረጃ ልሰጥዎ እችላለሁ። በሂደቱ ወቅት፣ በፈለጉት ጊዜ እረፍት መውሰድ ይችላሉ። በሚመችዎት ፍጥነትም እንጓዛለን። በዚህ ጊዜ፣ የሚፈልጉትን ሁሉ ሊጠይቁኝ ይችላሉ፣ እኔም ነገሮችን አስረዳለሁ። ከዚያም ዛሬ በጻፍኳቸው ማስታወሻዎች ላይ ተመስርቼ ሪፖርቱን እጽፋለሁ። ሁሉም የሚያቀርቧቸው መረጃዎች እና ትረካዎች ከአካላዊ እና ስነ ልቦናዊ ምርመራ ውጤቶች ጋር የተገናኙ መሆናቸውን በሚደመድም ማጠቃለያ ሪፖርቱ ያበቃል። | |

| ደረጃ | መመሪያ | ✓ |
|---|---|---|
| **ሚስጥራዊነት** | ይህ ሰነድ ሚስጥራዊ ነው። ስለዚህ፣ እርሶ ፍቃድዎን ካልሰጡ በስተቀር አይቀረጽም፣ አይታተምም ወይም ለማንም አካል አይጋራም። ይህ ሚስጥራዊነት የጋራ በመሆኑ በዘጋቢውም ሆነ በታካሚው የተጠበቀ ነው። በተጨማሪም፣ በ LDHR፣ ደህንነትን እና ሚስጥራዊነትን ለመጠበቅ በርካታ ጥብቅ እርምጃዎችን ወስደናል። ስለዚህ፣ የእርስዎን መረጃ ለመቅዳት እና ለማቆየት ደህንነቱ የተጠበቀ የተመሰጠሩ( encrypted) ዘዴዎችን እንጠቀማለን። በተጨማሪም፣ የማንኛውም ታካሚ ጉዳይ በምልክት እንጂ በሰው ስም አይጠቀስም። ዋናው ሪፖርት ከክልሉ ውጭ በሦስተኛ ሀገር ውስጥ አብረን ለምንሰራው አጋር ተቋማት ተላልፎ በአስተማማኝ ሁኔታ ተከማችቷል። ይህ ምስጢራዊነት አሁን የምንነግርዎትን አደጋዎች ለመቀነስ አስተዋፅዖ ያደርጋል። | |

| ደረጃ | መመሪያ | ✓ |
|---|---|---|
| **የመረጃ አጠቃቀም እና ሪፖርቱ ለማን እንደሚጋራ** | እንደገለጽኩት፣ ዛሬ የተናገሯቸው ነገሮች በሙሉ በሚስጥር የሚያዙ ሲሆን ማንኛውም መረጃዎች በተቻለን አቅም ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ ላይ ጥበቃን ያገኛሉ። የፎረንሲክ የሕክምና ግምገማ ለማድረግ ከተስማሙ፣ ሪፖርትዎን ለLDHR ለማጋራት ተስማምተዋል። በሪፖርቱ ውስጥ የተካተተው መረጃ መሰረታዊ ጉዳዮችን ለማወቅ ሲባል (ለምሳሌ፤ እርስዎን ወደ አገልግሎቶች ለመምራት፣ ለጥራት ማረጋገጫ ወይም ለመረጃ ትንተና) በውስጥ ከሌሎች የLDHR ሰራተኞች ጋር ጥቅም ላይ ሊዉል ይችላል። ሪፖርቱን ለLDHR ለማጋራት ስምምነትዎን ለመስጠት ፍቃደኛ ካልሆኑ፣ እኔ የLDHR አውታረ መረብ አባል ስለሆንኩ ይህን ማድረግ የማይቻል በመሆኑ የሰነድ ሂደቱ መቆም አለበት።<br><br>የእኛ ሀጋር ተቋማት በአሁኑ ጊዜ ዋና ሪፖርቶችን በሶስተኛ ሀገር ውስጥ ያከማቻሉ። የፎረንሲክ የህክምና ግምገማ ካደረጉ እና ሪፖርትዎን ካጠናቀቁ፣ የታሸገ ዘገባ ለአጋር ድርጅታችን ለ ሲነርጂ ፎር ጀስቲስ ለመጋራት ተስማምተዋል እንደማለት ነው። ሲነርጂ ፎር ጀስቲስ የእርስዎን መረጃ የማግኘት መብት አይኖረውም። የታሸገ ሪፖርትን ወደ ሲነርጂ ፎር ጀስቲስ የማዛወሩ ብቸኛ አላማ ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ ማስቀመጥ ብቻ ነው።<br><br>ይህንን ስራ የምሰራው የወደፊት የወንጀል ክሶችን ለመደገፍ ነው፣ ነገር ግን ሪፖርቱ እንዴት ጥቅም ላይ እንዲውል እንደሚፈልጉ መወሰን የእርስዎ ምርጫ ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ አንዳንድ አማራጮች ከዚህ በመቀጠል ተዘርዝሮ ይገኛሉ፦<br><br>1. ለሰብአዊ መብቶች ሪፖርቶች እና ስልጠናዎች፦ እርሶ ከተስማሙ፣ LDHR መረጃዎን የአለም አቀፉ ማህበረሰቡ እርምጃ እንዲወስድ ለማሳወቅ እና ግፊት ለማድረግ በማለም በሚታተሙ (ስም እና መለያ ዝርዝሮች ይደበቃሉ) የሰብአዊ መብት ሪፖርቶች ውስጥ ሊጠቀማቸዉ ይችላል። እንዲሁም፣ የእርሶን ጉዳዮች ወይም ከፊሎቹን በማይታወቅ መልኩ በተቋማችን ውስጥ ለጥራት ማሻሻያ እና ስልጠና ለመጠቀምም ከፈለግን ፍቃድዎን የምንጠይቅ ይሆናል።<br><br>2. ለተባበሩት መንግስታት ገለልተኛ አጣሪ ኮሚሽን (UNCOI)፦ ይህ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የምርመራ አካል ለተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብቶች ምክር ቤት እና የፀጥታው ምክር ቤት መደበኛ ሪፖርቶችን ያቀርባል። ጉዳዮችን አይከስም፣ ነገር ግን የሌሎች ሀገራት ተመሳሳይ ኮሚሽኖች የሚሰሩት ስራ አለም አቀፍ ወንጀሎችን የሚዳኝ የወንጀል ፍርድ ቤት በሚቋቋምበት ጊዜ ክስ ለመመስረት መሰረት ሆኖአል። በሶሪያ ውስጥ ምን እየተከናወነ እንዳለ ሙሉ መዝገብ እና ግንዛቤን ለማረጋገጥ ሲባል እንዲሁም በኋላ ላይ ተጠያቂነት እንዲኖርም መሰረት ሊፈጥር ስለሚችል ዘገባውን ልናካፍላቸው እንችላለን። እርስዎ ከተስማሙ፣ UNCOI እርስዎ የሚያቀርቧቸውን አንዳንድ መረጃዎች በይፋዊ ሪፖርቶቹ ውስጥ ሊያካትት ይችላል። | |
| | 3. ለ IIIM (በሶሪያ አረብ ሪፐብሊክ ከመጋቢት 2003 ዓ.ም. ጀምሮ የተፈጸሙትን እጅግ ከባድ የሆኑ ወንጀሎችን መመርመር እና ለፍርድ ማቅረብን የሚያግዝ አለምአቀፍ፣ የማያዳላ እና ገለልተኛ ስርአት)፦ በተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ ስልጣን ተሰጥቶት፣ IIIM በሶሪያ ውስጥ የተፈጸሙ ከባድ ጥሰቶችን ማስረጃዎች ይሰበስባል እንዲሁም ያስቀምጣል። የእርስዎን ፈቃድ ካገኘም፣ ይህን መረጃ ለሀገር አቀፍ፣ ለክልላዊ ወይም ለአለም አቀፍ የምርመራ ወይም የክስ ባለስልጣናት ማጋራት ይችላል።<br><br>4. ተጠያቂነትን የማስፈን ጥረት ላይ ለሚገኙ ዓለም አቀፍ ወይም የሶሪያ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ወይም የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት፦ ውጤታማ የሆነ የአለም አቀፍ የወንጀል ፍትህ ስርአት ባሌለበት በዚህ ወቅታዊ ሁኔታ፣ የፍትህ እድሎችን ከፍ ለማድረግ ሲባል የሶሪያ እና አለም አቀፍ ተቋማት በተለያዩ ሀገራት (ለምሳሌ በጀርመን) በሶሪያውያን ወንጀለኞች ላይ ክስ ለመመስረት እየሞከሩ ነው። እርስዎ ያቀረቡት መረጃ ከሚገነቡት የክስ ጉዳዮች ጋር የሚገናኝ ከሆነ፣ መረጃዎን እንድናካፍላቸዉ ይጠይቁናል እርሶ ፈቃደኛ ከሆኑ።<br><br>5. የአለም አቀፍ የወንጀል ፍትህ ዘዴዎች፦ እስካሁን የሶሪያን ጉዳዮች የማየት ስልጣን ያላቸው አለም አቀፍ ፍርድ ቤቶች የሉም። የሆነ ጊዜ ላይ፣ ካሉት ፍርድ ቤቶች አንዱ (ለምሳሌ የአለም አቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት) በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ክስ እንዲመሰርት ሊጠየቅ ይችላል፤ ወይም ደግሞ የሶሪያ ጉዳዮችን የሚመለከት አዲስ አለም አቀፍ ፍርድ ቤት ሊቋቋም ይችላል። ጉዳይዎ በዚህ አይነቱ ፍርድ ቤት ክስን ለመደገፍ ጥቅም ላይ እንዲውል ከፈለጉ መረጃዎን ለእነርሱ ልናካፍላቸዉ እንችላለን።<br><br>6. ከሽግግሩ በኋላ ሊመሰረቱ ለሚችሉ ብሄራዊ ወይም ድብልቅ የወንጀል ፍትህ ዘዴዎች፦ ግጭቱ ካለቀ በኋላ የወንጀል ፍትህ እና ተጠያቂነት በሶሪያ ፍርድ ቤት ሊሰጥም ይችላል። ይህ ለምሳሌ በቦስኒያ ተከስቷል።<br><br>7. ከሽግግር በኋላ ብሔራዊ የሰብአዊ መብት ይገባኛል መጠየቂያ ዘዴ፦ ለደረሰቦት የሰብአዊ መብት ጥሰት ካሳ መጠየቅ የሚቻልበት የሶሪያ የሰብአዊ መብት ጥያቄ ዘዴ ወደፊት ሊፈጠር ይችላል።<br><br>8. ልዩ ሂደቶችን እና የክልል ፍርድ ቤቶችን ጨምሮ የተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብት ዘዴዎች፦ ማንነትን በማያመላክት መልኩ መረጃዎን LDHR ለተባበሩት መንግስታት አካላት ወይም ለተባበሩት መንግስታት ልዩ ራፖርተሮች በሚያቀርብበት ጊዜ ጥቅም ላይ ሊያውል ይችላል።<br><br>9. ለእነዚህ ሁሉ አማራጮች፣ መረጃ ወደ እርስዎ ተመልሶ እንዳይገኝ ወይም ማን እንደ ሆኑ ለመለየት እንዳይቻል ሪፖርት ማድረግን ወይም ስለ ጉዳይዎ ማንነትን የማያገልጽ መረጃ መስጠትን መምረጥ ይችላሉ። ነገር ግን ከእነዚህ አማራጮች ውስጥ ለአንዳንዶቹ ሪፖርቱ ውጤታማ እንዲሆን ከተፈለገ ሙሉ መታወቂያ አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ፣ ለወንጀል ሂደቶች ተጎጂው ማን እንደሆነ ማወቅ ይፈልጋሉና ስለ ማስረጃዎ ሊያነጋግሩዎት ይችላሉ። | |

## 2.2. ከሰርቫይቨሮች ጋር ለመስራት ስነምግባር እና መልካም ተሞክሮዎች፦ ውጪያዊ ሰነዶች

**2.2.1. USAID Collective action to reduce gender-based violence (CARE-GBV), How to implement a survivor-centered approach in Gender-Based Violence (GBV) programming:** https://makingcents.com/wp-content/uploads/2021/01/CARE-GBV-03-Survivor-centered-v9-508c.pdf

**2.2.2. United Nations Population Fund (UNFPA), Guidance note on understanding efforts to prevent and address gender-based crimes in Myanmar: Analysis, research, and programming.**

**2.2.3. AMA Journal of Ethics, Survivor-Centered Approaches to Conflict-Related Sexual Violence in International Humanitarian and Human Rights Law:** https://journalofethics.ama-assn.org/article/survivor-centered-approaches-conflict-related-sexual-violence-international-humanitarian-and-human/2022-06

**2.2.4. OHCHR Protection of Victims of Sexual Violence: Lessons Learned:** https://www.ohchr.org/sites/default/files/Documents /Issues/Women/WRGS/ReportLessonsLearned.pdf

## 2.3. ሁለንተናዊ የድጋፍ አገልግሎቶች-ምሳሌ ግብዓቶች


### 2.1.1. የሪፈራል መንገዶችን ለመገንባት እና ለመጠገን የአካሄድ ቻርት

1. የሚገኙ አገልግሎቶችን መሳል ለምሳሌ፡ የጤና እንክብካቤ፣ የአእምሮ ጤና እና የስነ-ልቦና ድጋፍ፣ የመኖሪያ ቤት፣ የህግ እና የኢሚግሬሽን፣ የጥበቃ እና የፍትህ አገልግሎቶችን የሚያቀርቡ የሀገር ውስጥ አቅራቢዎች።
2. መሰረታዊ መስፈርቶችን የሚያሟሉ መሆናቸውን ለመወሰን የአገልግሎቶቹን ጥራት ይገምግሙ።
3. የእያንዳንዱን ሰርቫይቨር ወሲባዊ ዝንባሌ፣ የሥርዓተ-ፆታ ማንነት ወይም አገላለጽ፣ እና የፆታ ባህሪያት (SOGIESC) እና ማንኛውም የተደራሽነት ፍላጎቶችን ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚከተሉትን መሰረታዊ መስፈርቶች የሚያሟሉ አገልግሎቶችን ያሰባስቡ።
    - ሀ. ብቁነት፣ የቋንቋ ችሎታዎችን ጨምሮ።
    - ለ. አካባቢ ቅበላ።
    - ሐ. የመገናኛ ነጥቦች እና የተመደቡ ሰዎች።
    - መ. የስራ ሰዓታት እና ከስራ ሰዓት በኋላ እንክብካቤ።
    - ሠ. ዋጋ።
    - ረ. የመግቢያ ቅጾች እና ሂደቶች።
    - ሰ. ምስጢራዊነት ዝግጅቶች።
    - ሸ. የደህንነት እርምጃዎች።
4. በሚሰጡት አገልግሎት መሰረት ሪፈራል ዝርዝር እና ክላስተር ድርጅቶችን ይፍጠሩ፣
5. ዝርዝሩን ለሁሉም ሰራተኞች ያሰራጩ፤ ዝርዝሩ መቼ እንደሚገለጽ እና በአገልግሎቶቹ ላይ እንዴት አስተያየት መስጠት እንደሚችሉ ወይም አዲስ አገልግሎቶችን እንደሚጠቁሙ መረጃ በመያዝ፣
6. ለሁሉም ሰራተኞች ተደራሽ የሆነ ዝርዝር ስሪቶች ያትሙ እና በቢሮ ውስጥ ፖስተር ያስቀምጡ፣
7. ሚስጥራዊነትን እና በመረጃ ላይ የተመሰረተ ስምምነትን ጨምሮ ወደ ውጫዊ አገልግሎቶች ለመዘዋወር በመረጃ መጋራት ስርዓት ፕሮቶኮሎች ላይ አጭር ማስታወሻ ለሰራተኞች ይስጡ። ሰርቫይቨሮች አገልግሎቶችን ለማግኘት ታሪካቸውን እንዲደግሙ እንዳይጠየቁ የውስጥ ቅንጅትን ያረጋግጡ፣
8. በሪፈራል መንገዶች ላይ ያሉ ክፍተቶችን ስለመፍታት ከሰርቫይቨሮች ጋር ተነጋገሩ። መረጃ በሃገር ውስጥ ቋንቋ መተላለፍ እና የተለያየ የመጻፍ/የማንበብ ደረጃን ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት። ሰርቫይቨሮች በአገልግሎቶቹ ላይ ግብረመልስ የሚሰጡበት ዘዴ መኖር አለበት፣
9. አገልግሎቶችን በየጊዜው ይከታተሉ።

## 2.3.2. አእምሮ ጤና እና ማህበራዊ-ስነልቦና ድጋፍ አገልግሎቶችን መረዳት

‘የአእምሮ ጤና እና የማህበራዊ-ስነልቦና ድጋፍ’ የሚለው ቃል በሰዎች የስነ-ልቦና ገጽታዎች እና በአካባቢያቸው ወይም በማህበራዊ አከባቢዎች መካከል ያለውን መስተጋብር ለመግለጽ ያገለግላል። ስነ ልቦናዊ ገጽታዎች እንደ ሃሳባችን፣ ስሜታችን እና ባህሪያችን ካሉ ተግባራችን ጋር የተያያዙ ናቸው። ማህበራዊ አከባቢዎች የአንድን ሰው ግንኙነቶች፣ የቤተሰብ እና የማህበረሰብ አውታረ መረቦች፣ የባህል ወጎች እና የኢኮኖሚ ሁኔታን ጨምሮ፣ ትምህርት ቤት ወይም ወደ ስራ እንደ መሄድን የመሳሰሉ የህይወት ተግባራትን ያካትታል።

‘ማህበራዊ-ስነልቦና’ የሚለው ቃል የአንድ ሰው አእምሮአዊ ደህንነት የሚወሰነው በስነ ልቦናዊ ባህሪው ብቻ እንዳልሆነ እና ማህበራዊ ሁኔታዎችንም እንደሚያካትት ለማሳወቅ ‘ሳይኮሎጂካል’ የሚለዉን ቃል በመተካት ጥቅም ላይ ይውላል። ‘ማህበራዊ’ እና ‘ስነ-ልቦናዊ’ ምክንያቶች እርስ በርስ የሚደጋገፉ እና ለአጠቃላይ ማህበራዊ-ስነልቦና ደህንነት አስተዋፅኦ የሚያደርጉ ናቸዉ። አንድ ሰው የራሱን ስሜት እንዴት እንደሚያዳብር፣ ማንነቱን እንዴት እንደሚረዳ እና እርሱ እራሱ ከሌሎች ሰዎች እና ከተለያዩ ማህበረሰቦች ጋር ያለውን ግንኙነት እንዲገነዘብ ያበረታታሉ። የዩሪ ብሮንፈንብነር Socioecological Theory[3] በሰዎች እና በአካባቢያቸው መካከል ያለውን መገናኛዎች አስመልክቶ ጥልቅ ጽንሰ-ሀሳብ ያቀርባል። ማክሮ ሲስተም ውስጥ፣ ማህበረ-ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ገጽታዎች እና ለውጦች በማደግ ላይ ያለ ሰው ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ ማብራሪያ ይሰጣል። ይህም በተለያዩ የስርዓቶች መረጋጋት ላይ መስተጓጎል በሚፈጠርባቸው የሁከት ሁኔታዎች ውስጥ ጉልህ ይሆናል፣ ይህም የአንድን ሰው ስነ-ልቦናዊ ደህንነት የበለጠ የሚነካ እና በመጨረሻም ከጥቃት ጋር የተያያዙ ጉዳቶች እና ሌሎች የአእምሮ ጤና ችግሮችን ለመፈወስ በየትኞቹም መንገዶች ሊጀምሩ ይችላሉ።




የአእምሮ ጤና እና የማህበራዊ ስነ-ልቦና ድጋፍ አገልግሎቶች የአንድ ግለሰብ የአእምሮ ጤና ከሁለቱም ማለትም ከስነ-ልቦናዊ እና ማህበራዊ ሁኔታዎች ጋር በጥልቀት የተሳሰሩ መሆናቸውን ይገነዘባሉ፣ እናም እነዚህ አካላት በብዙ መንገዶች የተሳሰሩ ናቸው፦

- **የማህበራዊ የስነ-ልቦና ተፅእኖ ምክንያቶች**፦ እንደ ግለሰባዊ ጥቃት፣ አድልዎ እና መገለል ያሉ ማህበራዊ ልምዶች ወደ ስነ ልቦናዊ ጭንቀት እና የአእምሮ ጤና ጉዳዮች ሊመሩ ይችላሉ። ለምሳሌ፣ በአሰቃቂ ተግባራት ምክንያት ማህበራዊ መገለል ያጋጠመው ሰው ጭንቀት ወይም ድብርት ሊያዳብር ይችላል።
- **ማህበራዊ ድጋፍ እንደ መከላከያ ምክንያት፦** የጭንቀት እና የስሜት ቀውስን፣ የስነ-ልቦና ተፅእኖን በመቀነስ ረገድ ማህበራዊ ድጋፍ ወሳኝ ሚናን ይጫወታል። ደጋፊ ግንኙነቶች እና የማህበረሰብ ግንኙነቶች የስነ-ልቦና ጭንቀትን አሉታዊ ተፅእኖዎች መከላከያ አርማታ (Buffer) ይሆናሉ።
- **የትብብር ፈውስ፦** ውጤታማ የአእምሮ ጤና እና የማህበራዊ ስነ-ልቦና ድጋፍ አገልግሎቶች በስነ-ልቦና እና በማህበራዊ ድጋፍ ሰጭዎች መካከል የሚደረገዉን ትብብር ያካትታሉ።

ለምሳሌ፣ ከአሰቃቂ ሁኔታ የተረፈ ሰው ከሁለቱም ማለትም ከግለሰብ ሕክምና (የስነ ልቦና ድጋፍ) እና በድጋፍ ቡድኖች ወይም በማህበረሰብ እንቅስቃሴዎች (ማህበራዊ ድጋፍ) በመሳተፍ ሊጠቀም ይችላል።

- **ሁለንተናዊ ደህንነት፡-** ሁለቱንም ማለትም የስነ ልቦናዊ እና ማህበራዊ ጉዳዮችን በማንሳት የአእምሮ ጤና እና የማህበራዊ-ስነልቦና ድጋፍ የአእምሮ ጤናን እና ደህንነትን ለማሳደግ አጠቃላይ አቀራረብን እንደሚጠይቅ ያስገነዝባሉ። ግለሰቦች በማህበራዊ አውድ ውስጥ እንዳሉ እና የስነ ልቦና ጤንነታቸው ከማህበራዊ አካባቢያቸው ጋር በቅርበት የተገናኘ መሆኑን እና በተለያዩ ማህበረሰባቸው እና ስርዓቶቻቸው ውስጥ ያሉትን ሀብቶች ምን ያህል ማሰስ ይችላሉ ከሚለዉ ጋር እንደሚተሳሰር እውቅና ይሰጣል።

በአጠቃላይ፣ የአእምሮ ጤና እና የማህበራዊ ስነ-ልቦና ድጋፍ አገልግሎቶች የግለሰቦች የአዕምሮ ጤና የስነ-ልቦና ደህንነታቸው ውጤት ብቻ ሳይሆን ይልቁንም በማህበራዊ ግንኙነታቸው፣ በግንኙነቶቻቸው እና በሰፊው ማህበራዊ አውድ ትልቅ ተጽዕኖ ስር እንደሚወድቅ ያስገነዝባሉ። የአዕምሮ ጤናን ዘርፈ ብዙ ተፈጥሮ የሚዳስስ አጠቃላይ እና ሰውን ያማከለ እንክብካቤ ለመስጠት ሲባል ውጤታማ የአእምሮ ጤና እና የማህበራዊ ስነ-ልቦና ድጋፍ አገልግሎቶች እነዚህን ተያያዥነት ያላቸውን ልኬቶች ከግምት ውስጥ ያስገባሉ። ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ሰርቫይቨሮች የሚሰጡ ውጤታማ አገልግሎቶች አሰቃቂ ሁኔታን የተቃኙ እና የአሰቃቂው ሁኔታ መጠነ ሰፊ ተጽእኖ የአሰቃቂ ሁኔታ ሰርቫይቨሮች የአእምሮ ጤናን ብቻ ሳይሆን ከአሰቃቂ ገጠመኞች ለማገገም ከሚያስፈልጋቸው የአእምሮ ጤና እና የማህበራዊ ስነ-ልቦና ድጋፍ አገልግሎቶች ጋር እንዴት መሳተፍ እንደሚችሉም ይጨምራል።


### 2.3.3. ወደ አእምሯዊ ጤና እና የማህበራዊ ስነ-ልቦና ድጋፍ አገልግሎቶች ሪፈር ማድረግ፡-

የአእምሮ ጤና እና የማህበራዊ ስነ-ልቦና ድጋፍ አገልግሎት መስፈርቶች እንደየ ሀገሪቱ ሁኔታ ይለያያሉ። ሰርቫይቨሮችን ወደ አእምሯዊ ጤና እና የማህበራዊ ስነ-ልቦና ድጋፍ አገልግሎቶች ሪፈራል ሲያደርጉ በሪፈራል ዝርዝሩ ውስጥ ያሉ ተቋማት የሚያቀርቡትን የአገልግሎት ዓይነቶች እና እነዚያን አገልግሎቶች የሚሰጡ ዋና ሰራተኞችን መግለጽ መቻል አለባቸው። ከሰርቫይቨሮች ጋር በቀጥታ የሚሰሩ ተቋማት እና ሰራተኞች የአእምሮ ጤና እና የማህበራዊ ስነ-ልቦና ድጋፍ አገልግሎቶችን የሚሰጡ ድርጅቶችን አጠቃላይ ሪፈራል ዝርዝር እንዲኖራቸው የግድ አስፈላጊ ነው።

የሚከተለው ፒራሚድ በአእምሮ ጤና እና ማህበራዊ ስነ-ልቦና ድጋፍ አገልግሎቶች ሰፊ ወሰን ውስጥ የተካተቱትን የስራ ባህሪ የሚያሳይ ምሳሌን ይሰጣል። የሚከናወኑትን መፍትሄ ዓይነቶች እና በእንክብካቤ ክፍሎች መካከል የሚደረገውን የሪፈራል አቅጣጫዎች ያሳያል። አንዳንድ ድርጅቶች ሥራውን በሚሠሩት ሠራተኞች ልዩ ሙያዎች ላይ በመመስረት የተወሰነ የአገልግሎት መጠን ሊሰጡ ይችላሉ።

በብዙ ጥሩ ሃብት ባላቸው አውድ ውስጥ፣ አንዳንድ ተቋማት በፒራሚዱ ውስጥ የተመለከቱትን የተለያዩ አገልግሎቶች መስጠት ሲችሉ ሌሎች ተቋማት ደግሞ በአእምሮ ጤና እና ማህበራዊ ስነ-ልቦና ድጋፍ አገልግሎቶች የተወሰኑ ገጽታዎች ላይ ያተኩራሉ። የአገልግሎት አቅርቦት ብዙውን ጊዜ የተሻለ ምቹ የሚሆነዉ ተቋማት ሰርቫይቨሮች የፈውስ ሂደቶችን ያለምንም ችግር እንዲያገኙ ወይም ከፍላጎታቸው ጋር በቀጥታ የተገናኙ መፍትሄ ማግኘት የሚያስችል የሪፈራል መንገዶችን ሲያሳድጉ ነው።

**ከግጭት ጋር ለተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት የማህበራዊ-ሥነልቦና ፈውስ ስልትን የሚወክል።**
ከSAITS ሞዴል የተወሰደ (Higson-Smith, C., 2005)



ፒራሚዱ መዳረሻቸውን እና በተወሰነ አውድ ውስጥ የሚፈለገውን የአእምሮ ጤና እና የማህበራዊ ስነ-ልቦና ድጋፍን መሰረት በማድረግ የመፍትሄ ባህሪ ለመግለጽ ደረጃ በደረጃ የተቀመጠ ነው። እንደ ምሳሌ፣ አንዳንድ የአገልግሎት ጣልቃገብነቶች በስነልቦና ትምህርት ላይ ያተኮሩ ናቸው፣ ይህም ለጥቃት ከተጋለጡ ስብስቦች ጋር አብሮ መስራትን ሊያካትት ይችላል። እንደዚህ ያሉ ጣልቃ ገብነቶች ቀጣይነት ባላቸው፣ የተደራጁ ሁከቶች በነበሩባቸው አውዶች ውስጥ ቁልፍ የሆኑ ጣልቃ ገብነቶች ናቸው፣ እነዚህም ብዙውን ጊዜ በህብረተሰቡ ማህበራዊ-ፖለቲካዊ መዋቅር ወይም በሃገሪቱ ሁኔታ ውስጥ ሥር የሰደዱ ናቸዉ። የስነ ልቦና ትምህርት ክፍለ ጊዜዎችን የሚያካሂዱ ባለሙያዎች እንደየዐውዱ ከአእምሮ ጤና እና ማህበራዊ ስነ-ልቦና ድጋፍ አገልግሎቶች ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን መረጃዎችን ለግንዛቤ እና ትምህርታዊ ዓላማዎች ለማሰራጨት የታጠቁ ናቸው። የስነ-ልቦና ትምህርቶችን የሚያመቻቹ ባለሙያዎች ብዙውን ጊዜ አንድ ሰው በውይይት ርእሶች ባህሪ ምክንያት ጭንቀት ሲያጋጥመው ለይተው ማወቅ እና በክፍለ-ጊዜው ውስጥ ጭንቀትን ለማስወገድ ስሜትን መቆጣጠርያ ፈውስ መስጠት ይችላሉ።[4] አስተባባሪው ባለሙያ የምክር አገልግሎት መስጠት ካልቻለ፣ ሰርቫይቭሮች (በእነሱ ፈቃድ) ተገቢውን የምክር ወይም የሕክምና አገልግሎቶችን ወደሚሰጥ ድርጅት ወይም ባለሙያ ይልካሉ። የግንዛቤ ማስጨበጫ ዝግጅቶች፣ ንግግሮች፣ ወይም ሌሎች የአእምሮ ጤና እና የስነ-ልቦና-ማህበራዊ ድጋፍ አገልግሎት ጣልቃገብነቶች ላይ የሚሳተፉ ሰዎች አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አግባብነት ያላቸውን አገልግሎቶች ማግኘት እንዲችሉ እና እንደገና መጎዳትን እና ጉዳትን ለመቅረፍ ጣልቃ ገብነቶች እና ክስተቶች በአሰቃቂ ሁኔታ ላይ ያተኮሩ ከሆነ ይህ የሪፈራል ሂደት ወሳኝ ነው።

የተደራሽነት አገልግሎት ወይም የስነ-ልቦና ትምህርት አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች ሰርቫይቭሮች ያጋጠማቸው የጭንቀት ደረጃዎች ተቋሙ ከሚሰጣቸዉ የአእምሮ ጤና እና የማህበራዊ ስነ-ልቦና ድጋፍ አገልግሎት መፍትሄ ወሰን ውጭ መሆናቸውን ለይተው ካወቁ የሪፈራል/ማስተላለፊያ ሂደታቸው ምን እንደሚመስል ማሳየት መቻል አለባቸው። እነዚህ ድርጅቶች ብዙዉን ጊዜ በአመጽ የተጎዱ ማህበረሰቦች ደህንነት ላይ በማተኮር አገልግሎት ይሰጣሉ።

በተጨማሪም፣ ምንም እንኳን አንድ ድርጅት ከጥቃት ጋር በተያያዙ ጉዳቶች ላይ በመስራት ረገድ ብቁ እና ልምድ ያላቸው የስነ-ልቦና ባለሙያዎች እና የማህበራዊ ሰራተኞች ቡድን እንዳለው ማሳየት ቢችልም፣ ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ሰርቫይቭሮች ጋር የመሥራት ታሪክ ሊኖራቸው ይገባል፣ እንዲሁም የረጅም ጊዜ የደንበኛ ስራን ለመውሰድ አቅማቸውን እና ሀብታቸውን ጭምር ማሳየት መቻል አለባቸው። በሪፈራል ሂደቶች ውስጥ ተፈጥሮ ባደጉ ግንኙነቶች ምክንያት፣ እንደነዚህ ያሉ ድርጅቶች የጥቃት ሰርቫይቨሮች ባሉባቸው ማህበረሰቦች ውስጥ ለሚሰሩ ባለሙያዎች የክትትል፣ የአቅም ግንባታ ወይም ማብራሪያ ከመስጠት ጋር የሚያያዙ ድጋፎችን ለመስጠት በበቂ ሁኔታ ላይ ይቀመጣሉ።

የአይምሮ ጤና እና የማህበራዊ ስነ-ልቦና ድጋፍ አገልግሎቶች ፒራሚድ የግድ ተዋረዳዊ አይደለም፣ ነገር ግን ወደ አእምሮ ጤና፣ ማህበራዊ ስነ-ልቦና እና/ወይም የአእምሮ ጤና እና የማህበራዊ ስነ-ልቦና አገልግሎቶች የመግቢያ በርካታ ነጥቦችን ይወክላል። የማህበራዊ ስነ-ልቦና ድጋፍን የሚሰጡ ተቋማት የአእምሮ ጤና አጠባበቅ አገልግሎት ለመስጠት ብቁ ሰራተኞች ላይኖራቸው ይችላል። በተመሳሳይ፣ የሳይካትሪ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ጥልቅ የስነ-አእምሮ ሕክምና አገልግሎቶችን በውጭ ለማቅረብ የሚፈለጉ ብቁ እና ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች ላይኖራቸው ይችላል፣ (ለምሳሌ) የባዮሜዲካል ሞዴል፣ በተለምዶ የሕክምና(የመድኃኒት) መፍትሄዎችን እና ከአእምሮ ህመም ጋር የሚገናኙ የአመራር ዘዴዎችን ያካትታል።

## 2.4. ሁለንተናዊ የድጋፍ አገልግሎቶች — ውጪያዊ ሰነዶች

**2.4.1** Global Initiative for Justice, Truth and Reconciliation (GIJTR), Providing Psychosocial Support for Survivors of Conflict: A toolkit based on experiences from Sri Lanka https://gijtr.org/wp-content/uploads/2021/09/GIJTR-CSVR-6x9-toolkit-EN-final.pdf (በእንግሊዘኛ ቋንቋ ይገኛል)።

**2.4.2** Dr. Denis Mukwege Foundation, Handbook on Holistic Care for Survivors of Sexual Violence in Conflict: https://mukwegefoundation.org/wp-content/uploads/2019/07/Handbook-Care_for_SV_Survivors-ENG-screen.pdf (በእንግሊዘኛ ቋንቋ ይገኛል)።

**2.4.3** All Survivors Project, The Health of Male and Lesbian, Gay, Bisexual and Transgender and Other Nonconforming Individuals (LGBT+) Survivors of Conflict-Related Sexual Violence https://allsurvivorsproject.org/the-health-of-male-and-lgbt-survivors-of-conflict-related-sexual-violence/ (በእንግሊዘኛ ቋንቋ ይገኛል)።

**2.4.4** Global Initiative for Justice, Truth and Reconciliation (GIJTR), Truth, Bread and Tea: A Toolkit for Reintegration of Women Survivors of Conflict-Related Sexual Violence and Children Born of War https://gijtr.org/reintegration-and-transitional-justice/ (በእንግሊዘኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ስፓኒሽ፣ አረብኛ እና ሌሎች ቋንቋዎች ይገኛል)

## 3.1. እውነትን ይፋ ማድረግ እና ስነዳ — ውጪያዊ ሰነዶች

3.1.1. Institute for International Criminal Investigations, Global Code of Conduct for Gathering and Using Information about Systematic and Conflict-Related Sexual Violence (the Murad Code) (2022) https://www.muradcode.com/murad-code (በእንግሊዘኛ፣ አረብኛ፣ በኩርዲሽ፣ አማርኛ፣ ትግርኛ፣ ስዋህሊ፣ ኖስንያን፣ ፈረንሳይኛ፣ ሽፓኒሽ፣ ዩክሬንያን፣ ኔፓሊ እና ቡርሜስ ይገኛል)።

3.1.2 UK Foreign & Commonwealth Office, International Protocol on the Documentation and Investigation of Sexual Violence in Conflict (Second Edition) https://assets.publishing.service.gov.uk/media/5a803e9640f0b62305b8a06b/International_Protocol_2017_2nd_Edition.pdf (በእንግሊዘኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ስፓኒሽ፣ አረብኛ እና ሌሎች ቋንቋዎች ይገኛል)

3.1.3 Synergy for Justice, Syria Supplement to the Second Edition of the International Protocol on the Documentation and Investigation of Sexual Violence in Conflict https://synergyforjustice.org/syria-supplement (በእንግሊዘኛ እና በአረብኛ ይገኛል)።

3.1.4 Institute for International Criminal Investigations, Iraq Supplement to the Second Edition of the International Protocol on the Documentation and Investigation of Sexual Violence in Conflict https://iici.global/0.5.1/wp-content/uploads/2018/03/Iraq-IP2-Supplement_English_Online.pdf (በእንግሊዘኛ እና በአረብኛ ይገኛል)።

3.1.5 Case Matrix Network and Commission for International Justice and Accountability (CIJA), Central African Republic Supplement to the Second Edition of the International Protocol on the Documentation and Investigation of Sexual Violence in Conflict https://www.legal-tools.org/doc/b2e51b/pdf/ (በእንግሊዘኛ ይገኛል)።

3.1.6 RedressInstitute for International Criminal Investigations and REDRESS, Myanmar Supplement to the Second Edition of the International Protocol on the Documentation and Investigation of Sexual Violence in Conflict https://redress.org/wp-content/uploads/2018/03/Myanmar-IP2-Supplement_English_Online.pdf (በእንግሊዘኛ እና ቡርሜስ ቋንቋ ይገኛል)።

3.1.7 Institute for International Criminal Investigations and REDESS, Sri Lanka Supplement to the Second Edition of the International Protocol on the Documentation and Investigation of Sexual Violence in Conflict https://iici.global/0.5.1/wp-content/uploads/2018/03/20190315-Sri-Lanka-IP2-Supplement_Online.pdf (በእንግሊዘኛ ሲንሃላ እና ታሚል ቋንቋ ይገኛል)።

3.1.8 UN Office of the United Nations High Commissioner for Human Rights, Istanbul Protocol: Manual on the Effective Investigation and Documentation of Torture and Other Cruel, Inhuman or Degrading Treatment or Punishment https://www.ohchr.org/en/publications/policy-and-methodological-publications/istanbul-protocol-manual-effective-0 (በእንግሊዘኛ፣ፈረንሳይኛ፣ስፓኒሽ አረብኛ እና ሌላ ቋንቋ ይገኛል)።

3.1.9 Synergy for Justice, technical guidance on Forensic Medical Evaluations of Torture and Sexual Violence https://synergyforjustice.org/technical-guidance (በእንግሊዘኛ እና በአረብኛ ይገኛል)።

3.1.10 Institute for International Criminal Investigations, Guidelines on Remote Interviewing https://iici.global/publications/ (በእንግሊዘኛ፣ ስፓኒሽ፣ እና ፈረንሳይኛ ይገኛል)።

3.1.11 Global Initiative for Justice, Truth and Reconciliation (GIJTR), Creating Channels of Trust: Community Truth-Telling in Outlying Regions in Colombia https://gijtr.org/our-work/colombia/ (በእንግሊዘኛ፣ ስፓኒሽ፣ እና ፈረንሳይኛ ይገኛል)።

## 4.1 ፍትህ እና ተጠያቂነት—ውጪያዊ ሰነዶች

4.1.1 Philip Schulz and Kathrin Kreft, Accountability for Conflict-Related Sexual Violence, https://doi.org/10.1093/acrefore/9780190846626.013.702 (በእንግሊዘኛ ይገኛል)።

4.1.2 The US Holocaust Memorial Museum's Handbook for Victim Groups Pursuing Justice for Mass Atrocities: Chapter 3 'Using Law to Access Justice and Accountability for Mass Atrocities' https://www.ushmm.org/m/pdfs/USHMM-Pursuing-Justice-for-Mass-Atrocities.pdf (በእንግሊዘኛ፣ አረብኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ራሻኛ እና በዩክሬን ቋንቋ ይገኛል)።

**4.1.3** UN Women, Documenting good practice on accountability for conflict-related sexual violence: the Sepur Zarco case https://reliefweb.int/report/guatemala/documenting-good-practice-accountability-conflict-related-sexual-violence-sepur-zarco-case (በእንግሊዘኛ ይገኛል)።

**4.1.4** OHCHR, A Practitioners Toolkit on Women's Access to Justice Programming https://www.ohchr.org/sites/default/files/Documents/Publications/PractitionerToolkit/WA2J_Consolidated.pdf (በእንግሊዘኛ ይገኛል)።

**4.1.5** International Justice Monitor, The Kavumu Trial: Complementarity in Action in the Democratic Republic of Congo https://www.ijmonitor.org/2018/02/the-kavumu-trial-complementarity-in-action-in-the-democratic-republic-of-congo/ (በእንግሊዘኛ ይገኛል)።

# 5. ማካካሻ— የምሳሌ ሰነዶች

## 5.1.1. በማካካሻ ዐውድ ውስጥ "ተጎጂ" የሚለውን የሚያሟላ ማን ነው?

ከጉዳት ካሳ አንፃር ሲታይ፣ "ተጎጂዎች" የሚለው ጽንሰ ሐሳብ የሚያመለክተው አካላዊ ወይም አዕምሯዊ ጉዳት፣ ስሜታዊ ሥቃይ፣ የምጣኔሃብታዊ ኪሳራ ወይም መሠረታዊ መብቶች ላይ ከፍተኛ ጉዳት በግለሰብም ሆነ በቡድን ደረጃ ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች የሚያመለክት ሲሆን፤ ይህም በድርጊት ወይም ባለማድረግ (omission) የሚፈጸም ከፍተኛ የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ሕግ ጥሰት ወይም ከባድ የዓለም አቀፍ የጦርነት ሕግ ጥሰትን የሚያስከትል ነው። እንደ አስፈላጊነቱ እንዲሁም በሃገር ውስጥ ሕግ መሰረት፣ "ተጎጂ" የሚለው ቃል የቅርብ ቤተሰብን ወይም የቀጥታ ተጎጂውን ጥገኛ እና በችግር ጊዜ የተጎዱ ሰዎችን ለመርዳት ወይም ተጎጂዎች ላይ ሊደርስ የነበረውን ጥቃት ለመከላከል ጣልቃ በመግባት ጉዳት የደረሰበትን ሰው ያጠቃልላል። ጥቃቱን የፈጸመው ሰው ማንነቱ ቢታወቅ፣ ቢታሰር፣ ቢከሰስ ወይም ቢፈረድበት እንዲሁም በፈፃሚውና በተጎጂው መካከል ያለው ዝምድና ምንም ይሁን ምን፣ ተጎጂው እንደ ተጎጂ ተደርጎ ይቆጠራል። በጦርነት ውስጥ የተወለዱ ሕፃናት የጥቃት ተጎጂዎች ናቸው።

## 5.1.2 ተጎጂዎች ማካካሻ ማግኘት የሚችሉት እንዴት ነው?

የጉዳት ካሳ ለማግኘት፣ ለተጎጂዎች ውጤታማ የፍትህ እና/ወይም አስተዳደራዊ የሆኑ እርምጃዎች ሊቀርብላቸው ይገባል። ምንም እንኳ በተጎጂዎች በተለይም ከግጭት ጋር የተያያዙ ወሲባዊ ጥቃቶች ሰርቫይቨሮችን ሸክም ለመቀነስ አስፈላጊ የሆኑ ለውጦች ቢከናወኑም፣ ተጎጂዎች በፍርድ ቤቶች በኩል ካሳ ለማግኘት ሲሞክሩ አብዛኛውን ጊዜ ጥሰቱ መኖሩን እና የደረሰውን ጉዳት በማስረጃ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል። ከጅምላ ጭፍጨፋ ጋር በተያያዘ ያሉ የማጣራት ሂደቶች ብዙ ዓመታትን የሚወስዱ በመሆኑ ፍርድ ቤቶች ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ አይችሉም። ለዚህም ነው ከግጭት ጋር የተያያዙ ወሲባዊ ጥቃቶች (ግየወጥ) የተረፉ ሰዎችን ጨምሮ ለተጎጂዎች በቂ፣ ፈጣንና ውጤታማ የሆነ የጉዳት ካሳ ለማቅረብ በአገር ውስጥ በሚካሄዱ የካሳ መርሃግብሮች በመጠቀም የአስተዳደር እርምጃዎች አስፈላጊ የሚሆኑት። የተመድ ልዩ የእውነት፣ የፍትህ፣ የጉዳት ካሳ፣ እና ጥቃት ድጋሜ እንዳይፈጸም የዋስትና የማስፋፊያ ዘጋቢ (UN Special Rapporteur on the Promotion of Truth, Justice, Reparation, and Guarantees of Non-recurrence) እንደጠቆመው ከቀረቡላቸው ክሶች ወይም ጥያቄዎች ውጪ ማየት ከማይችሉ እና አዘውትረው ከፍተኛ የማስረጃ ደረጃዎችን ከሚጠይቁ ከፍርድቤት ትዕዛዞች ጋር ሲነፃፀር፣ የአገርውስጥ አስተዳደራዊ የካሳ መርሃግብሮች አብዛኛውን ጊዜ በዝቅተኛ የማስረጃ መስፈርቶች ብዙ ቁጥር ላላቸው ተጎጂዎች የተለያዩ የካሳ አይነቶችን ሊያቀርቡ እንደሚችሉ ገልጿል።

## 5.1.3 ማካካሻ ምን ምን ዓይነት ቅርጾች ሊኖሩት ይችላል?

ማካካሻ ለግለሰብ ተጎጂዎች ወይም ለሁሉም የአንድ ቡድን ተጎጂ አባላት ወይም ለተወሰኑ ምድቦች ብቻ ሊከፈል ይችላል። መጠነ ሰፊ ውጤቶችን የሚያስከትሉ ጭካኔ እና ግፍ በሚፈፀሙበት ሁኔታ፣ በግለሰብም ሆነ በቡድን ደረጃ የሚከፈሉ ካሳዎች ብዙውን ጊዜ አስፈላጊና ተገቢ እንደሆኑ ተደርገው ይቆጠራሉ። በተ.መ.ድ የማካካሻ መሰረታዊ መርሆች እና መመሪያዎች መሰረት፣ ለግለሰቦችም ሆነ ለቡድኖች ሊቀርቡ የሚችሉ የጉዳት ማካካሻዎች በሚከተሉት መልክ ሊታዩ ይችላሉ፦

1. **መልሶ ማቋቋም** የአንድን ሰው መብት በተቻለ መጠን ወደ ነበረበት ለመመለስ የሚሻ የጉዳት ካሳ አይነት ነው። ይህም ነጻነታቸውን፣ ዜግነታቸውን፣ ሥራቸውን፣ የትምህርት እድሎችን ወይም ያጡትን ወይም የተሰረቀ ንብረታቸውን ማስመለስን የመሳሰሉ ድርጊቶችን የሚያካትት ነው።
2. **ካሳ** ይህ የካሳ አይነት የገንዘብ ክፍያ ሲሆን አብዛኛውን በአንድ ጊዜ የሚደረግ ክፍያ፣ በየጊዜው በቋሚነት የሚደረግ ክፍያ ወይም ከቀረጥ ነፃ ከማድረግ ጋር በተያያዘ የሚከፈል ነው። ይህም የሚሰጠው የቤተሰብ አባላትን በሞት፣ ተግባሮችን ወይም ንብረቶችን በሚያጡበት ወይም ከጉዳቱ አንፃር ሲታይ የኢኮኖሚ ድጋፍ ተገቢና ተመጣጣኝ እንደሆነ ተደርጎ በሚታሰብበት ጊዜ ነው።
3. **መልሶ ማቋቋም** ደግሞ በሐዘንና በአሰቃቂ ሁኔታ ላይ ለሚገኙ ግለሰቦች የጤና እንክብካቤና ሥነልቦናዊ፣ የሥነ አእምሮና ማኅበራዊ ድጋፍ መስጠትን ጨምሮ የሕክምና አገልግሎት ማቅረብን ይመለከታል። ከዚህም ባለፈ ተጠቃሚዎች ይበልጥ እርካታ ያለው ሕይወት እንዲመሩ ሥልጣን ለመስጠት የሚያስችሉ ተያያዥ ህጋዊና ማህበራዊ አገልግሎቶችንም ያጠቃልላል።

4. **የመንፈስ እርካታ** ይህም ስለደረሰው ጉዳት በሕዝብ ፊት እውቅና ለመስጠትና ለሕብረተሰቡ ግንዛቤ ለማሳደግ የሚወሰዱ እርምጃዎችን ይጨምራል። ይህም ከተጠያቂዎቹ ይቅርታ መጠየቅን፣ የተገደሉትን አስከሬን ወይም የጠፉ ሰዎችን ማግኘትን፣ ቀደም ሲል ስለተፈጸመ ጥቃት ትክክለኛ ዘገባን በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ማካተትን፣ እና ያለፈውን እውነት መግለጥን እና መዘከርን ሊያጠቃልል ይችላል።

5. **ዳግም እንዳይከሰት የሚወሰዱ** እርምጃዎች ያለመጠቃት ዋስትና ያለፉት የጭካኔ ድርጊቶች እንዳይደገገሙ ለመከላከል የተነደፉ እርምጃዎችን የሚያጠቃልል ነው። ይህ ደግሞ ተቋማትን ማሻሻልን፣ አከባቢያዊ የግጭቶች የመፍቻ ዘዴዎችን ማቋቋምን፣ የፍትሕ ነፃነትን ማጠናከርንና በተለያዩ ዘርፎች የሰብአዊ መብት መስፈርቶችን ማስፋፋትን ሊያጠቃልል ይችላል።

### 5.1.4. ሰርቫይቨሮች የማካካሻ መርሃግብሮችን ንድፍ እንዴት ሊቀርጹ ይችላሉ?

ለማገዝ ባሰቧቸው ሰዎች ላይ ትርጉም ያለውና ጠቃሚ ተጽዕኖ ለማሳደር የሰርቫይቨር መረቦችና የሲቪል ኅብረተሰብ ድርጅቶች የማካካሻ መርሃግብሮችን በመቅረጽ ረገድ ወሳኝ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ። ንድፍ ተዘጋጅቶ ካለቀ በኋላ የሚነሱ ጉዳዮችን ማስተካከል አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፤ ይህ ደግሞ በሕይወት መትረፍ የሚችሉ ሰዎች እንዲገለሉ ወይም የታሰበውን የማካካሻ ጥቅሞችን እንዳያስገኙ ሊያደርግ ይችላል። ስለዚህ ሰርቫይቨሮች በመርሃግብሩ ንድፍ ደረጃ ላይ በንቃት ቢሳተፉ በጣም ይመረጣል።

ሰርቫይቨር ቡድኖች የሚከተሉትን ጨምሮ በርካታ ቁልፍ አላባዎች ላይ ሊወተውቱ ይችላሉ፦

1 **ቋሚ የማማከር ሂደት፦** ተጎጂዎች እና ተጎጂ ማህበረሰቦች በልዩ ልዩ የማካካሻ እርከኖች ወደ መርሃ ግብሩ የሚገቡትን ልዩ ልዩ ምኞቶች እና ፍላጎቶች ጋር የሚስማማ መሆኑን በማረጋገጥ በፕሮግራሙ ውስጥ የሚካተቱትን ልዩ ልዩ እርምጃዎች ላይ ግብአት የሚያቀርቡበት ቋሚ የምክክር ሂደት እንዲካሄድ ግፊት ማድረግ ይችላሉ።

2 **ለቀቅ ያለ የቅድመ ሁኔታ፦ መስፈርቶች** የጥቃቱ ሰለባዎች ክሳቸውን የሚደግፍ ማስረጃ በማግኘትና በማቅረብ ረገድ የገጠማቸውን ችግሮች በመገንዘብ፣ የጥቃቱ ሰለባ የሆኑ ቡድኖች መስፈርቱን ለማሟላት ይበልጥ ለቀቅ ላለ የማስረጃ መሥፈርቶች ሊወተውቱ ይችላሉ። እንዲህ ያለው ለቀቅ ያለ መስፈርት በቢሮክራሲያዊ እንቅፋቶች ሳቢያ ጉዳት እንዳይደርስባቸው እና እንዳይገለሉ ሊከላከል ይችላል።

3 **ለአደጋ የተጋለጡ ተጎጂዎችን ማስቀደም፦** ለአደጋ የተጋለጡ ተጎጂዎች አጣዳፊ ፍላጎቶች በሚያሟላ መልኩ ቅድሚያ እንዲሰጣቸው የመወትወት ሂደት በጣም ከባድ የሆኑ ሁኔታዎች ያጋጠሟቸው ተጎጂዎች ወቅታዊ ድጋፍ እንዲያገኙ ይረዳቸዋል።

4 **አካታች አቤቱታ ማቅረቢያ ሂደት፦** የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ተፈናቃይ እና የስደተኛ ተጎጂዎች የማመልከቻ ሂደት ማግኘት የሚችሉበትን ለመመስረት ሊሰሩ ይችላሉ። ይህ ደግሞ እነዚህ ግለሰቦች የማካካሻ ከመፈለግ ሊያግዳቸው የሚችሉ እንቅፋቶችን ያስወግዳል።

5 **ክትትል እና ግምገማ፦** የማካካሻ መርሃግብር መተግበር ከጀምረ በኋላ እነዚህ ድርጅቶች ጥብቅ እና ግልፅ የሆነ ክትትልና ግምገማ ሂደት እንዲተገበር ሊያበረታቱ ይችላሉ። ይህም የመርሃግብሩን ውጤታማነት እና አስፈላጊ ማሻሻያዎችን የማድረግ ችሎታን በቀጣይነት መገምገም ያስችላል።

የሰርቫይቨሮች ኔትዎርኮች እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ልዩ የሆነ የማስተዋልና የአመለካከት እይታ ለአደጋ ለተጋለጡ ሰዎች ስላጋጠሟቸው ተሞክሮዎችና ፍላጎቶች ሊያቀርቡ ይችላሉ። የፕሮግራም ቀራጮች እነዚህን ልዩ ተፈታታኝ ሁኔታዎች እንዲያስቡ በማድረግ ስለ ተፈናቃዮች ቦታ እና ሁኔታ ጠቃሚ መረጃ ማቅረብ ይችላሉ። ሰርቫይቨሮች እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ አብዛኛውን ጊዜ ከሀገር ባለስልጣናት ይልቅ በአካባቢው ካሉ ተሞክሮዎች ጋር ይበልጥ እንደመተዋወቃቸው፣ የመርሃግብሩ ንድፍ እነዚህን የአካባቢ ልዩነቶች ያካተተ እንዲሆን እና ከመርሃግብሩ መባቻ ጀምሮ ሰርቫይቨሮቹን የተወሰኑ አካባቢዎች ወይም ንዑስ ቡድኖች የሚነኩትን ተፈታታኝ ሁኔታዎች እንዲፈታ ማረጋገጥ ይችላሉ።

## 5.2. ውጪያዊ ሰነዶች


5.2.1 Impunity Watch, Guidelines on Transformative Reparations: https://www.impunitywatch.org/guidelines-transformative-reparatio/ (በእንግሊዘኛ እና ስፓኒሽ ቋንቋ ይገኛል)።

5.2.2 The US Holocaust Memorial Museum's Handbook for Victim Groups Pursuing Justice for Mass Atrocities: Chapter 1 'Pursuing and Using Transitional Justice Measures' https://www.ushmm.org/m/pdfs/USHMM-Pursuing-Justice-for-Mass-Atrocities.pdf (በእንግሊዘኛ፣ በአረብኛ፣ በፈረንሳይኛ፣ ራሽያኛ እና በዩክሬን ቋንቋ ይገኛል)።

5.2.3 Global Survivors Fund, Annual Report 2022 https://www.globalsurvivorsfund.org/fileadmin/uploads/gsf/Documents/Resources/Reports/GSF_Annual_Report_2022_EN_Web.pdf (በእንግሊዘኛ ይገኛል)።

5.2.4 International Center for Transitional Justice, We Will Never Forget the Scars and Pains Of Conflict: Nepal Study on Opportunities for Reparations for Victims and Survivors of Conflict-Related Sexual Violence https://www.ictj.org/resource-library/we-will-never-forget-scars-and-pains-conflict-nepal-study-opportunities (በእንግሊዘኛ እና በኔፓል ቋንቋ ይገኛል)።

5.2.5 UNHCR, Guatemala: National Compensation Program—Government Agreement No.258-2003 and Its Reforms (2005) https://www.refworld.org/pdfid/5b6d98414.pdf (በስፓኒሽ ቋንቋ ይገኛል)።

## 6. ለውጥ እና መከላከል —ውጪያዊ ሰነዶች

6.1.1. International Coalition of Sites of Conscience, Pathways of Innovation: Civil Society Advancing Transitional Justice https://www.sitesofconscience.org/wp-content/uploads/2020/03/Pathways-of-Innovation-Toolkit-2.pdf (በእንግሊዘኛ እና ፈረንሳይኛ ይገኛል)።

6.1.2. The Global Initiative for Justice, Truth and Reconciliation (GIJTR), Strengthening Participation in Local-Level and National Transitional Justice Processes: A Guide for Practitioners https://gijtr.org/wp-content/uploads/2021/10/Community-Participation-Toolkit-online-1.pdf (በእንግሊዘኛ እና ታሚል ቋንቋ ይገኛል)።

6.1.3. UK Government, A Theory of Change for Addressing Conflict-Related Sexual Violence https://www.gov.uk/government/publications/preventing-sexual-violence-in-conflict-initiative-strategy/a-theory-of-change-for-addressing-conflict-related-sexual-violence#executive-summary (በእንግሊዘኛ ይገኛል)።

## 7. ማስታወሻ እና ትምህርት—ውጪያዊ ሰነዶች

7.1.1. Asia Justice and Rights (AJAR), Stone and Flower: A Guide to Understanding and Action for Women https://asia-ajar.org/resources/books-research/stone-flower-a-guide-to-understanding-and-action-for-women-survivors/#:~:text=%E2%80%9CStone%20%26%20Flower%3A%20A%20Guide,AJAR's%20work%20with%20women%20survivors (በእንግሊዘኛ፣ በቡርሜስ፣ ኢንዶኔዢያ ቋንቋ እና ቴቱም ቋንቋ ይገኛል)።

7.1.2. International Coalition of Sites of Conscience, Memory to Action Toolkit https://www.sitesofconscience.org/member_resources/from-memory-to-action-a-toolkit-for-memorialization/ (በእንግሊዘኛ፣ በፈረንሳይኛ፣ ስፓኒሽ እና ፖርቹጋል ቋንቋ ይገኛል)።

7.1.3. Tearfund, Transforming Masculinities: A manual to train Gender Champions and Faith Leaders https://learn.tearfund.org/en/resources/series/changing-gender-norms-transforming-masculinities/transforming-masculinities (በእንግሊዘኛ፣ በፈረንሳይኛ፣ ስፓኒሽ እና ፖርቹጋል ቋንቋ ይገኛል)።

7.1.4. International Coalition of Sites of Conscience, Body Mapping Toolkit https://www.sitesofconscience.org/wp-content/uploads/2018/12/Toolkit-Body-Mapping-2018_Online-1.pdf (በእንግሊዘኛ ይገኛል)።

## 8. ማህበረሰብ እና አንድነት—ውጪያዊ ሰነዶች

8.1.1 SEMA Network, Breaking the Silence: Turning Pain into Power https://www.mukwegefoundation.org/wp-content/uploads/2022/12/FINAL-Breaking-the-silence-265x265-2.pdf (በእንግሊዘኛ ይገኛል)።

8.1.2 International Coalition of Sites of Conscience, Pathways of Innovation: Civil Society Advancing Transitional Justice—Chapter 6: Engaging Survivors Through Participatory Methods And Psychosocial Support In Guinea https://www.sitesofconscience.org/2020/03/pathways-of-innovation-civil-society-advancing-transitional-justice/ (በእንግሊዘኛ እና በፈረንሳይኛ ይገኛል)።

## የመጨረሻ ማስታወሻዎች

1. United Nations Security Council Resolution 2467 (2019): www.un.org/shestandsforpeace/sites/www.un.org.shestandsforpeace/files/unscr_2467_2019_on_wps_english.pdf.
2. "Five Gains and Gaps in the Campaign to End Conflict-Related Sexual Violence," Chantal de Jonge Oudraat and Kathleen Kuehnast, Ph.D., United States Institute of Peace (November 2023): www.usip.org/publications/2023/11/five-gains-and-gaps-campaign-end-conflict-related-sexual-violence.
3. Dara Jay Cohen, "Going Beyond Accountability to Deter Conflict-Related Sexual Violence," United States Institute for Peace: https://www.usip.org/publications/2023/03/going-beyond-accountability-deter-conflict-related-sexual-violence.
4. Schulz and Kreft, "Accountability for Conflict-Related Sexual Violence": https://doi.org/10.1093/acrefore/9780190846626.013.702.



ተጨማሪ ንባብ

International Coalition of
SITES *of* CONSCIENCE

www.sitesofconscience.org

Facebook.com/SitesofConscience
@SitesConscience
SitesofConscience

GIJTR
Global Initiative for Justice
Truth & Reconciliation

www.gijtr.org

@GIJTR
@GIJTR